ከወገኖቻቸው ያገኙት ምክርና አስተያየት፣ ሀሳባቸውን በበለጠ ሊያጠናክርላቸው ቻለ። ከንጉሠ ነገሥቱና ከጸሐፌ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጋር ስረዥም ሰዓቶች ሲነጋገሩ፤ እንድም ጊዜ ፌዴሬሽን ስለማፍረስ ሆነ ስለማላላት ጥያቄ አለመነሣቱ፣ አዲሉ ፌዴራሊስት የሆነውን ዕቅዱን ከግቡ ለማድረስ ችግር አይገጥመኝም ብለው አመኑ።

በጣም ያስቸግሩኛል የሚሏቸው ቢትወደድ አንዳርጋቸውና ፊታውራሪ አስፍሐ፣ እንዲሸኙላቸው የተመኙት ባይፈጸምላቸውም፤ ከጃንሆይና ከወልደጊዮርጊስ የተሰጣቸው ክብርና መልካም አስተያየት እጅግ አድርጉ አስደስቷቸዋል። በዚህ አኳኋን ተድላ ባይሩ የአዲስ አበባ ጉብኝታቸውን ፈጽመው አሥመራ የተመለሱት፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን እንዲጠነክርና፣ ለመቼውም እንዲቆይ ለማድረግ ስለሆነ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖቻቸውን ችላ ማለት የመጀመሪያው እርምጃቸው ሆነ።

## ያዝልቅልዎ !

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በዘመነ ማርቆስ 1946 ዓ.ም (በአውሮፓ 1953-1954) ደጃዝማች ተድላ ባይሩ የኤርትራን ፌዴሬሽን አጠንክሮ ለማቆየት የወሰኑት፣ እንዳችም የፖሊሲ መግለጫ ሳያደርጉ፣ በአሠራር ዘዴ ብቻ በመጠቀም እንዲሆን ነበር። ከዚህም ግብ ለመድረስ፣

1ኛ/ ከአንድነት አጥባቂ ወገኖች ጋር፣ ፌዴሬሽኑ ይፍረስ ወይም አይፍረስ የሚል ንትርክ ሳይከፈት፤

2ኛ/ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ስለሚሰጠው ጥቅም፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉ አስተያየት በዲስኩርም ሆነ በጋዜጣ ሳይገለጥ እንዲከናወን፤ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረባቸው።

ደጃዝማች እንደተመከሩት፤ ድምፃቸውን ፀጥ አድርገው ለአቀዱት ዓላማ በሚጥሩበት ጊዜ፣ ከአንድነቶች በኩል እንዳችም እንቅፋት እንዳይደነቀርባቸው፣ « ..... <u>ለኤርትራ እናቷ ኢትዮጵያ ናት።</u> ..... <u>መሪዋም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ናቸው።</u> ...... » እያሉ በየዲስኩራቸውና በየመግለጫቸው ጉላ አድርጉ ለማቅረብ ፕሮግራም አቀዱ። በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኙት የአዲስ አበባዎቹ ኤርትራውያኖች፣ በትምህርትም ሆነ በሥራ ኤክስፔሪያንስ እጅግ የላቁና የታወቁ በመሆናቸው፣ ከእነሱ የተሰጠው የፖለቲካ ቴክኒክ ፍቱን መድኃኒት ነው ብለው ከልብ አመኑበት። ይሁን እንጂ አሥመራም ያሉት የማህበረ ፍቅረ ሀገር አባሎችና፣ በተለይም የአንድነት አጥባቂ ወገኖች በቀላሉ የሚበገሩ አለመሆናቸውን፣ ደጃዝማች አልተረዱትም። ከአዲስ አበባ ጠ ቅላላ የመንፈስ እደሳ ተደርጉላቸው፣ አሥመራ በተመለሱ በሁለተኛው ሳምንት መጀመሪያ ላይ፤ <u>ከአንድነት አጥባቂ ወገኖች ለቺፍ ኤግዜኩቲፉ በተጻፈላቸው ልዩ ማስታወሻ የሚከተለው አስተያየት ቀረበላቸው።</u>

« ...... ከሎኒያሊስት ጣልያን ከኢትዮጵያ የነጠላት አገራችን ኤርትራ፤ ተመልሳ ከእናቷ ጋር እንድትዋሀድ ከእኛ ጋር ሆነው፣ ከአሥር ዓመታት በላይ ያደረጉትን ከፍተኛ ተጋድሎ ለመመስከር እኛ ወንድሞችዎ ወደ ኋላ አንልም።

...... ከባዕድ አስተዳደር ተላቀን ነፃነታችንን እንችትን፣ ወደ አገራችን ወደ ኢትዮጵያ እስከ ተቀላቀልንበት ጊዜ ድረስ፣ የአንድነት ያገር ፍቅር ማህበራችን ዋና ኤሑሬያችን አድርገን የጣልንብዎትን ኃላፊነቶች በሚያስደንቅ ትጋት መፈጸምዎን ምንጊዜም አንረሳውም:: .....

...... ከእኛ ከኤርትራውያኖች ጥያቄና ፍላጐት ውጪ፣ ከእናታችን ጋር የምንቀላቀለው « ፌዴሬሽን » በተባለ በባዕድ በተፀነስ ሕግ እንዲሆን የተባበሩት መንግሥታት በፈረደብን ጊዜ፣ ሌላ ምርጫ ስላልነበረን፣ ለጊዜው ተቀብለን፤ ለትልቁ የአንድነት ግባችን እንደምንቀጥል ስንወስን፣ እርስዎ ወንድማችን ያሳዩንን እና ያሳደሩብንን የቆራጥነት መንፈስ፣ ለመቼውም አንዘነጋውም::

...... ይህንንም በግዲታ የተጣለብንን የፌዴሬሽን አስተዳደር ለመምራት ከርስዎ የተሻለ አርቆ ተመልካችና አዋቂ አይኖርም ብለን፣ ለከፍተኛው የመሪነት ሥልጣን ያበቃንዎ እኛ ወንድሞችዎ መሆናችንን፣ ይስቱታል ብለን አንጠራጠርም::

...... ይህ « ፌዴራሲዮን » የተባለ በውጪ ተንኮለኞች የተቀመመ አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የተለየን አድርጐ የሚያሳየን በመሆኑ፤ መርዙ ሳያጠፋን ቀድመን እንድናጠፋው፣ አብረን ሆነን በሰፊው የመከርነውን ይዘነጉታል ብለን አናስብም::

...... ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ሰዓት የአስተዳደሩ ወንድማችን አኳኋን እየቀዘቀዘ፤ ከእኛም ጋር ያለውን ግንኙነት እያቆመ ሲሄድብን፤ ምክንያቱን እስከምንረዳው ድረስ፣ ምን ያህል ጭንቅና ሀሳብ ላይ እንደከረምን ሳይረዱት ቀርተዋል ብለን አናምንም::

...... አሁን ግን፣ ልባዊ ሀሳብዎን፣ አኳኋንዎ ቁልጭ አርጐ እንዳቀረበልን፤ ይህንን በጊዜያዊነት የተቀበልነውን የፌዴሬሽን አስተዳደር፤ ሕያው አድርጐ ለማኖር የወሰኑ ስለሆነ፤ እኛን ወንድሞችዎን ትተው፣ ብቻዎን የመረጡትን ረዥም ጉዞ፣ « ያዝልቅልዎ » ከማለት በስተቀር የምንጨምረው የለም:: ....... »

ተድላ ባይሩ ይህን ማስታወሻ አይተው፤ ምንም ዓይነት ሥጋት አላደረባቸውም:: መጀመሪያ፣ ጽሑፉ የተላከው በመላ የማህበረ ፍቅሪ ሀገር አባሎች ስም ሳይሆን፣ በጥቂቶቹ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች የተፈረመ በመሆኑ፤ ሁለተኛ፣ አቀራረቡ የቅሬታን መንፈስ የሚገልጥ እንጂ ዛቻ ሆኖ የሚቆጠር ስላልሆነ፤ ሶስተኛ ጽሑፉ የተዘጋጀውና የተቀናበረው በፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል ተንኮል ነው ብለው በማመን፤ ደጃዝማች፤ ለጉዳዩ ቁም ነገር መስጠ ት የሚያስፈልገው መስሎ ሳይታያቸው ቀረ::

ተድላ በተፈጥሮአቸው ግልጽ የሆነ ጠባይ የሌላቸውና፣ ወዳጅ አጥባቂም ባለመሆናቸው፣ ቅን የሆነ ምክር ለማግኘት የታደሉ አልነበሩም:: ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ሆነው ከተመረጡ በኋላ፣ ከሁሉም ይበልጥ መጠንቀቅ የሚያስፈልጋቸው ምክትል እንደራሴውን መሆኑን፣ አጐታቸው አቶ ዘካርያስ ተክሌ ደጋግመው ይመክሯቸው እንደነበረ ይነገራል:: የንጉሡ ነገሥቱ ምክትል እንደራሴ ፊታውራሪ አስፍሐ፣ በፋሽስት ዘመን የናዚ አስተርጓሚ ሆነው የሰሩ፣ ሮማ ተጋብዘው በሙሶሊኒ የተሸለሙ፣ የዱካ ዳውስታን መልካም አስተያየትና ሹመት የተቀበሉ፣ የፋሽስቱ

ሊቀ ሊቃውንት የኤንሪኮ ቸሩሊ አማካሪ የነበሩ፤ ከፋሽስት ውድቀት በኋላም የጐንደርን፣ የትግሬንና የሸዋን መኳንንት አስተዳደርና ዘዴ ጠጋ ብለው ያጠኑ፣ በጠቅላላውም በጥንቱም ሆነ በዘመኑ ሥራ ብዙ ኤክስፔሪያንስ ያከማቹ ስለሆኑ፣ የፌዴራሊስቶችን ዕቅድና ፕሮግራም ለማፍረስ ጥበቡ በእጃቸው እንደሚሆን፣ ደጃዝማች ተድላ ባይሩ አልታያቸውም:: በአንድነት አጥባቂዎች ስም የተላከላቸውን ደብዳቤ በተንኮለኛው በአስፍሐ የተጻፈ ነው ብሎ ከማራከስና ንቆ ከመጣል፣ ዓላማውና ግቡ ምን እንደሆነ ቢመራመሩ ከብዙ ጥቃት ይድኑ ነበር:: <u>ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝነቴን፣ ለኢትዮጵያ ያገር ፍቅር ስሜቴን፣ በአደባባይ እየገለጽኩ፣ የኤርትራን አቶኖሚ በአሠራር አጠነክረዋለሁ</u> ብለው፣ ተድላ ባይሩ እንደፎከሩት ሁሉ፣ እነ አስፍሐም ፌዴሬሽኑን የምንገድለው በአሠራር ዘዴ እንጂ፣ በዲስኩር አይደለም ብለው ውስጥ ውስጡን መዘጋጀታቸውን፣ ደጃዝማች አልሰሙም::

ቺፍ ኤግዜኩቲፉ የሚያደርጉባቸውን ክትትል ለማደናበርና መስመሩን ወደ ሌላ አቅጣጫ ለማስለወጥ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች፣ ውጭ ውጭውን የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ፣ ....... እኛ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኢትዮጵያዊነታችንና ስለ ባለውለተኛው ንጉሠ ነገሥታችን ስሜታችንን ከመግለጽ በስተቀር፣ በደጃዝማች ተድላ መንግሥት ውስጥ ገብተን፣ ስለ አቋሙ ሆነ ስለ አመራሩ፣ ለመምከርም ሆነ ለመውቀስ፣ ጨርሶ አንሞክረውም ....... » የሚል ነበር:: ይህንን አነጋገር ደጃዝማች ተድላ የተረጐሙት የብስጭትና የኩርፊያ አድርገው ስለሆነ፤ እነ አስፍሐ በምመራው መንግሥት ውስጥ እየገቡ እስካላስቸገሩኝ ድረስ፣ እንደፈለጋቸው ይሁኑ በማለት ችላ አሉዋቸው:: የቅርብ አማካሪዎቻቸው፣ እኁታቸው አቶ ዘካርያስ ተክሌ፣ የካቢኔያቸው ዲሬክተር አቶ መስፍን ገብረሕይወት (ኋላ ፊታውራሪ) ከወዳጆቻቸውም መካከል ብላታ ደምሣስ ወልደሚካኤልና ፊታውራሪ ሐድጉ ጊላ ጋብር፣ (ኋላ ደጃዝማች) « .... ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሕገ መንግሥቱን አክብሮ፣ አቶኖሚው የሰጠውን መብት በሥራ ላይ ቢገልጠው ፌዴራሊስት አያሰኘውም:: ..... ከዚህ በላይ ደግሞ አሰካሁን እንደተደረሰበት፣ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የሚጥሩት ቢትወደድ አንዳርጋቸው እና ፊታውራሪ አስፍሐ ናቸው እንጂ ንጉሠ ነገሥቱ የሉበትም:: ..... ጃንሆይ ቢፈልጉ ኖሮ፣ በጣም የሚያምኑትንና የሚወዱትን ተድላ ባይሩን ጠርተው ይነግሩት ነበር እንጂ፤ ከነ አስፍሐ ጋር ሆነው ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ አይደልቱም ....... » እያሉ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ያለ ሥጋት ጠንክረው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ አበረታቷቸው::

ተድላ ባይሩ በዚህ በአዲሱ አቋማቸው፣ ከማህበረ ፍቅሪ ሀገር አባላት መካከል ሞዴሬቶቹን በመሰብሰብ፣ ከእስላም ሊግ ሠፈር ፌዴራሊስቶቹን በመያዝ፣ የጠነከረ ሥልጣን ይኖረኛል ብለው ተነሱ:: ይሁን እንጂ የተድላ ባይሩ የሥልጣን አጠቃቀም፤ አስተዳደሩን በሚመለከቱ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ብዙ ጊዜ ሲፈጁ፤ ባለጋራዎቻቸውን ለማጥቃት ከሆነ፣ ሕግ አየጣሱ ፈጣን እርምጃ ሲወስዱ ይታያሉ:: ከስምንት ወራት በፊት በወልደዓብ ወልደማርያም ላይ እንዳደረጉት ሁሉ፣ ከራስ ተሰማ አስበሮም ልጆች ውስጥ፣ አቶ ኢያሱ የተባለው እኔን ለመግደል ሲዝት ተሰምቷል በማለት፤ ደጃዝማች አብርሃ ተሰማን፣ አዝማች ገብረኪዳን ተሰማንና ኢያሱ ተሰማን፣ በፖሊስ አሳድነው ወህኒ ቤት ጨመሯቸው:: በሕጉ መሠረት ቢሆን ኖሮ፣ አዝማች ገብረኪዳን የፓርላማው አባል በመሆናቸው፣ ምክር ቤቱ ሳይጠየቅ መታሰር አልነበረባቸውም:: ደጃዝማች ተድላ በዚህ ብቻ አልቆሙም:: የራስ ተሰማንና የቤተሰቦቻቸውን የምስለኔነት ሹመት ነጥቀው ለሌሎች ወዳጆቻቸው አከፋፈሏቸው:: በመጨረሻው የታሠሩት ሰዎች ለተከሰሱበት ጉዳይ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስላልቻለ፣ ፍርድ ቤቱ በነፃ ለቀቃቸው::

ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ከሕጉ ውጭ በደም ፍላት ተነሳስተው፣ ይህን የመሳሰለ እርምጃ በመውሰዳቸው፣ « ተድላ ዲክታተሩ » የሚል ስም ተነዛባቸው:: የአንድነት አጥባቂ ወገኖችም፣ ምንም እንኳን ከተሰማ አስበሮም ቤተሰቦች ጋር የከረረ ጠብና ጠላትነት ቢኖራቸውም፤ ፍርድ በሥርዓቱ መካሄድ ነበረበት እያሉ፣ ውስጥ ውስጡን ወሬውን በማናፈስ፣ በተድላ ካቢኔ ላይ ሆሜታ ሲነዙ ከርመዋል::

## « ...... ጫማ በእግር ልክ ካልሆነ ..... »

*ቀ.ኃ.ሥ የካቲት 6 ቀን 1954 ዓ.ም*

በጥርና በየካቲት ወራት 1954 ዓ.ም፤ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኤርትራን ሲጎበኙ በቆዩበት ጊዜ ውስጥ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች የፌዴራሊስቱን የተድላን ካቢኔ እያቆሰሉ፣ ሕዝቡን ወደ እነሱ ለመሳብ የሚያመች ጥሩ ዕድል አገኙ::

የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ የመንግሥታቸውን የገቢ ምንጭ ከፍ አድርገው፣ የወጪ በጀታቸውን ለማስተካከል፣ ከእንግሊዞች አስተዳደር ዘመን ጀምሮ ሕዝቡ ሲከፍል የቆየው የመሬትና የቦታ ግብር፣ በእጥፍ እንዲያድግ አዋጅ አወጡ:: ለምሣሌ በዓመት ሃምሣ ብር ይከፍል የነበረው ባለ መሬት፣ ዛሬ በአንድ ጊዜ መቶ ብር ገብር ሲባል፣ ሕዝቡ በየአውራጃውና በየወረዳው መንጫጫት ጀመረ:: አገራችን ከባዕድ አገዛዝ ወጥታ የራሷን ነፃ አስተዳደር አገኘች ብለን የተደሰትነው፣ እኛን መልሶ በችግር ለመጥበስ ከሆነ፣ ጥቅሙ እምን ላይ ነው ? ...... እያለ፣ ሕዝቡ እርስ በርሱ ሲወያይ፣ አንድነቶች በየምስለኔዎቹ በኩል እየሠረጉ፣ የሕዝቡን ንዴት ለማባባስና፣ የራሳቸውን እምነት ለማሳመን መልካም አጋጣሚ ሆነላቸው::

« ...... የተባበሩት መንግሥታት ፌዴራሲዮን በተባለ ሕግ ከኢትዮጵያ ጋር እንድንቀላቀል ያደረገን፣ ከእኛ ከኤርትራውያኖች የሚሰበሰበው ግብርና ታክስ አገሩን ለማስተዳደር ይበቃል በሚል ፈረንጆች ባቀረቡት የተንኮል ሀሳብ ነው:: ...... አናንተ አሁን ያዘናችሁት ለኤርትራ መንግሥት የምትከፍሉት ግብር ከቀድሞው እጥፍ በመሆኑ ነው:: ይህ ፌዴራሲዮን የተባለው አሠራር እናንተ ገና ያልሰማችሁት፣ የሚያመጣባችሁ ተጨማሪ ዕዳ አለ:: ይኸውም የፌዴራሲዮኑ መንግሥት ለተባለችው ኢትዮጵያ፣ ሌላ ተጨማሪ ታክስ እንድትከፍሉ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ትጠየቃላችሁ:: ይኸ ፌዴራሲዮን የተባለ ነገር ባይመጣብንና ሁላችንም ከመጀመሪያው በጠየቅነው መሠረት፣ አንድ ኢትዮጵያ አንድንሆን ተፈቅዶልን ቢሆን ኖሮ፣ 1ኛ/ ለሁለት መንግሥት (ለኤርትራና ለኢትዮጵያ) ታክስ እንድንከፍል አንጠየቅም:: 2ኛ/ የምንከፍለው ግብር በአንድ ጊዜ እጥፍ እንዲሆንብን አይሞከርም ነበር:: አሁን ለዚህ ሁሉ ችግር ሕዝቡ ማድረግ ያለበት፣ ደህና ወኪል መርጦ ለንጉሠ ነገሥቱ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማመልከት ብቻ ነው ...... » እያሉ አንድነቶች በያለበት የሚነዙትን ወሬ፣ የተድላ መንግሥት ለመመከት አልቻለም::

የካቲት 6 ቀን 1954 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሠራዬን አውራጃ ሲጎበኙ፣ የኤርትራ መንግሥት ከሕዝቡ አቅም በላይ በእጥፍ እንዲከፍል የወሰነውን የመሬት ግብር፣ ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያሻሽሉት የሕዝብ አቤቱታ ቀረበላቸው:: በዲስኩር ተዘጋጅቶ በሕዝቡ ስም ለጃንሆይ የተነበበው አቤቱታ፣

የአንድነት አጥባቂ ወገኖች ምን ያህል እንደቀመሙት በትክክል ሊያስረዳ ይችላል።

« ...... እኛ የኤርትራ ታማኝ ዜጎችዎ፣ በግርማዊነትዎ ከፍተኛ ድካም ኢትዮጵያዊነታችንን እና ነፃነታችንን ካገኘን በኋላ፣ ያደረጉልን አባታዊ ችሮታዎችዎ ልባችንን የሚነኩ ናቸው። ...... በዚህ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአገራችን ላይ የተሠሩልን፣ ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች፣ መስጊዶችና ቤተክርስቲያኖች ከፍ ያለ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው። ...... አሁን በቅርቡም ኤርትራን ሲያስተዳድር የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት፣ ለኤርትራውያን መልካም አኗኗር ያወጣሁት ወደ ሰባት ሚሊዮን ብር (7,000.000) የሚጠጋ ወጪ ካልተመለሰልኝ ብሎ በመጠየቁ፤ በግርማዊነትዎ መልካም ፈቃድ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሣጥን መከፈሉን ሰምተናል። ...... እንግዲህ ኤርትራ ግርማዊነትዎን የመሰለ አባትና አሳቢ ባይኖራት ኖሮ፣ አገራችን በዕዳ የተያዘች ንብረት ሆና፣ ሰብዓዊ መብታችንን አጥተን እንቀር እንደነበረ ጉልህ አድርጐ ያስገነዝበናል። ...... እኛ ብቻችንን ራሳችንን ችለን እንድንተዳደር የተወሰነብን፣ ራሳችን ከምንከፍለው ግብር በስተቀር ሌላ የገቢ ምንጭ እንደሌለን እየታወቀ፤ ከወዴት አምጥተን ዕዳችንን እንድንከፍል ታስቦ ይሆን ? ....... በዚህ በአሁኑ ሁኔታችን ላይ እንደምንወድቅ እየታወቀ፣ የውጭ ባዕዶች በዘረጉልን የአስተዳደር ገመድ እንድንታሰር አድርገውን ሄደዋል። ...... ነፃነታችንን አገኘን በምንልበት ሰዓት ይኸው በአንድ ዓመት ውስጥ እንደሚታየው፣ የምንከፍለው ግብር መቶ በመቶ ታጥፎ ዕዳ ላይ ወድቀናል። ከዚህም በቀር ገና ያልከፈልነውና ወደፊት ለመክፈል የምንገደድበት የፌዴራል ግብር አለባችሁ እየተባለ ሲነገርብን ሰምተናል። ...... ይህንን ሁሉ ስናስበውና ስንመለከተው፣ እጃችንን ለማሰር የተደረገብን ያስተዳደር ሥርዓት ባስከተለው ችግር ምክንያት ስለሆነ፤ ከዚህ ችግር ውስጥ ሊያወጣን የሚችለው ግርማዊነትዎ ብቻ ነው። ..... ኤርትራ በሀብትና በገንዘብ ራስዋን እንደማትችል አዋቂዎች መርምረው የደረሱበት ነው። ይህ መሆኑ እየታወቀ፤ ..... <u>እንደማትችል አዋቂዎች መርምረው የደረሱበት ነው። ይህ መሆኑ እየታወቀ፤ ..... ለመኖር እኛም ከአቅማችን በላይ የሆነ ወግና ግዳጅ የሚያከብር አስተዳደር ይዞ ለመኖር እኛም</u>

<u>ከአቅማችን በላይ የሆነ ወግና ግዳጅ የሚያከብር አስተዳደር ይዞ ለመኖር እኛም ከአቅማችን በላይ የሆነ ወግና ግዳጅ የሚያከብር አስተዳደር መሬታችንም የማይችለው ነው።</u> ....... ስለዚህ፣ ዘንድሮ የተጣለብንን ግብር ለመክፈል ጨርሶ የማንችለው ስለሆነ፣ ምሕረት እንዲደረግልን፤ ለሚመጣውም ዓመት እንደ አቅማችን እንድንገብር እንዲደረግልን፣ የግርማዊነትዎን ሰፊ ችሮታና ትእዛዝ እንለምናለን። ....... »

እንደሚታየው በዚህ ዲስኩር የተገለጸው ሀሳብ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ለግብሩ ችግሯ ምሕረት እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን፤ 1ኛ/ የኤርትራ ትልቁ ችግሯ ራሷን ትችላለች ተብሎ የተሰጣት የፌዴሬሽን ሥርዓት የጐዳት መሆኑን፤ 2ኛ/ የሕዝቡን ጉዳት በቅርቡ ወግና ግዳጅ አክባሪ የተባለው የተድላ ባይሩ አስተዳደር፣ የሕዝቡን ጉዳት በቅርቡ ሆኖ ለመረዳት አለመቻሉን የሚያመለክት ነው። ለዚህ ለቀረበላቸው አቤቱታ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወዲያውኑ የሰጡት የቃል መልስ፣ በፌዴሬሽኑ ሕግ መሠረት፣ በቺፍ ኤግዜኩቲፍ የውስጥ አስተዳደር ሥልጣን በቀጥታ ለመፍረድ እንደማይችሉ፣ ሸፈንፈን አድርገው በጨረፍታ ከጠቀሱ በኋላ፣ « ..... <u>አሥመራ እንደተመለስን፣ ደጃዝማች ተድላን አነጋግረን መልሱን እንሰጣችኋለን</u> .... » አሉ።

የመሬትና የቦታ ግብር በአጠፌታ እንዲከፈል በመወሰኑ፣ የኤርትራ ሕዝብ በጠቅላላው ማዘኑና መነጫነጩ እውነት ነው። ፌዴሬሽኑ ለኤርትራ ሕዝብ የሚሰጠውን መብት ለመጠበቅና፣ በተግባር ላይ ውሎ ጥቅም እንዲሰጥ መጣር የሚገባው መንግሥት፣ በአንድ ጊዜ ግብሩን በማጠፍ በሕዝቡ ላይ ጉዳት አለብኝ የሚል መንግሥት፣

ግድሬል [illegible]ትም:: የአንድነት አጥባቂ ወገኖችም፣ ወደ ሕዝቡ በመጠጋት የተድላን አመራር ለማስጠላት የቻሉት፣ ይህ በአጠራታ የተተመነ ግብር የቀሰቀሰውን የቁጣ ስሜት በመጠቀም ነው:: ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም፣ በአንድ በኩል የነ አስፍሐን ዘዴና ፕሮግራም በሚገባ እየፈጸሙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፌዴሬሽኑን ሕግ የሚጠብቁ እየመሰሉ፣ ደጃዝማች ተድላን አነጋግረን መልስ እንስጣለን በማለታቸው፣ የዋሁ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ እጅግ ተደሰቱ::

ጃንሆይ አሥመራ ከተመለሱ በኋላ፣ በቤተመንግሥቱ ጽሕፈት ቤታቸው ሆነው እንደራሴውና ምክትሉ ባሉበት፣ ስለ መሬት ግብር አከፋፈል ጉዳይ ከሕዝብ ስለቀረበላቸው አቤቱታ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሀሳብ እንዲሰጡ ጠየቋቸው::

ተድላ፣

..... የግብሩ አዋጅ የወጣው ብዙ ጥናት ተደርጎበት ነው:: ሕዝቡ ድሮ የሚከፍለው በጣም ትንሽ ስለነበር አሁን የተጠየቀው እንደማይከብደው ተጠንቶ ታውቋል:: ...... ስለዚህ ግርማዊነትዎ አቤቱታውን ችላ ከማለት በስተቀር መልስ መስጠቱ የሚጠቅም አይመስለኝም::

አስፍሐ፣

..... ለኤርትራ ሕዝብ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከፍተኛ ገዥው እና ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ አባቱ ናቸው:: ልጅ አባቱን እባክህ አባቴ ችግር ወደቀብኝ ብሎ ሲለምን፣ አባት የሚችለውን ያደርግለታል እንጂ ችላ ብሎ አያልፈውም:: እንደዚሁም የኤርትራ ሕዝብ፣ ችግር ተጫነኝ መከራ ደረሰብኝ ብሎ ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታውንና ልመናውን ሲያቀርብ፣ ቸል ተብሎ የሚታለፍ ነገር አይደለም:: ..... አሁን ግርማዊ ጃንሆይ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን የጠየቁት፣ ከሕዝብ ለቀረበላቸው አቤቱታ ምን ማድረግ እንደሚሻል አስተያየት ለመስማት እንጂ፣ የግብሩ አዋጅ የወጣው በሕጉ መሠረት ነው ? ወይስ ከሕግ ውጪ ? ተብሎ ንግግር እንዲደረግበት አይደለም::

ተድላ፣

...... እኔ ጃንሆይ ችላ ቢሉት ይሻላል ያልኩት ሕዝባቸውን ሳይሆን፣ ለግብሩ አከፋፈል ስለወጣው አዋጅ ብዬ ነው::

አስፍሐ፣

...... መቼም ሕዝቡ ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ሲያቀርብ፣ አንድ ነገር አገኛለሁ ብሎ እንደሚጠብቅ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: ስለዚህ፣ እንደተለመደው ጃንሆይ ለሚወዱት ሕዝባቸው፣ አንድ ዓይነት ችሮታ እንዲያደርጉለት ብናስቸግራቸው፣ ክቡር ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ምን ያስባሉ ?

ተድላ፣

...... ለእኔ ጥሩ ሀሳብ ነው የምለው::

ጃንሆይ፣

...... <u>ማለፊያ ነው</u> በዚሁ ይፈጸም::

...... በዚሁ ይፈጸም ተብሎ በፍጥነት የተሰጠው ውሳኔ፣ ለኤርትራ ሕዝብ ንጉሣዊ ችሮታ ለማድረግ መሆኑ የታወቀ ነው:: ምን ዓይነት ችሮታ? ..... ለጊዜው



« ....... ጫማ በእግር ልክ ካልሆነ እንደማያራምድ ሁሉ አስተዳዳሪም በሕዝቡ አቅም መጠን ካልሠራ አስቸጋሪነቱ የማይካድ ነው ....... »

(ቀ.ኃ.ሥ የካቲት 1954 ዓ.ም አሥመራ)

**አልተገለጸም ነበር**። ምክትል እንደራሴው ፊታውራሪ አስፍሐ አጥንተው ባቀረቡት **ሐሳብ መሠረት**፣ የካቲት 8 ቀን 1954 ዓ.ም ጃንሆይ ለመላው የኤርትራ ሕዝብ **የሚያደርጉትን** ሰፊ ችሮታ ሲገልጹ፣ ባደረጉት ንግግር እንዲህ አሉ።

« ..... ያመለከታችሁትን ስምተን ችግራችሁን ተገንዝበናል። ..... በማናቸውም ጊዜ ችግራችሁን ለማቃለል የዘወትር ሀሳባችን ስለሆነ፤ <u>በእጥፍ እንድትከፍሉ የወደቀባችሁን የግብር ዕዳ ለዘንድሮው እኛ እንከፍልላችኋለን።</u> ..... የፌዴራሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ድርሻ የሆነውንም ግብር፣ ባለፈው ዓመት ከንጉሠ ነገሥቱ ግምጃ ቤታችን እንዲከፈልላችሁ በተደረገው ዓይነት የዘንድሮውም እንደዚሁ ይቀጥላል ... »

ይህ ትልቅ የምሥራች ቃል በሕዝቡ ላይ ምን ያህል ከፍተኛ ደስታ እንደፈጠረ መገመት ያስቸግራል። ...... ይህ ፌዴሬሽን የተባለ አስተዳደር የግብሩን ሂሣብ በአንድ ጊዜ እጥፍ አድርጐ በሕዝቡ ላይ ያደረሰውን ሥቃይ፣ ሩህሩህ የሆኑት ንጉሠ ነገሥቱ በድንገት ደርሰው ከመከራው አላቀቁት። ...... ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሚወዱት የኤርትራ ሕዝባቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ስለአሳዘናቸው፣ <u>በአጠፌታ የተጠየቀው የግብር ሂሣብ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ግምጃ ቤት ወጪ ሆኖ በሕዝቡ ስም ለኤርትራ አስተዳደር እንዲከፈል አዘዙ።</u> ...... በተጨማሪም ኤርትራውያኖች መክፈል የነበረባቸውን የፌዴራል ታክስ ባለፈው ዓመት እንዳደረጉት ቸርነት ዘንድሮም ምሕረት አደረጉላቸው ....... » <u>እያሉ፣ አንድነቶች ዓላማቸውን በሕዝቡ ለማሳመን ደህና አድርገው ሠሩበት።</u>

ጃንሆይ በኤርትራ በቆዩባቸው ጊዜያቶች ውስጥ ለሕዝቡ ካደረጓቸው ንግግሮች መካከል፣ በሁለቱ ዲስኩሮቻቸው ውስጥ በአንዳንድ ዓረፍተ ነገሮች የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ቅር ተሰኝተዋል እየተባለ ይነገራል። ይኸውም፣ የመጀመሪያው የሠራዬን አውራጃ በጐበኙ ጊዜ፣ « ..... ወደ ኤርትራ በመምጣታችን በጣም ደስ የሚለን ችግራችሁን ለማቃለል ነው እንጂ <u>ለተድላና ለደስታ አይደለም</u> ...... » ሲሉ የተናገሩት ነው። ለተድላ ሲባል ምቾት ለማለት ስለሆነ፣ ከአማርኛ አጥረት ካልሆነ በቀር ደጃዝማች ተድላን የሚነካ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ስለ አጠፌታው ግብር ለሕዝቡ ንጉሣዊ ችሮታ ሲያደርጉ በተናገሩት ውስጥ፤ እንዲህ የሚል ቃል ይገኝበታል። « .... <u>አስተዳዳሪ እንደ አደረጉት ነው። ሆኖም፣ ጫማ በእግር ልክ ካልሆነ እንደማያራምድ ሁሉ፣ አስተዳዳሪም በሕዝቡ አቅም መጠን ካልሠራ አስቸጋሪነቱ የማይካድ ነው።</u> ...... » ይህ ንግግር በቀጥታ የተድላ ባይሩን መንግሥት አይመለከትም ብሎ መከራከር አይቻልም። የጃንሆይን ዲስኩር ያዘጋጁት ፊታውራሪ አስፍሐ፣ ይህችን ቃል የቀመሟት ለማን ኖርዋል ? ብዬ ደጋግሜ ብጠይቃቸው፤ ...... እኔ ብጽፈውም መምሪያው የወረደው ከላይ ነው። ከዚህ ሌላ የምጨምረው የለም ..... » ብለውኛል። ያም ሆነ ይህ፣ ቃሉ የተሰነዘረው የተድላን መንግሥት የሚመለከት ለመሆኑ አላጠራጠረም። ንጉሠ ነገሥቱ በኤርትራ የሚያደርጉትን ጉብኝት ፈጽመው ከተመለሱ በኋላ፣ አንድነቶች የተድላ ባይሩን ሞራል ለመንካት፣ ..... <u>ጫማ በእግር ልክ፣ አስተዳዳር በአቅም መጠን፣</u> ካልሆነ ...... የሚለውን ቃል በስፊው ተጠቅመውበታል።

እንደሚታወሰው፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች፣ ውስጥ ውስጡን ከንጉሠ ነገሥቱ የሞራል ድጋፍ እያገኙ፣ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር የሚያደርሰውን ጉዳት ሕዝቡ ተረድቶት ለማፍረስ እንደሚቻል ሙሉ ተስፋ አድርገዋል። ደጃዝማች ተድላና ወገኖቻቸው ደግሞ፣ ፌዴሬሽኑ ለኤርትራ ሕዝብ ያስገኘለትን መብት

በተግባር እያሳየን፤ ቋሚ መተዳደሪያ እንዲሆን እናደርጋለን ብለው ተነስተዋል:: ይሁን እንጂ በእነዚህ በጥቂት ወራቶች ውስጥ እንደታየው ከሆነ፤ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች አንድ እርምጃ ወደፊት ሲጓዙ፤ የተድላ ካቢኔ ደግሞ የማብሩና የታክሱ ጉዳይ እንዳመለከተው፤ ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ የተራመደ ሆኖ ተገኝቷል::

# ፌዴሬሽኑ፣ በሕይወት አለ ወይ?

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለብዙ ሳምንታት በኤርትራ በከረሙበት ስሞን፣ ሕዝቡ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር እያወዘ ወደ ፍጹም መዋህድ እንዲያመራ፣ የአንድነት ወገኖች በያለበት የለኳኩሱት እሣት፤ ቀስ በቀስ እየተቀጣጠለ የተድላን መንግሥት መለብለብ ያዘ::

ጃንሆይ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላ፣ የካቲት 22 ቀን 1954 ዓ.ም ሀያ ስድስት (26) የእስላም ሊግ ወገኖች የሆኑ የፓርላማ አባሎች፣ ንጉሠ ነገሥቱ የሕዝቡ የግብር ዕዳ ከፋይ የሆኑት በኤርትራ የውስጥ አስተዳደር ገብተው ስለሆነ፣ አስቸኳይ ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ጠየቁ:: ደጃዝማች ተድላ ወዲያውኑ በሰጡት መልስ፣ ፓርላማው የሁለተኛውን ዓመት መደበኛ ስብሰባ ከሶስት ሳምንት በኋላ ስለሚጀምር፣ ከዚያ በፊት አስቸኳይ ስብሰባ ማድረግ አያስፈልግም አሉ:: ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ይህን እርምጃ የወሰዱት፣ ከጠቅላላው አባሎች ውስጥ አንድ ሶስተኛውን ቁጥር የሚሞሉ መማክርቶች፣ ልዩ ስብሰባ ለመጠየቅ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ ቁጥር 2 የሚሰጣቸውን መብት በመጣስ ነበር:: እነዚህ ሀያ ስድስት መማክርቶች በዚያን ሰዓት መብታቸው እስከምን ድረስ እንደሚፈቅድላቸው በትክክል ስላላወቁት፣ ፓርላማው እስኪከፈት ሶስት ሳምንት ጠብቁ የተባሉትን የፍርደ ገምድል ውሳኔ ሳያንገራግሩ ተቀበሉ::

በአሥመራ ነዋሪ የሆኑት የሶስቱ ታላላቅ መንግሥታት ቆንስል ጄኔራሎች (የእንግሊዝ፣ የአሜሪካና የፈረንሣይ) ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የኤርትራን የውስጥ አስተዳደር መብት እየጣሱ የሚያደርጉት ውሳኔ ሁሉ ለፌዴሬሽኑ ሕይወት እጅግ አስጊ መሆኑን ለየመንግሥቶቻቸው አስታወቁ:: ከሎንዶን የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አዲስ አበባ ላለው አምባሳደሩ በላከው ደብዳቤ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የኤርትራን ፌዴሬሽን አፍርሶ አስተዳደሩን ለመጠቅለል ማሰቡ በሰፊው ስለሚነገር፤ ንጉሠ ነገሥቱን ለማስጠንቀቅ ማስፈለግ አለማስፈለጉን በቶሎ መወሰን አለብን:: ስለዚሁ፣ ያንተን አስተያየት እንጠብቃለንና በቶሎ ግለጽልን ሲል ጠየቀው:: « ..... በአሁኑ ጊዜ እየተበላሸ የሚታየውን የኤርትራ ፌዴሬሽን አስተዳደር፤ የተቃዋሚዎቹ ወገኖች ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታት ያቀረቡ እንደሆነ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ኢትዮጵያን እንደማትደግፍ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል:: ...... ነገር ግን ይህንን አቋማችንን ለንጉሠ ነገሥቱ ከማቅረባችን በፊት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የወሰዳቸውን እርምጃዎች የሚያሳዩ አጥጋቢ ማስረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቢሆን ይሻላል .... » በማለት፤ አምባሳደሩ አስተያየቱን አቀረበ:: በዚህ ሀሳብ መሠረት አሥመራ ያለው የታላቋ ብሪታንያ ቆንስል የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ውስጥ ውስጡን የሚጐነጉነውን ፈልጐ በማስረጃ ለመጨበጥ ጥረቱን ቀጠለ:: ሆኖም፤ እነ ፊታውራሪ አስፍሐ ያጠሩትን ክልል ጥሶ ለመግባትና የሚመኘውን ለማግኘት ሙከራው ሊሳካለት አልቻለም::

መጋቢት 8 ቀን 1954 ዓ.ም ፓርላማው ከመከፈቱ ከአንድ ሣምንት በፊት፣ የታላቋ ብሪታንያ ቆንስል ጄኔራል ወደ ቺፍ ኤግዜኩቲቭ ቢሮ ሄዶ፣ የገለጻላቸው ሁኔታ ደጃዝማችም የሰጡት መልስ የሚከተለው ነበር:: በአንድነቶችና በፌዴራሊስቶች መካከል ካለፉት ወራቶች ጀምሮ የተፈጠረው ጠብ እንደዚሁ እየቀጠለ ከሄደ፣ ለአገሩ ሠላም አስጊ እንደሚሆን ስሜቱን ከገለጸ በኋላ፣ የተድላ ባይሩ መንግሥት ዓላማውንና እምነቱን ለሕዝቡ ማብራራት ይገባዋል ሲል፣ የእንግሊዙ ወኪል በጥብቅ አሳሰበ:: ከዚህም በቀር ቆንስሉ እንዳስተዋለው፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት የተላኩት ባለሥልጣኖች ከሚገባቸው ሥልጣን እያለፉ፣ በኤርትራውያኖች ላይ የሚያሳዩት የበላይነት መንፈስ፣ የፖለቲካውን ፕሮብሌም የበለጠ እንዳባባሰው ተመልክቻለሁ አለ:: በጠቅላላው በኤርትራ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በራሱ አመለካከት የመሰለውን ዘርዝሮ ከተናገረ በኋላ፣ 1ኛ/ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ በሚጥሩትና ፌዴሬሽኑን ለማጠንከር በሚፈልጉት መካከል፣ የተድላ መንግሥት እውነተኛው አቋሙ ምን እንደሆነ፣ 2ኛ/ በንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴና በቺፍ ኤግዜኩቲቭ መካከል፣ የተፈጠሩት ችግሮች ምንና ምን መሆናቸውን፣ 3ኛ/ በዚህ ሁሉ ጉዳይ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የራሳቸው ሀሳብ ምን እንደሆነና፣ የኤርትራንም የውስጥ ችግር እስከምን ድረስ የተረዱ መሆናቸውን፣ ቺፍ ኤግዜኩቲቭ እንዲገልጹለት ቆንስሉ ጠየቀ::

ደጃዝማች ተድላ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች፣ ቆንስሉ እንደጠበቀው መልሱን በየጉዳዩ እየለዩ በዝርዝር መስጠት አልፈለጉም:: ሆኖም እንደራሴው ቢትወደድ አንዳርጋቸውም፣ ከሥልጣን ወሰናቸው ውጪ በቺፍ ኤግዜኩቲቭ ሥራ ውስጥ እየገቡ የሚፈጽሙትን ተገቢ ያልሆኑ ሥራዎች አልደበቁም:: በእንደራሴው ጣልቃ ገብነት ምክንያት በሥራቸው ላይ ብዙ እንቅፋቶች ቢያጋጥሟቸውም፣ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያላቸው ዕምነትና አክብሮት የማይዛባ መሆኑን፣ በሰፊው አስረድተዋል::

እንዲሁም ለልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት የሥልጣን ዘርፍ ተደልድለው ከአዲስ አበባ የመጡት ባለሥልጣኖች ሁሉም ሥራቸውን ያከናወኑት በጨዋነትና በመግባባት መንፈስ መሆኑን እና፣ ከእነሱም መካከል አቶ ፋንታዬ ወልደዮሐንስ፣ አቶ በፈቃዱ ወልደሚካኤል የረቀቀ ችሎታቸው የሚመሰገን ነው ሲሉ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲቭ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: ቆንስሉም በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ይህን ያህል እምነት ካለ፣ በአሁኑ ሰዓት ኤርትራ የምትገኝበትን ሁኔታ ሕዝቡ እንዲያውቀው ለምን እውነቱ ተገልጦ አይነገረውም ? ብሎ ሲጠይቃቸው፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለፓርላማው የፖሊሲ መግለጫ ንግግር እንደሚያደርጉ አስታወቁት:: የታላቋ ብሪታንያ ቆንስልም ቺፍ ኤግዜኩቲቭ ባሳዩት የተዝናና መንፈስና ዕምነት ተገርሞ፣ ከአንድ ሳምንት በኋላ ፓርላማው ሲከፈት፣ የኤርትራው መሪ የሚሰጡትን መግለጫ ለመስማት በናፍቆት የሚጠብቅ መሆኑን ገልጾ ተሰናበታቸው::

ከዚህ በላይ እንደታየው፣ደጃዝማች ተድላ ለቆንስሉ በሰጡት መልስ ውስጥ በአንድነቶችና በፌዴራሊስቶች መካከል ባለው ትግል፣ የእሳቸው መንግሥት ከማን ወገን እንደሆነ አልገለጹለትም:: ከቢትወደድ አንዳርጌ ጋር ያላቸውንም አለመግባባት ሲገልጡ፣ የአንድነቶች ዋና ሰው የሆኑትንና የተድላን መንግሥት በልዩ ልዩ ዘዴ የሚያጠቁትን ፊታውራሪ አስፍሐ ጨርሶ አልጠቀሷቸውም::

መጋቢት 15 ቀን 1954 ዓ.ም የኤርትራ ፓርላማ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በሚያደርጉት የዘውድ ዲስኩር፣ በሥነ ሥርዓት የሚከፈትበት ዕለት ነበር:: ባለፈው ዓመት ሚያዝያ 27 ቀን 1953 ዓ.ም የፓርላማው መደበኛ ስብሰባ ሲከፈት፣ የንጉሠ ነገሥቱ መልዕክት ያለ ሕዝቡ ፈቃድ ፌዴሬሽኑን ማንም እንደማይነካው ዋስትና ሰጥቶ ስለነበረ፣ ዘንድሮ ደግሞ ምን አዲስ ነገር እንሰማ ይሆን ? በማለት በጉጉት የሚጠብቁት ጥቂቶች አልነበሩም::

ፌዴራሊስቶቹ፣ የኤርትራ ኦቶኖሚ በሕጉ መሠረት እንዲሠራበት፣ ከአዲስ አበባና ከእንደራሴው ጽሕፈት ቤት የሚደረገው ጣልቃ ገብነት እንዲቆም፣ ንጉሠ ነገሥቱ በመልዕክታቸው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ብለው ያምናሉ:: አንድነቶች፣ የኤርትራ መንግሥት የአገሩን አቅምና መጠን ሳይመዝን በግብር አከፋፈል በሕዝቡ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲያቆም፣ በዘውዱ ዲስኩር መነገር አለበት ይላሉ:: የውጭ አገር መንግሥታት ወኪሎች ደግሞ፣ ስለ ፌዴሬሽኑ ሕይወት ከመንግሥቱ መሪ የሚሰጠው የፖሊሲ መግለጫ፣ ምን እንደሚሆን ለማወቅ ይጠብቃሉ:: በዚህ አኳኋን ሁሉም በየበኩሉ የሚመኘውን ለመስማት ሲዘጋጅ፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በፓርላማው ስብሰባ ላይ ወጥተው ያነበቡት የዘውድ ዲስኩር፣ የፖለቲካውን ጉዳይ በሙሉ ሠርዞ በልማት ሥራዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሆኖ ቀረበ::

የፌዴሬሽኑ አስተዳደር በተጀመረ በአሥራ ስምንት ወራት ውስጥ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልካም ፈቃድ ለኤርትራ ሕዝብ ልማት፣ ከኢትዮጵያ በኩል የተሰጠው እርዳታ ሀምሣ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ($50.000.000) መድረሱን የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ለፓርላማው ሲያስታውቁ፣ ከአንድነት ወገኖች በስተቀር፣ ሌሎቹ በሙሉ የደስታ መግለጫ ጭብጨባ ለማድረግ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ:: በዚያን ዘመን ኢትዮጵያ በነበራት አቅም፣ በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ሀያ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለአንድ ክፍለ ሀገር ልማት ስትከነዳ፣ ምን ያህል ከባድ ወጭ መሆኑን ለማድነቅ አልፈለጉም:: የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ባጭር ጊዜ ውስጥ ለኤርትራ ያደረጉት ይህ ታላቅ ችሮታ፣ እስካሁን በምን አኳኋን በተግባር ላይ እንደዋለና እንደሚውል፣ የመንግሥቱ መሪ ተድላ ባይሩ ያስረዳሉ ተብለው ሲጠበቁ፣ የልማት ሥራዎቹን በቀጥታ የሚያካሂዱትና ራፖሩንም ለፓርላማው የሚያቀርቡት የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ሆነው ተገኙ::

- በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ፣ አሥመራ ላይ ለሰባት መቶ ተማሪዎች የሚሠራው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕንፃ፣ በመፋጠን ላይ ነው:: .......

- የምዕራቡን ቆላ ሕዝብ ለመርዳት፣ ሆስፒታልና የሕክምና ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ የጃንሆይ ትእዛዝ ስለደረሰኝ፣ ፕላኑን በማዘጋጀት ላይ ነኝ:: ......

- በናቅፋና በቃሮራ አውራጃ ያለው ሕዝብ፣ ለጤናው መጠበቂያና ልጆቹን ለማስተማሪያ ምን እንደሚያስፈልገው አጥንቼ እንዳቀርብ በታዘዝኩት መሠረት፣ ጥናቱን በማጠናቀቅ ላይ ነኝ:: .......

- በአሰብ አውራጃ መስጊድና ሆስፒታል እንዲሠራ ግርማዊነታቸው ስለአዘዙኝ፣ የሕንፃዎቹ ሥራ እንዲጀመር ከተቋራጩ ጋር ውሉን በመፈራረም ላይ ነኝ:: ....

- **ዐኤፍትራ፤** አማካይ በሆነ ሥፍራ ከፍተኛ የርሻ ትምህርት ቤት እንዲቋቋም፣ የግርማዊነታቸው ትእዛዝ ስለደረሰኝ ፕላኑን በማፋጠን ላይ ነኝ። ..... ወዘተ ....

ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን፣ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ በኤርትራ የተፈጸሙትንና ወደፊትም በመሠራት ላይ ያሉትን የልማት ፕሮግራሞች ሲዘረዝሩ፤ <u>የተድላ ባይሩ መንግሥትና ፌዴሬሽኑ በሕይወት አሉ ወይ ? ብሎ መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ነበር።</u> ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር የተቀላቀለችው በሕግ የተዘረዘረ የውስጥ አስተዳደር ሥልጣን ተሰጥቷት መሆኑ የታወቀ ነው። በመከላከያና በውጭ ጉዳይ፣ በፋናንስና በውጭ ንግድ፣ በመገናኛዎችና በወደብ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር፤ ሌሎቹ የርሻው ልማት ሆነ የጤናው፣ የትምህርቱ ሆነ የማህበራዊ አገልግሎቱ በጠቅላላውም ለየአውራጃው ልማት ኃላፊነቱ የሚመለከተው ቺፍ ኤግዜኩቲፋን እንጂ፤ ክቡር እንደራሴውን አልነበረም። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 13 መሠረት ለፓርላማው መክፈቻ የሚደረገው የዘውድ ዲስኩር፣ ኢትዮጵያንና ኤርትራን በሚያገናኙ የጋራ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆን ነበረበት። « ...... እኛ ፌዴሬሽኑን በአሠራር ዘዴ እንገድለዋለን እንጂ፣ በዲስኩር አናፈርሰውም ...... » ሲሉ፣ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች እንደተናገሩት ሁሉ፣ የንጉሠ ነገሥቱም እንደራሴ ከአንድነቶች ጋር በመሆን፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉን ሥልጣንና መብት በተግባር የነጠቁ ሆነው ተገኝተዋል።

በዚህ በመጋቢት 15 ቀን 1954 ዓ.ም ለፓርላማው መክፈቻ የተደረገውን የዘውድ ዲስኩር በጥሞና ያዳመጡ ሁሉ፣ ከእንግዲህ ወዲህ የኤርትራ ፌዴሬሽን በሕይወት ይቀጥላል ለማለት ተስፋ የለም አሉ። የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በኤርትራ መንግሥት ሥልጣን ውስጥ ገብተው፣ የፕላንና የልማት ሪፖርት አቅራቢ ሲሆኑ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ አንዳችም እርምጃ አለመውሰዳቸው፣ የተቃዋሚዎቹ ክፍሎች « ተድላ የፌዴሬሽኑ ተባባሪ አፍራሽ » ነው የሚል ስም ሰጧቸው። የኃያላኖቹ መንግሥታት ወኪሎችም፣ ለየመንግሥታቶቻቸው ባስተላለፉት ዜና፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የኤርትራን ፌዴሬሽን ለማፍረስ መወሰኑ፣ አያጠራጥርም አሉ።

እንግዲህ ለተድላ የሚበጃቸው ምንድን ነው? አንድነቶች ተቀይመዋቸዋል። የእስላም ሊግ አባሎች ተቃውሞአቸውን አጠንክረውባቸዋል። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የነበራቸው የሞቀ ባለሟልነት ተቀንሶባቸዋል። በኤርትራ ጉዳይ፣ አለን አለን የሚሉት፣ የታላላቆቹ መንግሥታት ወኪሎች፣ ለሥልጣን ብቁ ያልሆነ ደካማ ሰው አድርገው ቆጥረዋቸዋል። ከርስዎ ጋር ነን ብለው ከሚያጨበጭቡላቸው ሞዴሬቶች የሚያገኙት ድጋፍ፣ የሸንበቆ ምርኩዝ ሆኖባቸዋል። በዚህ ሁሉ ሁኔታ ተድላ ባይሩ፣ የኤርትራ « መራህ መንግሥቲ » ነኝ ብለው ብዙ ለመኖር ስለማይችሉ፤ አንድ ውሳኔ ማድረግ ይኖርባቸዋል እየተባለ፣ ወሬው በስፊው ሲፋፋም ከረመ። ምን ዓይነት ውሳኔ ? ......

# ፌዴሬሽኑ ቢፈርስልኝ?.....

ተድላ ባይሩ

የኤርትራ ፌዴሬሽን እየጠነከረ እንዲኖር ለማድረግ፣ ከአንድ ዓመት በፊት ደጃዝማች ተድላ ሲወስኑ፣ ወገኖቻቸው አንድነቶች « እኛን ትተው የመረጡትን ረኸርም ጉዞ ያዝልቅልዎ » ብለው በብስጭት የተመረዘ ምኞት እንደአቀረቡላቸው ይታወሳል::

አዲሱ የተድላ ፌዴራሊስት ፕላን በሥራ ላይ መዋል በጀመረ በአሥራ ሁለት ወራቶች ውስጥ፣ በሕዝቡ ዘንድ ጥላቻና ቅያሜ እየተስፋፋ፣ በፓርላማ የተቃዋሚዎች ቁጥር እየበረከተ፣ አንድነቶች በየቦታው የሚጠምዱት ተንኮል ብዙ ችግር እየፈጠረ፣ አዲስ አበባ ከንጉሠ ነገሥቱ ይገኝ የነበረው መልካም አስተያየት እየቀነሰ፣ የቢትወደድ አንዳርጌና የፊታውራሪ አስፍሐ ሥልጣን እየጨመረ በመሄዱ፣ ተደራርበው የመጡትን ፕሮብሌሞች ለመቋቋም « መንግሥቲ ተድላ » አቅምና ዘዴ የሌለው ባይተዋር ሆኖ ተጋለጠ::

ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ በነዚህ በተዘረዘሩት ምክንያቶች፣ አምና ዘመነ ማርቆስ ሲጀመር የወጠኑትን የፌዴሬሽን ማጠናከሪያ ዕቅድ፣ ልክ በዓመቱ የዘመነ ሉቃስ ጉሕ ሲቀድ፣ መቀልበስ ግዴታ ሆነባቸው:: ለአሥራ ሁለት ወራት ያህል ከፌዴራሊስቶች ጋር ሲጋልቡ የነበሩት ደጃዝማች፣ ወደ አንድነቶች ለመመለስ ፍላጐታቸውን የገለጹት፣ መስከረም 11 ቀን 1954 ዓ.ም (በኢትዮጵያ አቆ. መስከረም 1 ቀን 1947 ዓ.ም) የኤርትራ ከኢትዮጵያ መቀላቀል የሁለተኛው ዓመት በዓል በተከበረበት ዕለት ነበር:: ተድላ ባይሩ ታሪካዊ ዲስኩራቸውን የከፈቱት « ...... በየዓመቱ በታላቅ ደስታ የምናከብረው ይህ ዕለት፣ የኛ የኢትዮጵያውያኖች የድል ቀን ነው፣ ብለን ልንጠራው ይገባናል...... » በሚል ማሳሰቢያ ሆነ::

ቺፍ ኤግዜኩቲፉ በዚህ በረኸሙ ዲስኩራቸው ውስጥ፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለኤርትራ ሕዝባቸው የፈጸሟቸውን ታላላቅ ሥራዎች በማስታወስ፣ የኢትዮጵያዊነትን ጥቅምና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መሪነት እያጋነኑ ስሜታቸውን በሰፊው ገለጹ:: ቀጥለውም ባለንበት ዓለም ፌዴሬሽን የተባለው የአስተዳደር ሥርዓት፣ በተለይ በአሜሪካን አገር በተግባር የዋለው እንዴት እንደሆነ፣ ከኤርትራ ፌዴሬሽን ጋር እያስተያዩ፣ ልዩነቱን ለማስረዳት ከሞከሩ በኋላ፣ የኤርትራ ጉዳይ በዓለም ማህበር የተወሰነው፣ በምን መንፈስና በምን ዓይነት አስተሳሰብ እንደነበረ ለማስታወስ፣ ዛሬ የምናከብረው በዓል ይጠ ይቀኛል አሉ::

« ...... የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራን በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ያደረገው፣ በሁለቱ አገሮችና ሕዝቦች መካከል ከጥንት ጀምሮ ያለውን የዘርና የባሕል፣ የታሪክና የጂዎግራፊ ግንኙነታቸውን፣ ከዚህም በላይ ለብዙ ሺህ ዓመታት አንድ ሆነው በአንዲት ኢትዮጵያ ስም የኖሩ መሆናቸውን አምኖበት ነው:: ....... የተባበሩት መንግሥታት የኤርትራን ጉዳይ ለመወሰን የረኸም ጊዜ ጥናት ባከናወነ ጊዜ፣ የአገራችንን የወደፊት ዕድል ከጣልያን ወይም ከእንግሊዝ፣ ከሱዳን ወይም ከግብፅ፣ ከዚያም ርቆ ከፓኪስታን ጋር እንዲሆን አላሰበም:: የኤርትራን ጉዳይ የወሰነው፣ ፍርዱ ትክክል ለመሆኑ ከማያጠራጥረው

ከኢትዮጵያ ጋር በማቀላቀል ነው:: ...... ስለዚህ፣ ከእናት አገራችን ከኢትዮጵያ ለይቶን የነበረው የመረብ ድንበር ተሰብሮ ኢትዮጵያዊነታችን ከተመለሰልን በኋላ፣ ሌላ አዲስ መረብ ለመፍጠር የሚፈልጉት ጠላቶቻችን፣ ተቀባይ የሌላቸው መሆናቸውን እንዲገነዘቡት እንፈልጋለን:: እንዲሁም የሱዳንን፣ የግብፅንና የፓኪስታንን እርዳታ አግኝተን፣ የተገነባውን አንድነታችንን እናፈርሳለን ብለው ለሚያልሙት ባለጋራዎቻችን፣ ምኞታቸው ሁሉ ከንቱ መሆኑን እንዲያውቁት እንመክራቸዋለን:: ...... »

ደጃዝማች ተድላ እንደዚህ እያሉ ሲናገሩ፣ የዲስኩራቸው ማስሪያው ወይም መደምደሚያው ምን ይሆን ? እያሉ፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴና ምክትሉ፣ የፓርላማው አባሎችና እንግዶቹ፣ በተለየ ስሜት ስለተጠባበቁ፣ በጣም ረዥም የሆነውን ንግግር ለማድመጥ የተሰላቸ አልነበረም:: በልማድ እንደሚታወቀው፣ የፓለቲካ ዲስኩር ከአጀማመሩ የመጨረሻውን ግብ የሚያመለክት ስለሆነ፤ በበዓሉ ላይ የተገኙት የእንግሊዝ፣ የአሜሪካና የፈረንሣይ ቆንስሎች፣ ካሁን ካሁን የፌዴሬሽኑ መፍረስ ሊገለጥ ነው በማለት፣ ከአገሩ ሰዎች ይልቅ እነሱ ሲቁነጠነጡ ይታዩ ነበር:: በዚህ አኳኋን የበዓሉ ተካፋዮች ሁሉ ፍጻሜውን ለመስማት ከፍ ባለ ጉጉት ሲጠባበቁ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ተድላ በዲስኩራቸው መደምደመያ ላይ ያሙሁት ጥይት እንደተፈራው ባይሆንም ማስደንገጡ አልቀረም::

« ....... የኤርትራ መንግሥት መሪ ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ ስለአገራችን የወደፊት ዕድል ምን ይሆን የሚያስበው ? እያሉ ብዙ ሰዎች መጨነቃቸውን ስለማውቅ፣ ለዚህ ከፍተኛ ጥያቄ በዛሬው ዕለት መልሱን ለመስጠት ወስኛለሁ:: ...... የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት ተቀብዬ፣ ንጉሠ ነገሥቴንና አገሬን ከልብ በማገልገል በቆየሁበት በእነዚህ በሁለት ዓመታት ውስጥ፣ አንድ መሠረታዊ የሆነ ዕምነት አድሮብኛል:: ይኸውም፤ ..... ያገሬ የመረብ ምላሽ ሕዝብ፣ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከማደር ይልቅ፣ ፍጹም የሆነ ውህደት እንዲደረግ ቢመርጥ፤ ለደስታዬ ወሰን አልሰጠውም ..... » በሚል ቃል ታሪካዊ ንግግራቸውን ፈጸሙ::

ደጃዝማች ተድላ ሥልጣን ከያዙበት ካለፉት ሀያ አራት ወራቶች ወዲህ፣ ፌዴሬሽኑን በሚመለከት ጉዳይ አስተያየታቸውን በይፋ የገለጹት ለመጀመሪያ ጊዜ በመሆኑ፣ ባቀረቡት አስተያየት ያልተደነቀ አልነበረም:: በገለጹት ሀሳብ በጣም የተገረሙትም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወዳጅነት ያሟሟቋቸው የፌዴራሊስት ግሩፖች ብቻ ሳይሆኑ፤ የጥንቱ ወገኖቻቸው፣ የማህበረ ፍቅሪ ሀገር አባሎች ጭምር ናቸው:: ይሁን እንጂ አንድነቶችም ቢሆኑ፣ ምንም እንኳን የተደረገው ንግግር የሚያስደስት ቢሆንም፣ ደጃች ተድላ ብቻቸውን ተነጥለው በችኮላ የወረወሩት ሀሳብ፣ በድንገት ሳያስቡት የባረቀ ጥይት ስለሆነባቸው፣ በዚያች ሰዓት የጋለ ጭብጨባ ከማድረግ በስተቀር፣ ብድግ ብለው የድጋፍ አስተያየት ለመስጠት አልተዘጋጁም:: እንዲሁም በፌዴራሊስቶቹ ሠፈር፣ የተድላ ባይሩ ንግግር ጨርሶ ያልተጠበቀ ከመሆኑም በላይ፣ የሰውየውንም ከግሩፑ ውስጥ መሰናበት የሚነግር መርዶ ስለሆነ፤ በማናቸውም መልክ መግለጫ ለመስጠት አልቻሉም:: በኤርትራ የውስጥ ጉዳይ እየገቡ የሚፈተፍቱት የምዕራባውያን አገሮች ቆንስሎችም፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ንግግር ፌዴሬሽን እንዲፈርስ ሀሳብ የሚያቀርብ ነው ? ወይስ ፍላጉት



*« ....... ያገሬ የመረብ ምላሽ ሕዝብ፣ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከማደር ይልቅ፤ ፍጹም የሆነ ውሕደት እንዲደረግ ቢመረጥ፤ ለደስታዬ ወሰን አልሰጠውም ....... »*

*(ደጃዝማች ተድላ ባይሩ)*
*መስከረም 11 ቀን 1954 ዓ.ም*

የሚገልጽ ? የትኛው እንደሆነ ትርጉሙ በትክክል ስላልገባቸው፣ በተምታታ አስተያየት እየተደናበሩ ወደየቤታቸው ተመለሱ።

ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላ፣ በኤርትራ የግርማዊነታቸው እንደራሴ ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይና ምክትሉ ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በየበኩላቸው ለንጉሠ ነገሥቱ በላኩት ማስታወሻ፣ ስለ ዲስኩሩ የገለጹት አስተያየትና ስሜት በአቀራረቡ የተለያየ መልክ የሚያሳይ ነበር።

« ...... ደጃዝማች ተድላ ልብ እየገዛ፣ ምክራችንንም መከተል የሚጠቅመው መሆኑን ስለተረዳው፤ ይህንን የመሰለ ጠቃሚ ዲስኩር ለመናገር በቅቷል ...... » ሲሉ ቢትወደድ አንዳርጌ አድናቆታቸውን ገለጡ። ምክትሉ እንደራሴ ፊታውራሪ አስፍሐ ደግሞ፣ « ...... ደጃዝማች ተድላ ለዚህ ከፍተኛ ደረጃ ያበቋቸውን የግርማዊ ጃንሆይን ውለታ ለማስታወስና፣ የኤርትራውያኖችንም ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ለመከተል መንቃታቸውን ያሣያል ...... » አሉ። አስፍሐ አስተያየታቸውን በመቀጠል « ...... ዛሬ የገለጹትን መልካም ሀሳብ፣ ቀደም ብለው ከአንድነት ሰዎች ጋር በመመካከር የተለየ ዝግጅት ቢያደርጉ ኖሮ፣ ውጤቱ በጭብጨባ ብቻ ተወስኖ አይቀርም ነበር። አሁንም የተወራወረው ሀሳብ አየር ላይ ተንጠልጥሎ እንዳይቀር፣ በተግባር የሚገለጽበትን ጉዳይ ለማዘጋጀት፣ ደጃች ተድላ መፍጠን ይኖርባቸዋል። በኛ በትሁት አገልጋይዎችዎ በኩል የሆነ እንደሆነ፣ ግርማዊነትዎ እንዳስተማረን፣ የተሳሳተን በትዕግሥት መምከር፣ የታረመን በደስታ መቀበል ዓይነተኛ ተግባራችን ስለሆነ፣ ወደ ምድረ በዳ ከሔዱት ጉዞአቸው በደህና ከተመለሱልን ወንድማችን ጋር፣ ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆናችን የተረጋገጠ ነው ...... » ብለዋል።

የተቃዋሚዎቹ ወገኖች እነ ኢብራሂም ሡልጣንና እነ ዑመር ቃዲ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ የኤርትራን ኮንስቲቱሽን ለማፍረስ ማሰባቸውን ስለገለጹልን፣ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 75 መሠረት፣ (GRAVE VIOLATION OF THE CONSTITUTION) ተድላን ከሥልጣን ለማውረድ መነጋገር አለብን ብለው ተፍጨረጨሩ። አዲስ አበባ ያሉት፣ የእንግሊዝ የአሜሪካና የፈረንሣይ አምባሳደሮች፣ የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ በፌዴሬሽኑ ጉዳይ ስላደረጉት ንግግር፣ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት አስተያየት ለማወቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ተቀብለው ባስቸኳይ ካላነጋገረን ብለው አስቸገሩ። አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በዚህ ጉዳይ እያንዳንዱን አምባሳደር ተቀብሎ ማነጋገር አያስፈልግም በማለት፣ በዚያን ጊዜ የሚኒስቴሩ የፕሮቶኮል ሹምና ዋና ዲሬክተር የነበሩት ልጅ እንዳልካቸው መኰንን፣ ስለ ተድላ ዲስኩር የኢትዮጵያን አስተያየት ለዲፕሎማቶቹ እንዲያስረዱ ወከሏቸው።

« ...... ኤርትራ በፌዴሬሽን ከምትተዳደር ይልቅ፣ ሕዝቡ ፍጹም መዋሀድ እንዲደረግ ቢመርጥ፣ ምን ያህል ደስ እንደሚላቸው፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ምኞታቸውን ገለጹ እንጂ፣ ፓርላማው ተነጋግሮ ውሳኔ እንዲያሳልፍበት ያቀረቡት ሪዞሉሽን የለም ...... » ሲሉ፣ ልጅ እንዳልካቸው መኰንን ለየአምባሳደሮቹ መግለጫ ሰጡ። የፕሮቶኮል ሹሙ ማብራሪያቸውን በመቀጠል፣ « ...... የኤርትራ ፌዴሬሽን አስተዳደር እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ፣ ከዚያም አልፎ እንዲሠረዝ፣ ለጉዳዩ አወሳሰን ኃላፊነቱ በቀጥታ የሚመለከታቸው ኤርትራውያኖችን መሆኑን፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት መሠረታዊ እምነት ነው ...... » ካሉ በኋላ፣ እስካሁን



1/ « ...... ደጃዝማች ተድላ ልብ እየገዛ፣ ምክራችንንም መከተል የሚጠቅመው መሆኑን ስለተረዳው፣ ይህንን የመሰለ ጠቃሚ ዲስኩር ለመናገር በቅቷል ...... »

አንዳርጋቸው መሣይ
መስከረም 11 ቀን 1954 ዓ.ም

2/ « ....... አሁን የተወረወረው ሀሳብ ዓየር ላይ ተንጠልጥሎ እንዳይቀር በተግባር የሚገለጽበትን ጐዳና ለማዘጋጀት፣ ደጃች ተድላ መፍጠን ይኖርባቸዋል ....... »

አሥፍሐ ወልደሚካኤል
መስከረም 11 ቀን 1954 ዓ.ም

ድረስ እንደታየው የኤርትራ ሕገ መንግሥት ተከብሮ እንዲሠራበት፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ድጋፉንና እርዳታውን አለማቋረጡን በተጨማሪ አስገነዘቡ::

የልጅ እንዳልካቸው መግለጫ፣ በትግሪኛና በጣልያንኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅቶ በጣልያን ራዲዮ ጣቢያ ከሮማ ወደ አሥመራ ሲተላለፍ፣ ምንም እንኳን መሠረተ ሀሳቡን የለቀቀ ነው ባይባልም፣ የጣልያን ዜና አዘጋጆች አቀራረቡን በተለየ አኳኋን ስለአፋፉሙት፣ በአሥመራ ከተማ ሲንሳፈፍ የነበረውን ፖለቲካ ከግራና ከቀኝ አነቃነቀው::

የተቃዋሚዎቹ ወገኖች ተድላን ከሥልጣን ለማውረድ ጥረታቸውን ለመቀጠል ቢወስኑም፣ ከዚሁ ጋር እያይዘው የኢትዮጵያን መንግሥት ለማውገዝ የሚያዘጋጁትን ዶክመንት ይህ የልጅ እንዳልካቸው ኮሙኒኬ አከሸፈባቸው:: አንድነቶች ግን እጅግ አድርገው ተበሳጩ:: « ..... ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠው መግለጫ፣ የሕዝቡን የሞቀ መንፈስ በአንድ ጊዜ አቀዝቅዞታል:: አቶ አክሊሉ ይህን መግለጫ ያወጡት ማንን ለማስደሰት፣ ማንንስ ለመጉዳት ነው? .. » በማለት በጣም ቅር መሰኘታቸውን ለጃንሆይ በቴሌግራም አመለከቱ::

## ፌዴሬሽኑ ይቀጥል

### የጃንሆይ ውሳኔ

በአውደ ዓመቱ ማግሥት መስከረም 12 ቀን 1954 ዓ.ም፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥታቸው ከፍተኛ ስብሰባ ተደርጐ ደጃዝማች ተድላ ባይሩ ስለገለጹት ሀሳብ ምክር እንዲደረግበት ትዕዛዝ ሰጡ::

ልዑል አልጋወራሽ፣ ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር፣ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ፣ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትር፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ አቶ ተፈራ ወርቅ ኪዳነወልድ የግርማዊነታቸው ልዩ ፀሐፊ፣ አቶ ገብረወልድ እንግዳ ወርቅ የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር የስብሰባው ተካፋዮች ነበሩ::

ስብሰባው ከመጀመሩ ጥቂት ጊዜ በፊት፣ የልጅ እንዳልካቸው መኰንን መግለጫ በዓለም ራዲዮ በተለይም በቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C) ተወራ የሚል፣ ሪፖርትና ከአሥመራ የተላከው የአንድነቶች ቴሌግራም ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ሲደርስ፣ ንጉሠ ነገሥቱን የሚያናድድ ሆነ:: የጃንሆይ ቁጣ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ ይህን መግለጫ ማውጣት ለምን አስፈለገው ? ሁለተኛ ዋና ዋና የሆኑትን አምባሳደሮች እራሱ ተቀብሎ ለምን አላነጋገረም ? የሚል ነበር:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በቤተ መንግሥቱ የደረሱት ልክ በተጠሩበት ሰዓት ስለሆነ፣ የጃንሆይ የቁጣ ወላፈን ሳይነካቸው ስብሰባው ተጀመረ::

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለኤርትራ ሕዝባቸው ደህንነትና ብልጽግና በቸርነታቸው የፈጸሚቸውን ሁሉ በመዘርዘር፣ ደጃዝማች ተድላ የተናገረው ልብ የሚነካ ከመሆኑም በላይ፣ ሳይፈራ ሳያመነታ ፌዴሬሽኑ እንዲሠረዝ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱን ስሜት አስመስክሯል በማለት፣ ብዙዎቹ መሣፍንቶች ከፍ ያለ

አድናቆት ያደረባቸው መሆኑ ታውቆ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ስብሰባውን ሲከፍቱ፣ ከደጃዝማች ተድላ ባይሩ ስለ ፌዴሬሽኑ ጉዳይ በተገለጸው ሀሳብ ላይ መተቸት የሚፈልግ ሁሉ እንዲናገር መልካም ፈቃዳቸው ሆነ።

ጸ.ት ወልደጊዮርጊስ፣

የደጃዝማች ተድላ ንግግር በፖለቲካ ረገድ ሲመዘን፣ ፍሬ ነገሩ እስከምን ድረስ እንደሆነ፣ ከዚህም በላይ በተባበሩት መንግሥታት በታላላቆቹም አገሮች ዘንድ ምን አስተያየት እንደሚፈጥር፣ የግርማዊነትዎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲያስረዳ ቢጠየቅ የተሻለ ይመስለኛል።

ጃንሆይ፣

(በቁጣ ቃል) ወልደጊዮርጊስ ያልከው ማለፊያ ነው። አክሊሉ ተናገር ! ..... የምትናገረውም ስለ ተድላ ዲስኩር ብቻ ሳይሆን፣ ካንተ ቢሮ እንዳልካቸው መኰንን አምባሳደሮችን እየጠራ በመንግሥታችን ስም፣ የተድላን ዲስኩር ዋጋ እንደሌለው አድርጐ የሰጠው ቃል በምን ምክንያት እንደሆነ ማስረዳት አለብህ።

አቶ አክሊሉ፣

ደጃዝማች ተድላ ያደረገው ዲስኩር ቁም ነገሩ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ከብላታ ዳዊት እቁበእግዚእ ጋር ሆነን በረዥሙ እጥንተነዋል። በእኛ አስተያየት የኤርትራ ሕዝብ ቢፈቅድና ፌዴሬሽኑ ቢፈርስ ደስታዬ ከሰው ሁሉ የበለጠ ይሆን ነበር ብሎ በመናገሩ፤ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል አዲስ መንገድ ከፈተ እያሰኘም። ደጃዝማች ተድላ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ከልቡ የሚያምንና የቆረጠ ቢሆን ኖሮ፤ « ቢፈርስ ደስ ይለኝ ነበር » የሚል የምኞት ዲስኩር ከማድረግ ይልቅ፣ አደባባይ ወጥቶ በእሱ ኤክስፔሪያንስ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ያስከተለውን ችግር በማስረዳት፣ ሕዝቡ በድምፁ ውሳኔ እንዲያደረግ ሬፈራንዶም መጠየቅ ነበረበት። ይህንን አላደረገም። ፌዴሬሽኑ ቢፈርስ ጥሩ ነበር በሚል ቀለም ቀባብቶ ያቀረበው ዲስኩር፣ ግቡ ከአንድነት ፓርቲዎች ጋር ያስታርቀኛል ብሎ ነው እንጂ፣ ከዚህ ውጭ ሌላ ፕላን አስቦ ወይም አዘጋጅቶ አይደለም። ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው፣ በዚያ በትግሉ ዘመን ተድላ ባይሩ ከእኔ ጋር ብዙ ሠርቷል። « ..... ለኤርትራ የታሰበውን የፌዴሬሽን አስተዳደር አንቀበልም። እኛ ኢትዮጵያውያኖች ነን። የኤርትራ ሕዝብ የጠየቀው ኢትዮጵያዊነትን ነው ...... » በማለት ተድላ ባይሩ ምን ያህል እንደታገለ ከምስክሮቹ አንዱ ነኝ። እንዲሁም የኤርትራ ሕገ መንግሥት በጃንሆይ ጸድቆ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ከሆነ በኋላ፣ ተድላ ባይሩ በፌዴሬሽን የሚያምን እንጂ፣ እንዲፈርስ የሚፈልግ አለመሆኑን ደህና አድርገው ካጠኑት ሰዎች አንዱ ነኝ። ስለዚህ በእኔ አስተያየትና በእኔ እምነት ተድላ ባይሩ፣ ዛሬም ነገም፣ ወደፊትም ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ይደግፋል፣ እሱም በትግሉ ይካፈላል ብዬ አላስብም። ጃንሆይ ከማንም የበለጠ ያውቁታል። ተድላ ባይሩ ይህንን ዲስኩር ለማድረግ የተገደደው የአንድነት ፓርቲዎች በየቦታው የሚያደርጉበትን ኀንትሪግ ለመቋቋም ስለአቃተው ብቻ ነው። እሱ እንደተመኘው ሞደሬቶቹንና አብዛኛዎቹን እስላሞች አሰባስቦ በሚያገኘው ድጋፍ፣የአንድነት ፓርቲዎችን አሸንፋለሁ ብሎ ቢያምን ኖሮ፣ ይህን ዲስኩር ለማድረግ አይሞክርም ነበር። ..... ስለዚህ፤ በዚህ ዲስኩር ውስጥ ግርማዊነትዎና መንግሥትዎ እንድ ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ የሚያመች ነገር የሌለበት መሆኑን፣ የራሴንና ኃላፊ የሆንኩበትን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን አስተያየት በትህትና አቀርባለሁ።

ጃንሆይ፣

እንዳልካቸው መኰንን፣ ባንተ ውስጥ ሆኖ ሳለ፣ በመንግሥታችን ስም እንዲናገር ያደረገበትን ከነ ምክንያቱ፣ ዳግም፣ ይህን መናገር ለምን እንዳስፈለገ አስረዳ ! .....

አቶ አክሊሉ፣

ልጅ እንዳልካቸው የተናገረው እኔ በሰጠሁት ዲሬክቲፍ (መምሪያ)ነው:: በጃንሆይ ፈቃድ የፕሮቶኮል ዋና ሹምና የአውሮፓ ጉዳይ ዋና ዲሬክተር ከሆነ ስንብቷል:: በሌላው አገር እንደሚደረገው፣ ለየአምባሳደሮች ለሚሰጠው መግለጫ ዋናው ኃላፊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቢሆንም፣ እሱ ደግሞ በስሙ ሆነው ኮሙኒኬ የሚሰጡትን እንደ ጉዳዩ ዓይነት ከዲፓርተማ ኃላፊዎች ውስጥ አንዱን ይወክላል:: እኔም ይህን ሚሲዮን ለእንዳልካቸው የሰጠሁት የእሱ ደረጃና ሥራ ለጉዳዩ የሚስማማ ስለሆነ፣ በተጨማሪም በሁለት ቋንቋዎች በእንግሊዝና በፈረንሣይ ደህና አድርጎ ማስረዳት ስለሚችል ነው::......

የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ስለአደረገው ንግግር የግርማዊነትዎን መንግሥት አስተያየት ማወቅ እንፈልጋለን ብለው ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጥያቄ ያቀረቡ አምባሳደሮች ብዙ ናቸው:: በተለይ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝና የፈረንሣይ አምባሳደሮች፣ የኤርትራን ጉዳይ በቅርብ መከታተል አለብን እያሉ በየጓዳው ወሬ ሲለቅሙ እንደሚውሉ እናውቃለን:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እነዚህ አምባሳደሮች ተንኮል ባያስቡ ኖሮ፣ የተድላ ባይሩ ዲስኩር ምን እንደሚል፣ ከአሥመራ ቆንስሎቻቸው ያገኙት ነበር:: ሁለተኛም የጃንሆይ መንግሥት በዲስኩሩ ላይ ስላለው አስተያየት መጠየቅ አልነበረባቸውም:: ነገር ግን እነሱ በየቀኑ የሚከታተሉን ከነገ ዛሬ፣ ጃንሆይ ፌዴሬሽኑን ያፈርሳሉ በሚል እምነት ስለሆነ፣ እኛ ለዚህ ምቹ ላለመሆን፣

1ኛ/ ተድላ ባደረገው ዲስኩር ፌዴሬሽን እንዲፈርስ በኦፊሴል አለመጠየቁን፣

2ኛ/ የፌዴሬሽኑ መፍረስ የሚወሰነው በኤርትራ ሕዝብ እንጂ፣ በጃንሆይ መንግሥት አለመሆኑን፣

3ኛ/ የኤርትራ ሕገ መንግሥት በትክክል ሥራ ላይ እንዲውል ጃንሆይ ድጋፋቸውን ከመስጠት አለማቋረጣቸውን፣ መናገር ግዴታችን ነበር:: ልጅ እንዳልካቸውም ደህና አድርጎ ያስረዳው ይህንኑ ነው:: ..... ከዚህ ቀጥዬ ግርማዊነትዎ ቢፈቅድልኝ ስለፌዴሬሽኑ ጉዳይ ያለኝን ሀሳብ ለማቅረብ እፈልጋለሁ::

ጃንሆይ፣

ተናገር !

አክሊሉ፣

በእኔ አስተያየት በአሁኑ ሰዓት የኤርትራ ፌዴሬሽን ሳይነካ እንደዚሁ እንዳለ ቢቆይ ይጠቅመናል ብዬ አስባለሁ:: የኤርትራ ፌዴሬሽን በሥርዓት ከቀጠለና ውጤቱ ፍሬያማ ከሆነ፣ ከዛሬ ስድስት ዓመታት በኋላ፣ የሞቃዲሾና የሐርጌሣ ሱማሌዎች ከጣልያንና ከእንግሊዝ አስተዳደር ሲወጡ፣ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንተዳደር ብለው ለመጠየቅ ይሰባቸዋል:: የወጣት ሱማሌዎች የፖለቲካ መሪ

የሆነው አብዱላሂ ኢሣ፣ በቅርብ ጊዜ መጥቶ ሲያነጋግረኝ፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን እኛንም ስለሚያጓጓን አሠራሩን በቅርብ በመከታተል ላይ ነን ብሎ የነገረኝን፣ ለጃንሆይ አመለክቻለሁ:: ይህንን የጠቀስኩት ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው ወደፊት የሱማሌ ጉዳይ እጅግ የሚያሳስብ በመሆኑ ነው:: የዛሬ ስምንት ዓመት እነ ኧርነስት ቤቨን ትልቅ ሱማሌ ለመፍጠር የለኩሱት እሳት ተዳፈነ እንጂ አልጠፋም:: ስለዚህ የኤርትራን የፌዴሬሽን ሞዴል ደህና አድርገን በመያዝ፣ ሱማሌዎች እንዲከተሉ ብናደርግ ለመጭው ፕሮብሌማችን መፍቻ ይሆነናል ብዬ አስባለሁ::

ከዚህ በቀር ደግሞ የኤርትራ ፌዴሬሽን ሳይነካ መቆየቱ ሌላ ጥቅም አለው:: ከጥቂት ቀናቶች በኋላ ግርማዊነትዎ ታላቋ ብሪታንያን፣ ፈረንሣይን፣ ጀርመንንና ሌሎቹንም የአውሮፓ አገሮች በሰፊው መጐብኘት የሁለት ወር ፕሮግራም ታቅዷል:: ይህ የጃንሆይ ረዥም ጉዞ፣ ስለ ኢትዮጵያ ጠቅላላ ጉዳይ፣ በዓለም ጋዜጣና ራዲዮ እንዲነገር ትልቅ ምክንያት ይሆነናል:: በተለይ እንግሊዞችና ፈረንሣዮች በኤርትራ ጉዳይ አዋቂዎች ነን ስለሚሉ፣ አሁን አሥመራ ላይ የሚነፍሰው የፌዴሬሽን መፍረስ ወሬ፣ በንጉሡ ነገሥቱ የተዘጋጀ ነው ተብሎ የጠላት ፕሮፓጋንዳ ቢነዛብን፣ በዚህ ብዙ በታሰበበት የጃንሆይ ጉዞ ለኢትዮጵያ ዕድገት ብዙ እርዳታ እናገኛለን ብለን የምንጠብቀውን ሁሉ ሊያበላሽብን ይችላል:: ጃንሆይ እንደሚያውቁት ፕሮፓጋንዳ ቀድሞ ካጠቃ በኋላ፣ ለመከላከል የሚደረገው ጥረት የልብ አያደርስም:: ጃንሆይ ! ብዙ በመናገር የግርማዊነትዎን ጊዜ በመፍጀቴ ይቅርታ እየለመንኩ፣ በእኔ በኩል የቀረበውን ሀሳብ፣ በሶስት መልክ ከፍዬ አጠቃልላለሁ::

1ኛ/ ደጃዝማች ተድላ ያደረገው ዲስኩር፣ የኤርትራን ፌዴሬሽን አሁን ካለበት ሁኔታ ምንም የሚለውጠው ነገር አለመኖሩ እንዲታወቅ ያስፈልጋል:: ግርማዊነትዎ እንደሚያውቀው ፌዴሬሽን መልዕክት በሌለው ዲስኩር አይፈርስም::

2ኛ/ በአሁኑ ሰዓት ፌዴሬሽኑን ከማፍረስ ይልቅ ማቆየቱ ይጠቅማል ብዬ ባቀረብኩት ሀሳብ ውስጥ ያልተዘረዘሩ ብዙ ነገሮች ስላሉ፣ በልዩ ኮሚቴ ተጠንቶ ለጃንሆይ ውሳኔ ቢቀርብ ይሻላል ብዬ እመለከታለሁ::

3ኛ/ እኔ በማላውቀው ከፍተኛ የፖለቲካ ጉዳይ፣ ፌዴሬሽኑ በቶሎ መፍረስ አለበት ከተባለ፣ ለማፍረስ ሕጉንና ሥርዓቱን መከተል አስፈላጊ መሆኑን በብርቱ አሳስባለሁ:: ይኸውም፣ ሬፈራንደም ተደርጐ ሕዝቡ በድምፅ ብልጫ ይፍረስ ብሎ መወሰኑ፣ ታዛቢዎች ባሉበት ሲረጋገጥ ነው:: ይህንን ሥርዓት ባልተከተለ መንገድ ፌዴሬሽኑ ቢፈርስ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ኃያላን አገሮች፣ በተለይም ጠላቶቻችን እንደሚቃወሙንና ከባድ ችግር እንደሚያደርሱብን በትህትና እገልጻለሁ:: በመጨረሻም ለጃንሆይ ማመልከት የምፈልገው፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን ጉዳይ ቢፈርስም ቢቆይም፣ ጉዳዩ መከናወን ያለበት በኤርትራውያኖቹ እንጂ የጃንሆይ መንግሥት እጅ እንዳይገባበት መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

<u>ጃንሆይ፣</u>

እንተ የኤርትራን ጉዳይ የምታውቀው በዚያ በሙግቱ ዘመን የሆነውን ነው:: በታላላቆቹ መንግሥታቶች ዘንድ እና በዓለም ማህበር ጉባኤዎች ላይ ለብዙ ዓመታት የኛን አደራ ተቀብለህ፣ ብዙ መድከምህን፣ ብዙ መሥራትህን እኛም እውቀን ሕዝባችንም እንዲያውቀው ማድረጋችንን ታስታውሳለህ:: የተባበሩት

መንግሥታቶች እኛ ያልጠየቅነውን፤ የኤርትራም ሕዝብ ተጠይቆ ያልተናገረውን፣ ይህንን የፌዴሬሲዮን ነገር በግዴታ ከጫኑብን በኋላ፣ በኤርትራ ውስጥ የሆነውን ነገር ሁሉ በግድ አለማየትህን አሁን የምትናገረው ያስረዳል::

..... ከሁለት ዓመት ዠምሮ፣ የኤርትራ ሕዝባችንን በየከተማው ያለውን ብቻ ሳይሆን፣ በየገጠሩም እየተጓዝን ሕዝቡ የሚለውን ስናዳምጥና ስናነጋግር፣ ይኸ ፌዴራሲዮን የተባለ ነገር ምን ያህል ደንቃራ ሆኖበት የባዕድ መንፈስ ያሳደረበት መሆኑን ደህና አድርጎ ገልጠልናል:: የሚቆጨን፣ በዚህ ጉዞአችን አንተን ባለማስከተላችን ነው እንጂ፣ አንተው ራስህ ብታየው ኖሮ ይኸን ጊዜ ፍርዱን አስማምሮ ለማቅረብ የሚያህልህ አይኖርም ነበር:: ከዚህ ሌላ አንድ ሁልጊዜ ትዝ የሚለን ነገር አለ:: ስለ አገራችን አስተዳደር ጉዳይ አልፎ አልፎ ሀሳብህን ስንጠይቅ፣ ማናቸውም ነገር መደረግ ያለበት ከሕዝቡ መንፈስና ፍላጐት ጋራ ተስማሚ መሆኑ ሲታይ ነው፤ እያልክ የምትናገረው ዛሬ ትዝ አለን:: ዛሬ እኛ የኤርትራ ሕዝባችንን መንፈስና ብርቱ ፍላጐት እዚያው አገሩ ድረስ ሄደን አይተን፣ ይህንን ፌዴራሲዮን የተባለውን ሕግ ምን ያህል እንደጠላውና እንዳዘነበት፣ ከአቅሙም በላይ ግብርና ታክስ እንደተጫነበት፣ በዲስኩርም በአቤቱታም የገለጸልንን ተረድተን፣ ከዚህ ከተቸገረበት ወጥመድ እንዴት እንደምናላቅቀው ስናጠና፤ <u>ፌዴራሲዮኑ መነካት የለበትም:: እንዲያውም ለምን ጊዜውም መኖር አለበት</u> የሚል ሀሳብ በመናገርህ በጣም ተገርመናል:: ደግሞስ አንተ የስጋህበት ሌላው ነገር፣ የዓለም ታላላቅ መንግሥታቶችም ቢሆኑ፣ የተባበሩት መንግሥታቶችም ቢሆኑ፣ አንተ ስትነግረን እንደነበረው፣ ሕዝቡ <u>የሚፈልገውን ነገር በመሥራታችን ለምን ይቃወሙናል ? ጠላቶቻችንስ እኛን ለማጥቃት ምን መንገድ ይኖራቸዋል ?</u> ስለዚህ ይህን ሀሳብህን እንደገና ብታስብበት ሳይሻል የሚቀር አይመስለንም::

ስለ ሱማሌ የተናገርከው ልክ አይደለም አይባልም:: ቢሆንም ገና የዛሬ ስድስት ዓመት ምናልባት ሊረዳን ይችላል ለሚባል ነገር፣ ዛሬ የኤርትራ ሕዝባችን የወደቀበትን ችግር ችላ ማለት አይገባም:: ...... ስለ ተድላ ንግግር በረዥሙ ያስረዳኸው የተገባ ነው:: በፌዴራሲዮንም መንገድ እኔ መሪ ነኝ ብሎ ለመኖር መፈለጉ እርግጥ ነው:: ከአገር ፍቅር ስዎችም ጋር ተራርቆ ከሌሎች ጋር ሲሠራ ከቆየ በኋላ፣ በመጨረሻው ብቻውን ስለአስቀረው፣ አሁን ማጣፊያው ሲያጥርበት አቀድሞ ቦታው ለመመለስ ማሰቡ እውነት ነው:: ሆኖም አንተ ያልታየህ፣ ተድላ አንድ የጫረው እሳት አለ:: ፌዴራሲዮኑ ቢፈርስ ደስ ይለኛል፡ ያለውን ከዜህ ቀደም ተናግሮት አያውቅም:: አሥመራ ያሉት ታማኝ አገልጋይዎቻችን፣ ተድላ የስጠው ፍንጭ ሕዝቡን የሚቀሰቅስ መሆኑን አመልክተውናል:: እንግዴህ፣ ሕዝቡ አደባባይ ወጥቶ ፌዴራሲዮን አንፈልግም፣ ንጉሠ ነገሥታችን አንድ ነገር ያድርጉልን ብሎ ቢጠይቅ፣ ምን ማድረግ እንዳለብን ተዘጋጅቶ መጠበቅ የተገባ መሆኑን ሁላችሁም ታውቃላችሁ:: ይህንንም ስብሰባ ያደረግነው ለዚሁ ብለን ነው:: አሁን እዚህ ያላችሁት ሁሉ፣ እኛም የተናገርነውን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችንም በረዥሙ ያስረዳውን እንደሰማችሁት፤ የሚጠቅም ነው የምትሉትን፣ የሚጨመርም አለ ብላችሁ የምታስቡትን እንድትናገሩ ይሁን::

<u>ራስ ካሣ፣</u>

ይኸ የኤርትራ ነገር ሙሉ በሙሉ በአንድ ኢትዮጵያ፣ በአንድ ንጉሠ ነገሥት እንዲገዛ ሳይሆን፣ ለራሱ የተለየ መንግሥት እንዲሰጠው መደረጉ፣ ለሌላው ኢትዮጵያ ክፉ ጠንቅ አይሆንም ወይ ? ብዬ፣ ከሁለት ስት ዓመት በፊት እክሊሉን



ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ

« ....... የውጭ ጉዳዩን አክሊሉን በጣም አደራ የምለው፣ የኢትዮጵያ አንድ መሆን ከሁሉ በላይ ትላቅ ነገር መሆኑን ነው። ....... በኤርትራ ነገር የሆነው ሲገርመኝ፣ አሁን ደግሞ የመቅደሾም የሀርጌሣም ሱማሌዎች በኤርትራው ዓይነት መተዳደሪያ ፌዴሬሽን ወደ እኛ እንዲመጡ መድከም አለብን ብሎ አክሊሉ ሲናገር ሰማሁ። ...... ሱማሌዎች ወደ እኛ መምጣት ካመለከቱ፣ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ሆነው ነው እንጂ፣ መተዳደሪያቸው ግማሽ በግማሽ ሆኖ አደለም። ግማሽ በግማሽ የሆነ መተዳደሪያ ትላቋን ኢትዮጵያን ስለማይጠቅማት፣ እዚያው አለብት ይኑሩ ....... »

ራስ ካሣ ኃይሉ መስከረም 1954
(Phto AAU)

መጠየቁን እስታውሳለሁ:: በዚያን ጊዜ አክሊሉ የነገሩኝ የወደፊቱ ሁኔታ ተስፋ ያለው አድርጎ ነበር። ሕዝቡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአንድ ኢትዮጵያና በጃንሆይ መሬት ብቻ ለማደር ሕጉን ሊለውጠው ስለሚችል አያሳስብም ብሎኝ ነበር:: ዛሬ ግን የምሰማው በጣም የተለየ ሆነብኝ:: ይኸ የኤርትራ ማደሪያ ሕግ እንኳን መለወጥ እንዲያውም ቢቆይልን ይሻላል ሲባል ሰማሁ:: አክሊሉ በዚህ ብቻ አልቆመም:: ወደፊትም ሱማሌዎች ከመቅደሾም ከሀርጌሣም ወደ እኛ ሲመጡ፤ በዚህ በኤርትራው መተዳደሪያ ዓይነት እንድንቀበላቸው መድከም አለብን የሚል፣ አዲስ ነገር ከዚህ ቀደም ያልሰማሁት ሀሳብ ጨምሮበታል። እንግዲህ እንደ አክሊሉ አባባል ከሆነ፣ በዕድሜያችን የጥንቷ ኢትዮጵያን፣ በሰሜን፣ በደቡብ በማሀሉ እየተባለ በሶስት ዓይነት የመተዳደሪያ መንግሥት ተከፋፍላ ልናያት ነው:: እንደዚህ ከሚሆን <u>እግዚአብሔር በቸርነቱ አገራችንን ከዚህ መከፋፈል ይሰውራት ማለት ይገባል::</u>

...... አሁን የሩቁን ችግር ትተን እዚሁ እፊታችን ያለውን ጉዳይ እንነጋገርበት:: ስለዚሁ ስለ ኤርትራ ጉዳይ አክሊሉ ያስረዳው አንድ ትልቅ ነገር አለ:: በዓለም ማህበር ተፈርዶ፣ በጃንሆይ ማህተም ጸድቆ ለህማሴኖች መተዳደሪያ የተሰጠውን ሕግ ለማፍረስ ተጽፈው የተቀመጡ ሕጎች አሉ ብሏል:: ቀጥሎም ሲያስረዳ፣ እነዚህን ሕጎች ተከትለው፣ ይኸንን አንወደውም ብለው፣ ከዓለም ማህበር የተሰጣቸውን መተዳደሪያ ማፍረስ ያለባቸው ሀማሴኖቹ ራሳቸው ናቸው እንጂ፣ የጃንሆይ ስም መግባት የለበትም ብሏል:: በእውነቱ ይኸ ጉዳይ በጣም መታሰብ ያለበት ትልቅ ነገር ነው:: መቼም ፈረንጆች የማይሠሩት የለም:: ሕግ የሚቆመው ለማስተዳደሪያ፣ ለዳኝነት ለሥርዓት ማስከበሪያ ብቻ ሳይሆን፣ ለማፍረሻም የተለየ ሕግ ታስቦ መዘጋጀቱ ድንቅ ነው:: እንግዲህ ይኸ ከሆነ፣ አክሊሉ እንዳለው፣ ባለጉዳዮቹ የሆኑት ሀማሴኖቹ፣ በዓለም ማህበር ተፈርዶ የተሰጠ ን መተዳደሪያ እጅግ የሚጐዳን ስለሆነ፣ አፍርሰን ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ሆነናል ብለው በዳኛ እና በምስክሮች ፊት እስኪወስኑ ድረስ፤ ዛሬ በእኛ በኩል የሚዘጋጅም የሚሠራም ነገር የለም ማለት ነው::

...... በመጨረሻ የውጭ ጉዳዩን አክሊሉን በጣም አደራ የምለው፣ የኢትዮጵያ አንድ መሆን ከሁሉ በላይ ትላቅ ነገር መሆኑን ነው:: ጃንሆይ ከልጅነት ጀምሮ የሚደክሙት ይህን ከአባቶች የተወረሰውን የኢትዮጵያን አንድ መሆን ለመጠበቅና፣ ለትውልድ ለማስያዝ ነው:: .... በጠላት ተቆራርጠው የተወሰዱብን ግዛቶቻችን፣ በሰሜኑም ሆነ በደቡቡ ያሉት ሕዝቦቻችን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የሚገባቸው ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ሲሆኑ ነው እንጂ፣ መተዳደሪያቸው ግማሽ በግማሽ ሆኖ አይደለም:: መቸም የኤርትራ ጉዳይ አንድ ጊዜ ሆኗል:: በእምላክ ፈቃድ በጃንሆይ ድካም ወደፊት ይስተካከላል ብለን እናስባለን:: ስለ ሱማሌ የተባለው ግን፣ የኤርትራን ዓይነት መተዳደሪያ ይዘን እንምጣ ካሉ፣ የሚበጀው አለመቀበሉ ነው:: ጥንት በኢትዮጵያ ተገዝተው የኖሩ መሆናቸውን ካመኑበት፣ ሙሉ ኢትዮጵያ ሆነው ይምጡ:: አለበለዚያ ግማሽ ለግማሽ የሆነ መተዳደሪያ ትላቋን ኢትዮጵያ ስለማይጠቅማት እዚያው አሉበት ይኑሩ::

<u>ቢትወደድ መኩንን፣</u>

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በስፊው የተናገረው፣ መጀመሪያ የኤርትራ ፌዴሬሽን መፍረስ የሚችለው በሕጉ መሠረት ሕዝቡ በድምፅ ብልጫ ሲወስን መሆኑን፤ሁለተኛ ያለ ሕጉ ቢፈርስ በአገራችን የውጭ ፖለቲካ ላይ

የሚያስከትለውን ችግር ነው። በመሠረቱ ጃንሆይም ያሉት፣ የደጃዝማች ተድላን ዲስኩር ሕዝቡ ተከትሎ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስለት ለንጉሠ ነገሥቱ አቤት ቢል፣ ምን ማድረግ እንደሚገባ ተዘጋጅቶ መጠበቁ ይጠቅማል በማለት ነው እንጂ፣አግባብ በሌለውና ሕግ ባልተከተለ መንገድ እንዲፈርስ አይደለም። እኔ ካቶ አክሊሉ ሀሳብ ጋር የማልስማማቸው ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው የፌዴሬሽኑ መቆየት ይጠቅማል ያለው ነው። የኤርትራ ሕዝብ ፌዴሬሽኑ ይፍረስልኝ ብሎ ከጠየቀ፣ የለም ቢቆይ ይሻላል የሚል መልስ አይሰጠውም። ከሕዝቡ ጥያቄ ካልቀረበ ደግሞ ጃንሆይ ከሕጉ ውጭ እንዲሆን ስለማይፈልጉ፣ ፌዴሬሽኑየግዱታ መቆየት ይኖርበታል። ሁለተኛው ጉዳይ፣ ደጃች ተድላ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ጨርሶ አይፈልግም ብሎ የተናገረው ነው። ምናልባት ደጃዝማች ተድላም አቶ አክሊሉ እንደሰጠው አስተያየት የፌዴሬሽኑ መቆየት ለፖለቲካ ሊጠቅም ይችላል ብሎ አስቦ እንደሆነ፣ ቢታወቅ ጥሩ ነበር። በእኔ ግምት እስካሁን በታየው ደጃች ተድላ ከኢትዮጵያዊነት መንፈስ የሚርቅ አይደለም።

<u>ልዑል መኰንን፣</u>

ደጃዝማች ተድላ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ አይፈልግም ብሎ አቶ አክሊሉ ነግሮናል። ለነገሩ አቶ አክሊሉም ቢሆን የፌዴሬሽኑን መፍረስ አይደግፍም። ሁኔታው እንደዚህ ከሆነ፣ በደጃዝማች ተድላ ቦታ ያገሩ ተወላጆች ከሆኑት ለምሣሌ እንደ ፊታውራሪ አስፍሐ የመሳሰሉት ሰዎች፣ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ቢያደርጉ፤ የታላላቅ መንግሥታቶችና የተባበሩት መንግሥታት፣ አገራችን ላይ ምን ዓይነት ችግር ሊያደርሱ ይችላሉ ? ለዚህ ጥያቄ አቶ አክሊሉ ቢመልስልኝ ደስ ይለኛል።

<u>ጃንሆይ፣</u>

እክሊሉ ! መልስለት።

<u>አቶ አክሊሉ፣</u>

ጃንሆይ ከፈቀዱልኝ ከሁሉ በፊት ማስረዳት የምፈልገው፤ በኤርትራ ጉዳይ እኔ በተለይ የፌዴሬሽን አድናቂ አለመሆኔ እንዲታወቅልኝ ነው። ይህ ዓይነት አስተያየት ስለተሰጠኝ አዝናለሁ። በሙግቱ ዘመን የፌዴሬሽን ሀሳብ በቀረበ ጊዜ ይህን ለማስቀረት ምን ያህል እንደጣርኩ፣ ከስንት መንግሥታቶች ጋር ጠብ ላይ እንደደረስኩ፣ ጃንሆይ ስለሚያውቁት ዝርዝሩ አያስፈልግም። አሁንም ፌዴሬሽኑን አለመንካት ጠቃሚ ነው ብዬ የማምንበትን ሀሳብ ከነ ምክንያቶቹ ቀደም አድርጌ ስለተናገርኩ፤ እንደገና በመድገም የጃንሆይን ጊዜ አላጠፋም። አሁን ልዑል የሐረር መስፍን ለጠየቁኝ መልሱን አቀርባለሁ። የኤርትራ ፌዴሬሽን ሥርዓቱን ሳይከተል በአንዳንድ ሰዎች ዲስኩር እንዲፈርስ የተፈቀደ እንደሆነ፣ የተባበሩት መንግሥታትና ታላላቆቹ አገሮች በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሊያደርሱ ይችላሉ ብዬ ስናገር፡ እንደ ኮሪያ ጉዳይ መንግሥታቶችን አስተባብረው በጦር ይወጉናል ማለቴ አይደለም።የተባበሩት መንግሥት፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የሕዝቦችን መብት ጥሷል በማለት መጀመሪያ በሬዞሉሽን ያወግዙናል። ሁለተኛ ደግሞ ምናልባት በመላው ዓለም የኢኮኖሚ ጭቆና እንዲደረግብን ይወስን ይሆናል። ይኸ ከሆነ አገራችንን በጣም እንደሚጎዳት ጥያቄ የለውም። ያንኑ አገራችን የሚያመርተውን ቡና እና ቆዳ በመጠኑም የቅባት እህሎች ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እንከለከላለን።ከውጭ የምናስመጣቸውን ዕቃዎች ሁሉ ሌላው ቢቀር፣ እንደ መድኃኒቶች የመሳሰሉትንም የሚሸጥልን አናገኝም ይሆናል። ታላላቆቹ መንግሥታቶች ደግሞ በኤርትራ ውስጥ ለሚነሱት ተቃዋሚዎች መሣሪያ በማደል የሽፍቶች ጦርነት ያስከፍቱብናል። ነገር ግን ፌዴሬሽኑ የሚፈርሰው ሬፈረንደም

**ተዘጋጅቶ፡ የተባበሩት** መንግሥታት ታዛቢዎች ባሉበት ሕዝቡ በድምፅ ብልጫ **ፌደሬሽኑን** አለመፈለጉ ከተረጋገጠ፡ የጃንሆይ መንግሥት የዴሞክራሲን ሥርዓት **በትክክል** አክብሯል ተብሎ ይደነቃል እንጂ ጥቃት አይታሰብበትም:: አሁን ትልቁ **ጉዳይ**፣ ይህንን የዴሞክራሲ ሥርዓት ተከትሎ፣ የሕዝብ ድጋፍ ለመሰብሰብና ለማስፈጸም የሚችለው ሰው ማን ነው ? የሚለው ጥያቄ ነው:: ..... ደጃዝማች ተድላ በኤርትራ የፖለቲካ መሪ ሆኖ በአራቱ ኃያላን አገሮችና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታወቀ ሰው በመሆኑ፡ ለዚሁ ጉዳይ ተቀባይነት የሚኖረው እሱ ነበር:: እሱ ግን ይህንን እርምጃ አይወስድም ብዬ የተናገርኩትን አለውጥም::በዚህ ጉዳይ ቀደም ሲል ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተያየታቸውን ሲሰጡ፣ ደጃዝማች ተድላ ከኢትዮጵያዊነት መንፈስ የሚርቅ አይደለም ብለዋል:: እኔም ፌዴሬሽኑን ማጠንከር እንጂ ማፍረስ አይፈልግም ብዬ ስናገር፣ ኢትዮጵያዊነቱን ጥያቄ ውስጥ አለማስገባቴን በዚህ አጋጣሚ ክቡርነታቸው እንዲረዱት እፈልጋለሁ:: ...... ልዑል የሐረር መስፍን የመረጧቸው ፊታውራሪ አስፍሐ፣ እስከዛሬ ድረስ በፖለቲካው ሜዳ የኤርትራ ሕዝብ እንደራሴ ሆነው ተመርጠው አያውቁም:: በትግሉ ዘመን ለኤርትራና ለኢትዮጵያ አንድነት ከፍ ያሉ ሥራዎች የፈጸሙት፣ እኔ በምመራው ሚኒስቴር ውስጥ የክፍል ዋና ዲሬክተር ሆነው ነው:: ዛሬም የጃንሆይ ምክትል እንደራሴ በመሆናቸው፣ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ መሪ ሆነው ቢቀርቡ፣ በጃንሆይ የታዘዙ ናቸው በመባል ውጤቱ እንደምንመኘው አይሆንም:: በአሁኑ ሰዓት በኤርትራ ያሉት የታላላቆቹ መንግሥታት ቆንስሎች፣ ለየአገራቸው በሚያቀርቡት ራፖር የጃንሆይ እንደራሴና የምክትላቸው የአስፍሐ ዋና ሚሲዮን፣ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ስለሆነ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን እላሠራ ብለውታል እያሉ፣ በሰፊው የሚሰጡትን ትችት አላቆሙም:: ደጃዝማች ተድላም ከቆንስሎቹ ጋር ሲነጋገር፣ ይህንን ጥሩ አድርጎ ተጠቅሞበታል::

....... ስለ ኤርትራ ፌዴሬሽን በሥራ ላይ መዋል ኢትዮጵያ የተጠረጠረችው ገና ከመነሻው እንደነበረ ለማስታወስ እንዲፈቀድልኝ ጃንሆይን እለምናለሁ:: የዛሬ አራት ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፌዴሬሽኑ ለመጽደቅ ሲቀርብ፣ የደረሱብንን ችግሮች መርሣት አንችልም:: የኢትዮጵያ መንግሥት የፌዴሬሽኑን አስተዳደር ያከብራል የሚል ዕምነት ስለሌለን፣ፌዴሬሽኑ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለሚቆጣጠሩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ወኪሎች፣ አሥመራ ላይ ቢሮ ማቆም ያስፈልጋል፤ የሚል ሬዞሉሽን በማርቀቅ፣ ተንኮል ያጠመዱብን አገሮች ጥቂቶች አልነበሩም:: በዚያች አስቸጋሪ ሰዓት ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን፣ አቶ እበበ ረታ፣ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚእ እና እኔ ሆነን፣ በአራት መንታ የየመንግሥታቱን እንደራሴዎች ተከፋፍለን፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ገና ከዤኔቩ የመንግሥታት ማህበር ዘመን ጀምሮ ለኮሌክቲፍ ሴኪውሪቴና ለተባበሩት መንግሥታት ቻርተር እምነታቸውንና ታማኝነታቸውን ያስመሰከሩ መሆናቸው እየታወቀ፣ እንዴት በዚህ በፌዴራል አስተዳደር ጉዳይ ተቆጣጣሪ ይመደብባቸዋል ? በማለት፣ ጠንክረን በማስረዳታችን ጠላቶቻችን ያሰናዱልን ሬዞሉሽን ወድቆ ቀረ:: ይህንን ለማስታወስ የተገደድኩት፣ በዚህ በኤርትራ ጉዳይ ዛሬም አሰፍስፈው የሚጠባበቁን ጠላቶቻችን ብዙ ስለሆኑ፤ የንጉሠ ነገሥታችን ስም በዓለም ላይ ተከብሮ እንዲቆይ፣ የኢትዮጵያ ታሪክና ዝና እንዲጠበቅ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ለማሳሰብ ነው::

<u>ጸ.ት ወልደጊዮርጊስ፤</u>

ጃንሆይ እንደሚያውቁት ባለንበት የፖለቲካ ዓለም ውስጥ ትናንት የተሰጠው ቃል ለዛሬ የማይከበር፣ የዛሬው ለነገ መከበሩ የማይረጋገጥ ሆኖ እናየዋለን::

ልዑል ራስ ካሣ፤ ከስስት ዓመት በፊት ስለ ኤርትራ ፌዴሬሽን አቶ አክሊሉ የነገራቸውን ሲያስታውሱ፤ ዛሬ የቀረበው ሀሳብ ልዩነት ያለው ሆኖ ያገኙት፣ በዚህ ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ምክንያት ነው።

...... የዛሬ ሁለት ዓመት በዚሁ ጊዜ፣ የኤርትራን ሕገ መንግሥት ጃንሆይ ሲያጸድቁ፣ አብዛኛዎቻችን ስንናገር፣ የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ የተለየ አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ የተለየ ባንዲራ፣ ከኢትዮጵያ የተለየ የመጠሪያ ስም፣ እንፈልግም ብሎ በግዴታ የተጣለበትን ፌዴሬሽን የተባለ ሕግ ለማፍረስ ከስድስት ወር የበለጠ ጊዜ አይወስድበትም ብለን ነበር። ነገር ግን በዚህ በሁለት ዓመት ውስጥ ነገሩ እንደአሰብነው አልሄደም። ለዚህም ምክንያቶች አሉት። ለኤርትራ የአስተዳደሩን ኃላፊነት የተቀበሉት ሰዎች፣ የፌዴሬሽኑ ሥልጣን እየጣማቸው ስለሄደ፣ ሕዝቡን አነሳስተው ፌዴሬሽኑን ማፍረስ አልፈለጉም። ፌዴሬሽኑ በቶሎ እንዲፈርስ የፈለጉት ሰዎች ደግሞ፤ የሕዝብ ወኪሎች ባለመሆናቸው፣ ውስጥ ውስጡን ከመጉንጉን በስተቀር አደባባይ ወጥተው ሕዝቡን ማነሳሳት አልቻሉም።

...... የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርዎ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በአንዳንድ ምክንያት ፌዴሬሽኑ በጥድፊያ ቢፈርስ፣ በግርማዊነትዎ መንግሥት ላይ የሚያስከትለውን ችግር፣ ቀጥሎ ደግሞ ፌዴሬሽኑ መፍረስ አለበት ተብሎ ከተወሰነ፣ ለአፈራረሱ ያለውን ወግና ሥርዓት መከተል አስፈላጊ መሆኑን ዘርዝሮ አስረድቷል። <u>እኔም ይህን ሀሳብ መደገፍ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪም አስተያየት እንዳቀርብ የጃንሆይን ፈቃድ እጠይቃለሁ።</u> ይኸውም፤ ፌዴራሲዮኑ ነገ ቢፈርስ፣ የግርማዊነትዎ መንግሥት በአንድ ጊዜ የኤርትራን የውስጥ አስተዳደር ተረክቦ ለመሥራት፣ ምንም ዓይነት ዝግጅት ስለሌለ፣ ከባድ ችግር የሚፈጥር መሆኑን ነው።

...... ግርማዊነትዎ እንደሚያውቁት፣ ኤርትራ ለሀምሣ ዓመታት በጣልያን የኰሎኒ አገዛዝና ለአሥር ዓመታት በእንግሊዞች ይዞታ በመቆየቷ፣የተለያየ አስተዳደር ስትቀምስ የኖረች ነች። አሁን በመጨረሻውም፣ ስትጠቀምበት የቆየችው የሁለት ዓመት የፌዴራሲዮን አስተዳደር፣ ከውጪው ዓለም መንፈስ የተወረሰ ስለሆነ፣ አሠራሩ ከእኛ ጋር ሲተያይ የተለየ መልክ አለው። ይህንን ከእኛ ጋር የማይዛመድ የአስተዳደር ሲስተም በአንድ ጊዜ ተረክቦ፣ በግርማዊነትዎ መሪነት ከተመሠረተው አድሚኒስትራሲዮን ጋር ለማዋሃድና ለመምራት ብዙ የተወሳሰቡ ፕሬብሌሞች ስለሚገጥሙን እንቸገራለን። ስለዚህ ጊዜ ወስዶ ማጥናትና አስፈላጊውን ማደራጀት ግዴታ ስለሚሆን፣ የፌዴራሲዮኑ አስተዳደር እንዳለ መቆየቱ፣ በዓለም ላይ ስለሚያስከትለው የፖለቲካ ፕሮብሌም ብቻ ሳይሆን፤ ለዚህም ለውስጥ ችግራችን የሚረዳ መሆኑን በጥልቀት አጥንቼ አምኜበታለሁ።

....... ይህንን ሀሳብ ሳቀርብ እኔም እንደ አቶ አክሊሉ የፌዴሬሽን ደጋፊ ተብዬ እንደማልቆጠር ተስፋ አደርጋለሁ። አቶ አክሊሉ ከእኔ በፊት ሲናገር የፌዴራሲዮኑን መፍረስ እንደ ደጃች ተድላ ተቃዋሚ ነው ተብሎ በመገመቱ ምን ያህል እንዳዘነ ለጃንሆይ አመልክቷል። በዚህ ረገድ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርዎ ላይ የተወሰደው አስተያየት ቅር የሚያሰኝ መሆኑን እኔም መደበቅ አልፈልግም። ጃንሆይ ብዙ ጊዜ የመከሩንና አደራ ያሉን፤ ይህን በመሰለ ከፍተኛ ስብሰባ ላይ የግርማዊነትዎ ታማኝ አገልጋይ የሆነ ሁሉ ሀሳቡን ሳይሸሽግ ገልጦ ከተናገረ የጉባኤው ውጤት በቁም ነገር ይፈጸማል ብለው ነው። እኔም ይህንኑ የጃንሆይን መምሪያ ከሚከተሉት አንዱ ነኝ። .....አቶ አክሊሉ የፌዴራሲዮኑ አስተዳደር ሳይነካ

ቢቆይ ለግርማዊነትዎ መንግሥት ይጠቅማል ብሎ ያቀረባቸው ምክንያቶችና፡ ደጃች ተድላ ፌዴራሲዮኑን ይዞ ለመኖር የሚያደርገው ጥረት፡ እንደ ወልደማርያምና ገብረማርያም የመጠሪያ ስሞች ልዩነት የላቸውም ተብሎ መገመቱ ተገቢ አይደለም:: የሁለቱ ሰዎች የሀሳብ ልዩነት እጅግ የተራራቀ መሆኑን ለመረዳት ይህን ያህል አስቸጋሪ አልነበረም:: የሆነ ሆኖ ትልቁ ቁም ነገር ግርማዊነትዎ የሁላችንንም አስተያየት እንኳን ተናግረነው፣ ገና ስናስበው ምን መሆኑን አበጥረው ስለሚያውቁን፣ ያልጠበቅነው ግምት ይወድቅብናል ብለን እንስጋም::

...... እሁን በእኔ በኩል ለግርማዊነትዎ ውሳኔ የማቀርባቸው አራት ዋና ዋና ሀሳቦች አሉኝ::

1ኛ/ በአገር ውስጥና በውጭው ዓለም ያለው የፖለቲካ ሁኔታ፣ የሚያመች መሆኑ እስኪረጋገጥ፣ ፌዴራሲዮኑ ሳይነካ እንዲቀጥል፣

2ኛ/ በአገር ፍቅር ስሜታቸው ተገፋፍተው ፌዴራሲዮኑ እንዲፈርስ ለሚጥሩት ታላላቅ ኤርትራውያኖች፣ በኃያላኖቹ መንግሥታቶችና በዓለም በኩል የሚፈጠረውን ችግር በማስረዳት በትዕግሥት እንዲጠብቁ ማድረግ፣

3ኛ/ በኤርትራ የግርማዊነትዎ እንደራሴና ምክትል እንደራሴው ፌዴራሲዮኑ እንዲፈርስ የሚሠሩት ሁሉ፣ ብዙ የፖለቲካ ችግር ስለሚፈጥር፤ ወደፊት ከሚላክላቸው መምሪያ እንዳይወጡ ትዕዛዝ እንዲተላለፍላቸው፣ በተጨማሪም የኤርትራ ፌዴራሲዮን መፍረስ ጉዳይ፣ የሚከናወነው በኤርትራውያኖቹ ብቻ መሆኑን እንዲገነዘቡት መምሪያ እንዲደርሳቸው፣

4ኛ/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እንደተናገረው፣ የኤርትራ ሕዝብ በሬፈራንደም ፌዴራሲዮኑን ቢያፈርስ፣ አስተዳደሩን ለመረከብ ዱብዕዳ እንዳይሆንብን፤ ጥናቱ በከፍተኛ ምሥጢር ከአሁኑ እንዲጀምር አስፈላጊ መሆኑን አመለክታለሁ::

ጸሐፊ ትእዛዙና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከወትሮው ልማድ ትንሽ በጠነከረ አነጋገር በስፊው የገለጿቸውን ሀሳቦች፣ ንጉሠ ነገሥቱ ብዙም ሳይቆጡ በሙሉ ካዳመጡ በኋላ፣ በስብሰባው መጨረሻ ላይ የተናገሩት ቃልና የሰጡት ውሳኔ፣ የሚከተለው ነበር::

« ...... እያንዳንዳችሁ የምታስቡትን ገልጣችሁ በመናገራችሁ ማለፊያ አድርጋችኋል::

...... ራስ ካሣ የተናገርከው ትላቅ ነገር ነው:: ለኢትዮጵያ አንድ መሆን፣ በአንድ አስተዳደር እንዲሆን ማድረግ፣ ከልዥነት ዠምሮ ስንደክምበት የቆየውን ካንተ ሌላ የሚያውቅ ምስክር ስለሌለ፣ የተናገርከው ሁሉም ፍሬ ነገር ነው:: ስለ ኤርትራም ስለ ሱማሌም አንተ የተጨነቅክበት ጉዳይ እኛንም ምን ያህል እንዳስጨነቀን ታውቃለህ:: ጊዜ ተለዋዋጭ ስለሆነ፣ ነገ፣ ጊዜ የሚፈጥረውን እናውቀውም:: ለሁሉም ሁሉን የሚችል እምላክ ብርታቱን እየሰጠን የምንደክምበት ሁሉ፣ ለኢትዮጵያ ፍሬ እንዲሆን ተስፋ እናደርጋለን::



ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ፣ የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትር፣

*« ...... የኤርትራ ፌዴራሲዮን ቢፈርስ፣ በታላላቅ መንግሥታቶችና በዓለም ማህበር በግርማዊነትዎ መንግሥት ላይ የሚያስከትለውን ችግር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርዎ ዘርዝሮ አስረድቷል። ....... እኔም ይህን ሀሳብ መደገፍ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም የማሳስበው፤ ፌዴራሲዮኑ በጥድፊያ ቢፈርስ፣አስተዳደሩን ለመረከብ ስላልተዘጋጀን፣ ዱብ ዕዳ እንዳይሆንብን መጠንቀቅ አለብን ....... »*

*ወልደጊዮርጊስ መስከረም 1954*

...... ዛሬ ባደረግነው ስብሰባ ላይ የተገለጠው ሀሳብ ሁሉ ደስ አሰኝቶናል:: ደስ ብሎናል የምንለውም፤ ሁላችሁም የምታስቡትን ሳትሸሽጉ በመናገራችሁ፣ አንዳንድ የሚለቀም ፍሬ ነገር ስለአገኘንበት ነው:: ለዚህም እክሊሉ ዘርዝሮ በመናገሩ ብዙ ነገር ተገላልጦ ሊታወቅ ችሏል::

...... ወልደጊዮርጊስ በገለጥከልን ሀሳብ ውስጥ ጠቃሚ ነገር መኖሩን ተመልክተናል:: ሆኖም፣ የኤርትራ ፌዴራሲዮን የሚፈርሰው ከተባበሩት መንግሥታት ሕግ ጋር በሚስማማ አኳኋን እንዲሆን እክሊሉ የተናገረውን እኔም እደግፋለሁ ያልከው፣ ለእኛ የማናውቀው አዲስ ሀሳብ ሆኖ አላገኘነውም:: የኤርትራ ፌዴራሲዮን ሕግ ባልያዘና ሕዝብ ባልጠየቀው መንገድ እንዲፈርስ፣ እኛም የማንፈቅድ መሆናችንን መኩንን እንዳልካቸው ተናግሮታል:: አንተም ይኸንን እንዴት እንደሳትከው አልገባንም:: ከዚህ ሌላ ደግሞ የፌዴራሲዮኑ መፍረስ ጉዳይ፣ የሚታሰበውም የሚዘጋጀውም በኤርትራውያኖቹ ብቻ መሆን አለበት እያላችሁ፤ አንተም እክሊሉም የተናገራችሁት፣ ከምን የተነሳ እንደሆነ አልተረዳነውም:: በእኛ በኩል ለፌዴራሲዮኑ አፍራሾች እንዲሆኑ ከሌሎቹ ግዛቶቻችን ሰው እየመለመልን ወደ ኤርትራ እየሄዱ እንዲያስፈስፉ አለማድረጋችንን፣ ካንተ ከጽሕፈት ሚኒስትራችን የተሻለ የሚያውቅ የለም:: <u>እንደራሴያችንና ምክትሉም ቢሆኑ፣ ፌዴራሲዮኑን ለማፍረስ በብርቱ እንዲሠሩ ከእኛ ትእዛዝ አለመስጠቱን አንተ የምታውቀው ነው::</u> እነሱም ተድላን አላሠራም ብለው አስቸግረውታል እየተባለ በውጭ መንግሥታቶች የሚወራ ከሆነ፣ እክሊሉ ሀብተወልድ ይኸ ጉዳይ እንተን ስለሚመለከት፤ አሁን አዲስ በፈጠርከው አሠራርህ፣ ያንኑ እንዳልካቸውን እየወከልክ፣ በእንደራሴያችን ላይ የሚነገረው ሁሉ ፍሬ የሌለው መሆኑን ለየአምባሳደሮቹ ማስረዳት ነው:: ...... ፌዴራሲዮኑ ቀርቶ ሙሉ በሙሉ መዋሀድ እንዲሆን፣ ወደፊት በተድላ ቦታ አስፍሐ ወልደሚካኤል በሕዝብ የተመረጠ ባለመሆኑ አይችልም ብለህ እክሊሉ የተናገርከውን በጥሞና አዳምጠናል:: መቸም ፖለቲካ ተለዋዋጭ ነውና ነገ ጊዜው የሚፈጥረውን ማወቅ ስለማይቻል፣ ስለዚሁ ጉዳይ ወደፊት የሚሆነውን እናያለን:: አንተም እንድታየው ይሆናል ...... »

## የንጉሠ ነገሥቱ ውሳኔ

1. ኤርትራውያኖቹ፣ የፖለቲካዎቹም ሆኑ የፓርላማዎቹ፣ ከሕዝቡ ጋር ሆነው፣ አገራቸው በአስተዳደር ከኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን የሚጠቅማቸው መሆኑን አውቀው፣ ለእኛ እስኪያመለክቱን ድረስ፣ የፌዴራሲዮኑ ሥራ ሳይነካ እንዳለ እንዲቆይ ይሁን፣

2. ወልደጊዮርጊስ፣ ፌዴራሲዮኑ እንዲፈርስ ሕዝቡ በሚያመለክተን ጊዜ ተዘጋጅቶ ለመጠበቅ፣ የአስተዳደሩ ሁኔታ ይጠና ያልከው ማለፊያ ሀሳብ ስለሆነ፣ በአንተ ሰብሳቢነት ለጉዳዩ የሚሆኑት ሚኒስትሮች ገብተውበት የሚያስፈልገው እንዲሰናዳ ይሁን::

ደጃዝማች ተድላ በድንገት ተነስተው ያደረጉት የይስሙላ ዲስኩር ምክንያት ሆኖ፤ ስለ ኤርትራ ፌዴሬሽን መኖርና መጥፋት ጉዳይ በጃንሆይ ቢሮ በስፊው የተካሄደው ስብሰባ፣ በመጨረሻ ያስገኘው ውሣኔ በጊዜው ላይ ለተፈጠሩት ችግሮች መፍትሔ ሰጥቷል::



« ....... ሬፈራንደም ሳይደረግ፣ ዓለም የሚያምንበትን ሥርዓት ሳይከተል፣ የኤርትራ ፌዴሬሽን በአንዳንድ ሰዎች ዲስኩር እንዲፈርስ የተፈቀደ እንደሆነ የተባበሩት መንግሥታትና የኃያላን አገሮች ብዙ ጥቃት ሊያደርሱብን ይችላሉ ብዬ ስናገር፣ እንደ ኮሪያ ጉዳይ በጦር ይወጉናል ማለቴ አይደለም። ........ ነገር ግን አሰፍስፈው የሚጠባበቁን ጠላቶቻችን ሁሉ በፖለቲካ ሜዳና በኤኮኖሚ ጭቆና የሚያደርሱብን ጉዳት ቀላል አይደለም ብዬ እገምታለሁ ....... »

አክሊሉ ሀብተወልድ
መስከረም 12 ቀን 1954

« ...... የኤርትራ ሕዝብ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ቢመርጥ ለደስታዬ ወሰን አልሰጠውም ነበር ..... » ብሎ መናገር፣ የግልን ምኞት መግለጥ እንጂ፣ ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ሥርዓቱንና ሕጉን ተከትሎ ስሕዝብ ውሳኔ የቀረበ ጥያቄ አለመሆኑን፣ በዚህ በጃንሆይ ቢሮ በተደረገው ስብሰባ ደህና አድርጎ ሊብራራና ሊታወቅ ተችሏል:: እባ ጠቅል ኃይሌ፣ ኤርትራን ጠቅልሎ በአንዲት ኢትዮጵያ አስተዳደር ሥር ለማድረግ፣ የተድላ ባይሩ ዲስኩር የሚያፋጥነው መስሎ ታይቷቸው ነበር:: ነገር ግን ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ጣጣው እጅግ ብዙ መሆኑን ከአክሊሉ ሀብተወልድ የቀረበው ስፊ ማብራሪያ፣ ወልደጊዮርጊስም ይህንኑ በመደገፍ እያቀጣጠሉ የጨመሩት ሀሳብ፣ የጠቅል ምኞት ጉዞውን እንዲገታ እስደርጐታል:: ንጉሠ ነገሥቱ ጸሐፊ ትእዛዛቸውና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ያደረጉት ንግግር ሁሉ ብዙም ባይጥማቸው፣ ያቀረቡትን መሠረታዊ ሀሳብ እስመቀበል ችግር እንደሚሆንባቸው ስለተረዱት፣ በመጨረሻው <u>የኤርትራ ፌዴሬሽን ሳይነካ ይቆይ አሉ::</u>

ጃንሆይ ስብሰባውን ሲዘጉ፣ ለጸሐፊ ትእዛዝና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሰጡት መልስ፣ በቁጣና በቅሬታ መንፈስ የተደባለቀ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነው:: ከስብሰባው በፊት ስለ ተድላ ዲስኩር ጉዳይ፣ ለውጭ አገር እምባሳደሮች የተሰጠውን መግለጫ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ ለምን በቅድሚያ አላስፈቀደም ? እንደዚሁም እሱ ራሱ እምባሳደሮቹን ለምን አላነጋገረም ? በማለት ስለተናደዱ፣ ቁጣው በቶሎ እልበረደላቸውም ነበር:: እንደዚሁም በዚያን ሰሞን ኃይለኛ የሆኑባቸውን ጸሐፊ ትዕዛዛቸውን ቀስ በቀስ ከባለሟልነታቸው ለማግለል ያዘነበሉበት ጊዜ ስለሆነ፣ ይህ መንፈስ እንዲሰማቸው ለማድረግ፣ ከወልደጊዮርጊስ የቀረበውን አስተያየት ከአክሊሉ ጋር እየደረቡ በማቃለል ተችተውበታል:: ይሁን እንጂ በዚህ ስብሰባ ለጃንሆይ ብዙ ነገሮች እንደተገለጡላቸው ጥርጥር የለውም:: ዓስም የሚያምንበትን ሥርዓት ባልተከተለ መንገድ የኤርትራ ፌዴሬሽን ቢፈርስ፣ የተባበሩት መንግሥታትና ኃያላን አገሮች በኢትዮጵያ ላይ ከባድ ችግር ለማድረስ እንደሚችሉ ንጉሠ ነገሥቱ በትክክል የተረዱት በዚህ ስብሰባ ላይ ነው ማለት ይቻላል:: ከዚህ በፊት ግን የኤርትራ ፌዴሬሽን ፈርሶ እስተዳደሩ ወደ አዲስ አበባ ቢዛወር፣ አንዳንድ የዓለም ጋዜጦች ዜናውን በወቀሳ ከማቅረባቸው በስተቀር፣ ሌላ ከባድ ችግር የሚኖር መስሎ አይታያቸውም ነበር::

የኤርትራን ግዛት እየተዘዋወሩ በጐበኙ ጊዜ፣ ከሕዝቡ የሚጐርፍላቸው እጅግ የጋለ እቀባበል፣ ከባላባቶቹና ከሽማግሌዎቹ የሚደረግላቸው ያገር ፍቅር አንድነት ዲስኩር፣ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የሕዝቡ ድጋፍ ማረጋገጫው ነው ብለው እምነዋል:: ለምሳሌ በስብሰባው ማሀል ላቶ አክሊሉ በሰጡት በመጀመሪያው መልሳቸው ላይ፣ <u>ሕዝብ የሚፈልገውን ነገር በመሥራታችን የዓለም መንግሥታቶች ለምን ይቃወሙናል</u> ? ብለው የጠየቁት፣ በዚህ እምነት ተመርኩዘው ነበር:: አሁን ግን የኤርትራ ፌዴሬሽን በዓለም መንግሥታት ዘንድ ብዙ ጥያቄዎች የሚቀርቡበት መሆኑን ሲረዱት፣ ለአፈራረሱም ሕጉንና ሥርዓቱን መከተል ግዴታ እንደሆነ ሲያውቁት፣ ሚኒስትሮቻቸው ተጨንቀው ተጠበው ያቀረቡትን ሀሳብ በመቅለብ፣ ለውሳኔው መምሀሩና አስረጂው ራሳቸው ሆነው ቁጭ አሉ:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተፈጥሮ ብልህነትና በሰው የመጠቀም ችሎታ እጅግ የላቀ ስለሆነ፣ ...... <u>አንተ ያልከው፣ ቀደም ሲል እኛ ያሰብንበት ነው::</u> ...... <u>አንተም ያቀረብከው፣ የማናውቀው አዲስ ሀሳብ ሆኖ አላገኘነውም::</u> ...... <u>አንተም የደገፍከው፣ ቁም ነገሩ የት ላይ እንደሆነ አልታየንም::</u> ...... እያሉ ሞራልን

የሚከረኩም ትችት በመስጠት፣ የመጨረሻውን ውሳኔ ከራሳቸው የመነጨ ሀሳብ አድርገው አጸደቁት::

ወደፊት ታሪኩ ፈለጉን እየተከተለ እንደሚያስረዳው፣ ከዚህ ስብሰባ በኋላ የኤርትራ ፌዴሬሽን ግብዓተ መሬት እስከተፈጸመበት እስከ ህዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም ድረስ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከአፍራሾቹ የሚቀርብላቸውን ልዩ ልዩ ሀሳቦች፤ ሕጉ ይፈቅዳል ወይ ? ...... ነገሩስ በእርጋታ ተጠንቷል ወይ? እያሉ ከመጠየቅና ጉዳዩን ከማስታመም በስተቀር በግልጽ በርቱ ! ፍጠኑ ! ብለው በይፋ ሲገፉፉ አልታዩም::

# ብቸኛው ተድላ

ደጃዝማች ተድላ ባይሩ በመስከረም 11 ቀን 1954 ዓ.ም ዲስኩራቸው፣ ኤርትራና ኢትዮጵያ ከፌዴሬሽን ወደ ፍጹም መዋሀድ የሚሸጋገሩበትን ትልቅ ድልድይ ዘርግቻለሁ ብለው፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ከፍ ያለ አድናቆት እንደሚያገኙ እርግጠኛ ነበሩ:: ነገር ግን የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ባደረጉት ንግግር፣ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር አሁን ካለበት ሁኔታ የሚለውጥ መሠረታዊ ሀሳብ አላቀረቡም ተብሎ ስለተወሰነ፤ የጠበቁት አድናቆትና ምሥጋና ሊደርሳቸው አልቻለም:: ደጃዝማች ተድላ ስለአደረጉት ዲስኩር፣ መልስ እንዲላክላቸው፣ ጃንሆይ ለጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ለአቶ ገብረወልድ እንግዳወርቅ መምሪያ የሰጡት፣ ታላቁን ስብሰባቸውን እንደፈጸሙ ስለሆነ፣ በዚያን ሰዓት በነበራቸው መንፈስ የወረወሩት ሀሳብና የተጠቀሙባቸው ቃላቶች እጅግ የጠነከሩ መሆናቸው በግልጽ ይታያል::

ይድረስ ከደጃዝማች ተድላ ባይሩ፤ እንደምን ሰንብተሃል ? ከሚለው ከተለመደው ሰላምታ በኋላ፣ በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ላይ የተገለጸው የንጉሠ ነገሥቱ መልዕክት፤ « ..... ስለ ፌዴሬሽኑ ጉዳይ መልካም ንግግር ማድረጉ ተገቢ ነው ቢባልም፣ የሚታሰበው ሁሉ በመልካም ቃላቶች ብቻ ይፈጸማሉ ማለት አይቻልም:: እንተ የተናገርከውን በተግባር እንዲገለጥ ለማድረግ፣ በመዠመሪያ ብዙ የሚሠሩ ሥራዎች መኖራቸው መታወቅ ነበረበት ...... » የሚል ስለሆነ፣ ተድላ ባይሩ ባልጠበቁትና ባላሰቡት መንገድ የወደቀባቸውን ሞራል የሚነካ ትችት መቀበል አዳግቷቸው ነበር:: ይሁን እንጂ ንጉሣዊው መልዕክት በዚህ ብቻ አልቆመም:: « ..... የኤርትራ ሕዝባችንን እዚያው እየመጣን ስንጎበኘው፣ በእኛ ላይ ያሳደረውን ዕምነት ከትላቅ ፍቅር ጋር በሰፊው ገልጠልናል:: ይኸው የሚወደንና የምንወደው ሕዝባችን በልቡ ዘወትር የሚያስበውን፣ ደህና አድርገን ስለምናውቅ የሚመኘው የሚፈጸምለት በትዕግሥት መሆኑን እንዲረዳው ያስፈልጋል:: »

በዚህ መልዕክት ንጉሠ ነገሥቱ ተድላ ባይሩን የገለጹት፣ በሌላ አነጋገር ሕዝቡን ሳታደራጅ ብድግ ብለህ፣ ፌዴሬሽኑ ቢፈርስ የሚሰማህን ደስታ በመግለጥህ ብቻ፣ ቁም ነገር አለመሥራትህን ማወቅ አለብህ ብለው ነው:: ደጃዝማች በዚህ በተሰጣቸው መልስ እንደዚያ ሲያዝኑ ያያቸው ሰው፣ በገነተ ልዑል ስብሰባ ላይ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ በተድላ መተማመን አይቻልም እየተባለ፣ በእሳቸው ቦታ ሌላ ሰው ሲታጭ እንደነበረ ቢሰሙ ኖሮ፤ ብስጭቱ ከባድ ሕመም ላይ ሳይጥላቸው

አይተረጎም ነበር። የዚህ መልዕክት ግልባጭ ለንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ሲደርስ፣ የቋንቋይ ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ተድላ በቺፍ ኤግዜኩቲፍነት መቆየቱ፣ ጥቅም እንደሌለው የሚያመለክት ነው በማለት፤ ቢትወደድና ፊታውራሪ እጅግ ተደሰቱ።

የግርማዊነታቸው እንደራሴና ምክትሉ፣ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የሚሠሩት ሁሉ ብዙ የፖለቲካ ችግር ስለሚፈጥር፣ ወደፊት በዚህ ጉዳይ እንዳይገቡ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው ወልደጊዮርጊስ በስብሰባው ላይ ያቀረቡት ሀሳብ፣ በንጉሠ ነገሥቱ ከተሰጡት ውሳኔዎች መካከል ሳይመዘገብ ቀርቷል።አንዳርጋቸው መሣይና አስፍሐ ወልደሚካኤል ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ እንዲሠሩ ከዚህ ቀደም ትእዛዝ አለመስጠቱን ንጉሠ ነገሥቱ ተናገሩ እንጂ፣ ከጸሐፊ ትእዛዙ የቀረበው ሀሳብ ይፈጸም አላሉም፤ በማለት አቶ ገብረወልድ እንግዳ ወርቅ የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ማዘዣ አይተላለፍም ብለው አገዱ። ይህ ሁኔታ በጥልቀት ሲታይ፣ የጽሕፈት ሚኒስትሩ ሀሳብ አልተፈቀደም ብሎ የሚያግደው ዋና ዲሬክተሩ ከሆነ፤ የዘመኑ ሉቃስ መስከረም ከጠባ በኋላ፣ የአጅሬ የወልደጊዮርጊስ ሥልጣን ቀስ በቀስ እያዘቀዘቀ መሄዱን ያመለክታል ማለት ነው። እንደዚሁም ኤርትራን በሚመለከት ጉዳይ፣ ቢትወደድ አንዳርጋቸውና ፊታውራሪ አስፍሐ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስም ሆነ ተድላን ለማስቸገር የሚሠሩት ሁሉ፣ በስውር ጃንሆይን እያማከሩ ነው የሚባለውን ለማመን ያስችላል።

የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አንድ ዓመት ሙሉ ፌዴራሊስት ለመሆን ያደረጉት ሙከራ ባለመሳካቱ፣ ወደ ጥንቶቹ ወገኖቹ ወደ አንድነቶች ልመለስ ብለው፣ መስከረም 11 ቀን 1954 ዓ.ም ያደረጉት ዲስኩር፣ ያልጠበቁትን ልዩ ልዩ ችግሮች አደራርቦ አወረደባቸው።

-- ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከዲስኩር በፊት ሥራ መቅደም ነበረበት ብለው ሲገስጿቸው፣

-- የንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ዲስኩራቸው የፖለቲካ መልዕክት የሌለው፣ የምኞት ንግግር ነው ብሎ መግለጫ ሲያወጣባቸው፣

-- አንድነቶች ምን አስኬደህና ምን መልሶ አመጣህ ? እያሉ ሲራቀቁባቸው፣

-- በፓርላማው ፌዴሬሽን ለማፍረስ አስበዋል በመባል፣ የተቃዋሚው ክፍል ከሥልጣን እንዲወርዱ ሲዶልትባቸው፣

-- ቢትወደድ አንዳርጌና ፊታውራሪ አስፍሐ፤ ተድላ ከሥልጣን ካልወረደ አይሆንም በማለት በያለበት ሲገዘግዟቸው፤

አበይ ተድላ ይህን ሁሉ መዓት ብቻቸውን እንዴት አድርገው ይሸከሙት ? እንዴትስ አድርገው ይገላገሉት ? ...... ከነዚህ ፕሮብሌሞች ውስጥ በቀላሉ ለማሸነፍ የሚችሉት፣ እነ ኢብራሂም ሡልጣን በፓርላማው ውስጥ፣ በእሳቸው ላይ ሁከት ለመፍጠር ያደረጉትን ዝግጅት አስቀድሞ በማገድ ብቻ ነበር። ይኸውም፣ ሕገ መንግሥቱ የሚሰጣቸውን ሥልጣን በመጠቀም፣ ከወዳጃቸው ከፓርላማው ፕሬዚዳንት ከዓሊ ራዳይ ጋር ተስማምተው መስከረም 15 ቀን 1954 ዓ.ም ምክር ቤቱን ለሀያ ቀን ዘጉት። ይህ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 48 ንዑስ ክፍል 5 ላይ የተመለከተው፣ በምክር ቤቱ ውስጥ ከባድ ችግር የተፈጠረ እንደሆነ፣ ጉዳዩ

እስኪበርድ ፓርላማውን ለሀያ ቀን እንዲዘጋው፣ ለቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሥልጣን የሚሰጥ ነበር። ደጃዝማች ግን፣ መንግሥታቸው በሚፈጽመው ተግባር የምክር ቤቱ አባሎች እንስማማም ብለው ጥያቄዎች ለማቅረብና፣ ሰፋ ያለ ክርክር ለመክፈት በተሰናዱ ቁጥር፣ ከውዝግቡ ለመሸሽ ተሽቀዳድመው ፓርላማውን ለሀያ ቀን መዘጋት አዘውትረዋል። በዚህ አኳኋን ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 የሚሰጣቸውን ሥልጣን ለሆነ ላልሆነው መጠቀሙን ስለአበዙ፣ ይህ አድራጎታቸው አንድ ቀን የሥልጣናቸው ማክተሚያ ያደርግባቸው ይሆናል እያሉ፣ አንዳንድ ሰዎች ይሰጉ ነበር። ነገር ግን ተድላ ባይሩ ምክር ተቀባይ ባለመሆናቸው፣ ብቻቸውን የሚያስቡት ሁሉ ትክክል ነው ብለው እርምጃ በወሰዱ ቁጥር፣ ፕሮብሌሞቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተከመሩ ሲያጠቋቸው ኖሩ።

በመጋቢት ወር 1955 ዓ.ም ደጃች ተድላ በድንገት ብድግ ብለው፣ የየአውራጃ ገዥዎችን ከአንዱ ወደ አንዱ በማዘዋወር፣ ለሚያምኗቸው አስተዳዳሪዎች፣ የፌዴሬሽኑ ሕግ የሚሰጣችሁን መብት በመከተል በሙሉ ሥልጣን ሥሩበት፣ የሚል ትእዛዝ አስተላለፉ። ይህ ሁኔታ እንደገና ወደ ፌዴራሊስትነት ለማፈትለክ የታሰበ ሳይሆን አይቀርም የሚል ወሬ መሰራጨት ጀምሮ ነበር። ፊታውራሪ አስፍሐንም የጉዱ መሰሏቸው፣ ዘመዳቸውና ዋና የአንድነት ወገን የሆኑትን፣ አዝማች ባራኪ ሐብለእግዚእን፣ ከአካለ ጉዛይ አውራጃ ገዥነት አንስተው ምፅዋ ላኳቸው። የግርማዊነታቸው ምክትል እንደራሴ፣ የተድላን ጉዳይ የሚመለከቱበት ሰፋ ያለ ፕላን ስላላቸው፣ በዘመዳቸው ላይ በተወሰደው እርምጃ የተነኩ ወይም ያዘኑ መስለው መታየት አልፈለጉም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተድላ ባይሩ ብቸኝነትና ደካማነት እየባሰበት በመሄዱ፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ጽሕፈት ቤት፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሥልጣን መኖር አለመኖሩን ጨርሶ እንደረሳው ይታይ ነበር። በተለይም የጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ የሥልጣን ዕድሜ የጥቂት ቀናት ጉዳይ መሆኑን፣ የንጉሠ ነገሥቱ እማች እንዳርጋቸው መሣይ እርግጠኛ ሲሆኑ፣ መንግሥቲ ተድላንም አብሮ ለመሸኘት ዝግጅታቸውን ማፋጠን ጀመሩ።

መጋቢት 28 ቀን 1955 ዓ.ም የኤርትራን ፓርላማ መደበኛ ስብሰባ ሲከፍቱ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደራሴ ያደረጉት የዘውድ ዲስኩር፣ ከዚህ ቀደም ተሰምቶ የማይታወቅ፣ የፌዴሬሽኑን ሕግ የሚዳፈር፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉንም ሥራ የሚያንኳስስ ሆኖ ቀረበ።

እንዳርጋቸው መሣይ በኤርትራ የውስጥ አስተዳደር እየገባ አስቸግሯል እየተባለ የሚነገረው መሠረተ ቢስ ወሬ፣ ከየት እንደመነጨ፣ ፊት ለፊት ቢወጣ ምን ያህል ደስ እንደሚላቸው ካስገነዘቡ በኋላ፤ « በማናቸውም ረገድ ለእንደራሴው ጽሕፈት ቤት በኤርትራ ጉዳይ፣ የውስጥና የውጪ የሚባል ነገር አለመኖሩን እና፤ ወደፊትም እንዲኖር የማንፈቅድ መሆኑ መታወቅ አለበት » አሉ። ወዲያውም ከዚሁ ጋር አያይዘው « …….. ምንም እንኳን ኤርትራ የውስጥ አስተዳደር መብት እንዳላት ብናውቅም፣ በአሠራር ረገድ ጥሩ አስተዳዳሪና ጥሩ ሕብረት ከሌለ፣ ኢትዮጵያ በጠቅላላ፣ ኤርትራ በከፊል የሚጠቀሙበት ነገር አይኖርም። …… » ብለው፣ የጃንሆይ እንደራሴ ይህን እጅግ የናረ መግለጫ ሲሰጡ፣ ከቺፍ ኤግዜኩቲፉም በኩል ሆነ ከፓርላማው መልስ ለመስጠት የደፈረ አልነበረም።

እንግዲህ፣ ቢትወደድ አንዳርጌ እንደተናገሩት፣ በኤርትራ ጉዳይ የውስጥና የውጭ ሥልጣን የሚባል ነገር ከሌለ፤ የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ምን ሊያደርግ ይቀጥል ተባለ ? በዚህ መግለጫ ምክንያት፣ ከሰልሣዎቹ የፓርላማ አባሎች ውስጥ፣

**በተለይ የእስላም** ሊግ ወገኖች፡ በምክር ቤቱ ውስጥ ከፍ ያለ ሁከት ሊፈጥሩ **ይችላሉ ተብለው** ሲጠበቁ፥ የንጉሡ ነገሥቱ እንደራሴ ተድላ ባይሩን ለማጥቃት **ማዘጋጀታቸውን** እንደማፋለን በሚል ሀሳብ ጸጥ አሉ። ከዚህም አልፈው፣ የንጉሡ **ነገሥቱ** እንደራሴ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ከሥልጣን ለማስነሳት ከፍ ያለ ጥረት **ካደረጉ**፣ የምክር ቤቱ አባሎች ደግሞ ተድላን ሲያንቀባርርዙን የኖረውን፣ የፓርላማውን ፕሬዚዳንት ዓሊ ራዳይን እንሸራለን በማለት ውስጥ ውስጡን መነጋገር ጀመሩ።

የፓለቲካ ሥራ ብዙ ጊዜ ስብዓዊነት የሌለው፣ ወዳጅነትንና ታማኝነትን በጥቅም የሚለውጥ በመሆኑ፡ ተድላ ባይሩን ከሥልጣን ለማውረድ ሲባል ብዙ፣ የአንድነት ወገኖች፡ የኢትዮጵያ ጠላቶች ከሆኑት ከነ ኢብራሂም ሡልጣን ወገኖች ጋር መተባበርን መረጡ። ከአንድነት ወደ ፌዴራሊስትነት፣ ከፌዴራሊስትነት ወደ ፍጹም አንድነት፣ የተንቆራጠጡት ደጃዝማች ተድላ ባይሩ፣ ከሁለት ያጣ ጐመን እንደሚባለው በቺፍ ኤግዜኩቲፍነት የሥልጣን ዘመን፡ ከየትኛውም ወገን የጠበቀ መሠረት ሳይጨብጡ በብቸኝነት ብዙ ተሰቃዩ።

## ተድላ ከወልደጊዮርጊስ በኋላ

ሚያዝያ 25 ቀን 1955 ዓ.ም፣ (እንደ ኢትዮጵያ አቆ. ሚያዝያ 17 ቀን 1947 ዓ.ም) ከእኩለ ቀን በኋላ በስምንት ሰዓት ከሩብ፣ የአዲስ አበባ ራዲዮ « ታላቅ ሹመት » በሚል አርእስት፣ የወልደጊዮርጊስን ሽረት ሲያበስር፣ በደጃዝማች ተድላ ባይሩ ላይ የደረሰው ድንጋጤ መጠን አልነበረውም። እውነት መሆኑን ማመን ስለአቃታቸው፣ በኩርፊያ ሳያነጋግሯቸው የሰነበቱትን ፊታውራሪ እስፍሐን ስልክ ደውለው እስከ መጠየቅ ደረሱ። እስፍሐም እልፎ አልፎ ማሾፋን ስለሚያውቁበት « ..... ሹመቱ እውነት ነው። ቢታላቁ ወዳጃችን መሻር ቢትወደድ እንዳርጌና እኔ እጅግ ተከዝናል .... » አሏቸው። የዚህ አነጋገር ትክክለኛ ትርጉሙ፣ እንተ አዝነሃል እኛ ተደስተናል መሆኑን ተድላ ሊሳናቸው አይችልም። አሁንም ደጃዝማች እርግጠኛ መሆን አልቻሉም። ስሰሙ የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትር ይባሉ እንጂ፣ በኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥት ማንም ጠቅላይ ሚኒስትር የማይኖረውን ሥልጣን ይዘው፣ መላ ኢትዮጵያን ያንቀረቅቡ የነበሩት ሰው፣ በማይጠበቅ አኳኋን ወደ አሩሲ ይላካሉ ለማለት፣ እንኳንስ ተድላ ባይሩ፣ የቅርቦቹም የጃንሆይ ሚኒስትሮች፣ የሚያስቡት አልነበረም። ቀኑ እልፎ ምሽቱ ሲገባ፣ የእጅሬ የጸሐፊ ትእዛዝ ሽረት እየገነነ ስለተረጋገጠ፣ ከዚያች ዕለት ጀምሮ <u>ብቸኛው ተድላ፣ የኤርትራ መሪ ሆኖ ለመቆየት ያላቸው ዕድል የመነመነ መሆኑ ተሰማቸው።</u> ከእንግዲህ ወዲህ ቢትወደድ እንዳርጋቸው መሣይና ፊታውራሪ እስፍሐ ወልደሚካኤል፣ በብዙ ረገድ እንደሚያጠቋቸው ግልጽ ሆኖ ታያቸው። ወልደጊዮርጊስ ቢኖሩ፣ ምንም እንኳ በየዕለቱ እንዳርጌና እስፍሐ የሚጐነትጉኑባቸውን ተንኮል በቀጥታ ባይከላከሉላቸውም፣ ከቺፍ ኤግዜኩቲፍነቱ ሥልጣን እንዲወርዱ የሚዘጋጅላቸውን ወጥመድ እንደሚሰብሩላቸው ደጃዝማች ጽኑ እምነት ነበራቸው።

ተድላ ባይሩ የገነተ ልዑልን ፖለቲካ ለመረዳት ጥበቡ ስላልነበራቸው፣ በተለይ ከህዳር 1954 ዓ.ም ወዲህ፣ የወልደጊዮርጊስ ሥልጣን በአራቱም ማዕዘን ጠብመንጃ እንደተደገነበት፣ ጨርሶ አልታያቸውም። መጋቢት 28 ቀን 1955 ዓ.ም በቢትወደድ እንዳርጌ ዲስኩር ውስጥ፤ ...... <u>ለኤርትራ ጥሩ አስተዳዳሪ ከሌለ</u> ...... የሚል ቃል የተወረወረው፣ በወልዴ መውደቂያ ዋዜማ ላይ መሆኑን

አልገባቸውም። ልጅ ተድላ፣ በአንድ ጊዜ ከፍተኛውን የኤርትራን መሪነት ሥልጣን ካገኙበት ከሁለት ዓመት ተኩል ወዲህ፣ ከጃንሆይ ከፍተኛ ሚኒስትሮች መካከል፣ ከጸሐፊ ትእዛዝ በስተቀር ሌላ ወዳጅ ለማፍራት አልሞከሩም። አስፈላጊነቱንም አስበውበት አያውቁም። አጅሬ ወልደጊዮርጊስ ካለ፣ ሌላው ትርፍ ነው በማለት፣ ሌሎቹን ሚኒስትሮች ከቁም ነገር አልቆጠሩም።

በዚያ በትግሉ ዘመን ኒውዮርክ ለተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ሲሄዱ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉን ሲያከብሩ እንዴት ባለ ትህትና እንደነበረ፣ ብዙ ሰዎች ያስታውሳሉ። ሥልጣን በየረድፉ ሳይሆን በተለይ በድንገት ዱብ ብሎ ጣሪያውን ሲይዝ፣ የሰውን አቋምና ጠባይ ባልታሰበ ሁኔታ የሚለውጥ በሽታ በመሆኑ፣ ልጅ ተድላ የኤርትራ መሪ ከተባሉ በኋላ ብዙ ተለወጡ። ለሥራ ጉዳይ አዲስ አበባ በሚመጡ ጊዜ፣ ከጃንሆይና ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ለማየት እቢሮአቸው መሄድ ይኖርብኛል ወይ ? ብለው ፕሮቶኮል እስከ ማማከር ደርሰው ነበር። በመሠረቱ ከሆነ፣ አንድ የፖለቲካ መሪ የፕሮቶኮል ክብሩ የላቀ እንዲሆንለት ከሚያደርገው ጥረት ይልቅ፣ የሥልጣኑ ሕይወት እንዲረዝምለት ብዙ ታታሪና ንቁ መሆን ነበረበት። ተድላ ባይሩ ግን በራቸውን ዘግተው ብቻቸውን በመከፈሳቸው፣ በደጋፊዎች ቦታ ተቃዋሚዎች በርክተው፣ በወዳጆች ፋንታ ጠላቶች በዝተው፣ ሠላምና ደስታ ሳያገኙ ጊዜያቸውን ጨረሱ። የወልደጊዮርጊስ መውደቅ ለተድላ ባይሩ የሥልጣን ዕድሜ ማጠር አንዱ ምክንያት ነው።

## የመሰናበቻው ዋዜማ

ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው፣ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ጽሕፈት ቤትና አብዛኞዎቹ የምክር ቤት አባሎች፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉና የፓርላማው ፕሬዚዳንት ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ ስምምነት አድርገዋል። ይህም ሀሳብ በምን ዓይነት ዘዴ እንደሚፈጸም፣ በፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል የተዘጋጀውን ምሥጢራዊ ፕላን ሁሉም በደስታ ተቀብለውታል።

ሕገ መንግሥት አንቀጽ 75 በሚጠይቀው መሠረት፣ ፓርላማው ደጃዝማች ተድላን ከሥልጣን ለማውረድ በዚያን ሰዓት በቂ ምክንያት አልነበረውም። ወደፊትም ባጭር ጊዜ ውስጥ ለመሻር፣ ተፈላጊውን ምክንያት ፓርላማው ያገኛል ብሎ ማሰብ አይቻልም። በአንቀጽ 75 እንደተጠቀሰው፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ከባድ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ከሥልጣኑ አይወርድም። ስለዚህ፣ ፓርላማውና የእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ከተድላ መንግሥት ለመገላገል ያላቸው ዕድል፣ ተድላ ራሳቸው የተድላን ሥልጣን አውልቀው ሲጥሉ ብቻ ሆኖ ተገኘ። በሌላ አነጋገር ተድላ ዲሚሲዮን ካልሰጡ በስተቀር የተመረጡበትን የአራት ዓመት ጊዜ እስኪፈጽሙ ድረስ፣ ማንም ሊነካቸው አይችልም ማለት ነው። ያለው ዕድል ይህ ብቻ ከሆነ፣ ተድላ በገዛ ፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን እንዲለቁ መገፋፋት የሚቻለው በምን ዘዴ ነው ? ...... እስካሁን እንደታየው የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ዓሊ ራዳይ በሥልጣን ላይ ከሌሉ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ የመንግሥቱ መሪ ሆነው መቆየት አይችሉም። ፓርላማው ነገ ተነስቶ ፕሬዚዳንቱን በድምፅ ብልጫ ቢሽራቸው፣ ያን ጊዜ ተድላ ባይሩ በእልህ ተነስተው፣ ወዳጄ ወንድሜ ለምን ይነካብኛል ? በማለት ሕገ መንግሥቱን የሚፃረር ከባድ ስህተት ሊፈጽሙ

ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ፓርላማው አንቀጽ ሰባ አምስትን (75) በመጠቀም፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ከሥልጣን ያስናብታል። ይህ አንዱ ዘዴ ነው። ሁለተኛው ዘዴ ደግሞ፣ ፓርላማው ዓሊ ራዳይን ሲሽር፣ ግልፍተኛው ተድላ በድንገት ይነሱና፣ እኔም በራሴ ፈቃድ ሥልጣኔን ለቅቄያለሁ ብለው መግለጫ ሊያወጡ ይችላሉ። ይህ ሁለተኛው ፕላን በእርግጥ ውጤት የሚሰጥ ነው ተብሎ ስለታመነበት፣ አርባ አራት የምክር ቤት አባሎች፣ ሰኔ 17 ቀን 1955 ዓ.ም በሚደረገው የፓርላማ ጠቅላላ ስብሰባ ላይ ፕሬዚዳንታቸውን ለመሻር ሙሉ ስምምነት አደረጉ። ብዙ ጊዜ መማክርቶቹ ከፓርላማው አዳራሽ ውጭ የሚነጋገሩበትን ጉዳይ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ በመረጃ ስለሚደርሱበት፣ እሳቸውም በበኩላቸው በቅድሚያ የመከላከያ መሣሪያቸውን ያዘጋጃሉ።

ሰኔ 17 ቀን 1955 ዓ.ም ከጠዋቱ በአራት ሰዓት፣ ምክር ቤቱ የሚነጋገርበትን አጀንዳ ከመጀመሩ በፊት፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ እንደለመዱት ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመስማማት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 የሚሰጣቸውን መብት ጠቅሰው ፓርላማውን ለሀያ ቀን መዘጋታቸውን አስታወቁ። ሁለቱ ባለሥልጣኖች ተስማምተው ምክር ቤቱን ከዘጉ በኋላ፣ ደጃዝማች ተድላ በአውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ሲሳፈሩ፣ ሼህ ዓሊ ራዳይ ደግሞ የእርሻ ምርታቸውን ለመቆጣጠር ወደ አገራቸው ወደ ተሰነይ ሄዱ። ለነገሩ ፓርላማው የተዘጋው በዓሊ ራዳይ ላይ የተጠነሰሰውን እድማ ለማፍረስ ስለሆነ፣ በነዚህ በሀያ ቀናቶች ውስጥ ሁለቱም ባለሥልጣኖች ከመማክርቶቹ ጋር በመደራደር፣ መፍትሔውን በማግኘት ፋንታ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ወደ አዲስ አበባ፣ ፕሬዚዳንቱ ወደ ቆላ መንሸርሸር አልነበረባቸውም። አርባ አራቱ የምክር ቤቱ አባሎች ግን፣ በዚህ በሀያ ቀናት ውስጥ ፕሬዚዳንቱን ለመሻር ባቀዱት ሀሳብ ትብብራቸውን አጠነከሩ እንጂ፣ ተድላና ዓሊ እንዳሰቡት በመካከላቸው መለያየት ተፈጥሮ አልተዳከሙም።

ሰኔ 17 ቀን የተዘጋው ፓርላማ፣ በደንቡ መሠረት ከሀያ ቀን በኋላ የሚከፈተው ሐምሌ 6 ቀን ስለሆነ፣ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ በሶስት ሰዓት ተኩል ጀምሮ የምክር ቤቱ አባሎች ያስናዱትን <u>የሽረት ነጋሪት</u> ለማስተጋባት ወንበሮቻቸውን ይዘው ሲጠባበቁ፣ ተሻሪው ሼህ ዓሊ ራዳይ በተከበረው የሊቀመንበርነት ወንበራቸው ላይ አልተገኙም ነበር። ምክትሉ ፕሬዚዳንት ብላታ ደምሳስ ወልደሚካኤል በዓሊ ራዳይ ቦታ ሆነው፣ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 መሠረት ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ከፓርላማው ፕሬዚዳንት ጋር ተስማምተው ለሁለተኛ ጊዜ ምክር ቤቱን ለሀያ ቀናት መዝጋታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ካነበቡ በኋላ፣ በጥድፊያ የመሰብሰቢያውን አዳራሽ ለቅቀው ወጡ። በዚሁ ጊዜ የምክር ቤቱ አባሎች እጅግ ተናደው፣ እኛም የበኩላችንን እርምጃ እንወስዳለን አሉ። ይኸውም፣

1ኛ/ ከሰኔ 17 ቀን 1955 ዓ.ም ጀምሮ፣ የፓርላማውን ፕሬዚዳንት ሼህ ዓሊ ራዳይን በአርባ አራት (44) ድምፅ ብልጫ ሽረናቸዋል።

2ኛ/ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ከተሻረው ከቀድሞው ፕሬዚዳንት ጋር ተስማምተው ምክር ቤታችንን በድጋሚ ዘግቻለሁ የሚሉት፣ ሕገ ወጥ ሥራ ስለሆነ አንቀበለውም።

3ኛ/ በዛሬው ስብሰባችን አዲስ ፕሬዚዳንት መርጠን፣ ከሕዝብ የተቀበልነውን ኃላፊነት በተግባር ማዋል አለብን።

በማለት፣ የጽሑፍ መግለጫ ለማዘጋጀት ሲሞክሩ፣ በቺፍ ኤግዜኩቲፋ ትእዛዝ የፖሊስ ኃይል ተጠርቶ መማክርቶቹ ፓርላማውን ለቀው እንዲወጡ ተደረገ:: በዚሁ ዕለት የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ለንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ በላኩት ደብዳቤ፣ « ..... አንዳንድ የምክር ቤት አባሎች ከሰኔ 17 ቀን ጀምሮ የፓርላማውን ፕሬዚዳንት ሽረነዋል በማለት ሁከት ለመፍጠር ሲሞክሩ በመገኘታቸው በሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 መሠረት ፓርላማው ለሀያ ቀን ተዘግቷል:: ..... የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የሚመረጠውም የሚሻረውም በፓርላማው በሚደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ፣ ሥርዓቱን ተከትሎ ነው እንጂ፣ ከፓርላማው ውጪ በሚዘጋጅ አድማ አይደለም:: በሰኔ 17 ቀን እና ከዚያም ወዲህ እስከዛሬ ድረስ ፓርላማው በደፋ ተሰብስቦ የወሰደው እርምጃ ስለሌለ፣ የተከበሩ ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ አልተሻሩም:: ዛሬም በሥልጣን ላይ ናቸው ........ » ሲሉ አስታወቁ::

ቺፍ ኤግዜኩቲፋ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 የሰጣቸውን ሥልጣን እያከታተሉ መጠቀሙን በማብዛታቸው የደረሰባቸው ወቀሣ እጅግ ብዙ ነው:: ነገር ግን ሁለት ጊዜ ፓርላማውን አከታትለው የዘጉት፣ መማክርቶቹ ፕሬዚዳንታቸውን ለመሻር ስብሰባቸውን ከመጀመራቸው በፊት ስለሆነ፤ ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ ዛሬም በሥልጣን ላይ ናቸው ሲሉ የሰጡትን መግለጫ መቃወም አይቻልም:: ቢትወደድ አንዳርጋቸውና ፊታውራሪ አስፍሐ ግን ከአርባ በላይ የሆኑት የሕዝብ እንደራሴዎች፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፋን ሥልጣን አጠቃቀም በማውገዝ የሚወስዱትን እርምጃ የሚደግፉ በመሆናቸው፤ ይህንን የደጃዝማች ተድላን ማብራሪያ እንቀበላለን ማለት አልፈለጉም:: ከዚህ ሁሉ ችግር ለመላቀቅና ፓርላማው በቶሎ እንዲከፈት፣ የምክር ቤቱ አባሎች አቤቱታቸውን ለታላቁ መሪያቸው ለግርማዊ ጃንሆይ እንዲያቀርቡ በመገፋፋትና፣ የተጫረውም እሣት እንዳይጠፋ በማራገብ፣ የእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ያደረገው ጥረት የሚመኘውን ውጤት የሚሰጠው ሆነ:: አድመኞቹ አርባ አራቱ መማክርቶች፣ በመጀመሪያ እንደራሴው ዘንድ ቀርበው፤ የደረሰባቸውን እንዲያመለክቱ ከተደረገ በኋላ፣ ከመካከላቸው አሥር ሰዎች መርጠው (አምስት ክርስቲያኖችና አምስት እስላሞች) ወደ አዲስ አበባ በመላክ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ እንዲያቀርቡ አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቀቀ::

....... በግርማዊነትዎ ታላቅ ቸርነት የጸደቀልንን ሕገ መንግሥታችንን በመጣስ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፋ በየጊዜው በሚወስዱብን እርምጃዎች ከሕዝብ የተቀበልነውን ኃላፊነት ለመፈጸም አላስቻለንም:: ...... ከሰኔ 17 ቀን 1955 ዓ.ም ጀምሮ የመንግሥቱ መሪ (ደጃች ተድላ) ከሕጉ ውጭ በራሳቸው ሥልጣን ፓርላማችንን እያከታተሉ ለአርባ ቀናት ዘግተውታል:: ይህ አርባ ቀን ሲፈጸምም፣ ሌላ ሀያ ቀን በመጨመር ምክር ቤታችንን ለመዘጋት ማቀዳቸውን ደርሰንበታል:: ...... አሁን በመጨረሻው ፓርላማው የተዘጋበት ምክንያት፣ እኛ የምክር ቤቱ አባሎች የሾምነው ፕሬዚዳንታችን፣ የሰጠነውን እምነት አጉድሎ ስለአገኘነው፣ ከሥልጣኑ እንዲነሳ በአርባ አራት (44) የድምፅ ብልጫ ስለሻርነው፣ ይህን ማድረግ አትችሉም ተብለን ነው:: ግርማዊነትዎ እንደሚያውቁቀው፣ የመንግሥቱ መሪ በእኛ በሕዝብ ወኪሎች የተመረጡ ሲሆኑ፣ የተሰጣቸውን ከፍተኛ የአስተዳደር ኃላፊነት ትተው፣ በምክር ቤታችን የውስጥ ሥራ እየገቡ ለማስቸገር ሕጉ አይፈቅድላቸውም:: ..... ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 የሚለውን በትክክል ስንመለከተው፣ የመንግሥቱ መሪ፤ ምክር ቤቱን ለሀያ ቀን ለመዝጋት የሚችሉት፣ ከፓርላማው ፕሬዚዳንት ጋር ሲስማሙ ነው ይላል:: እኛ የምክር ቤቱ አባሎች ከሰኔ 17 ቀን ጀምሮ ፕሬዚዳንታችንን የሻርነው ስለሆነ፣ አሁን ሐምሌ 6 ቀን

**ለሁለተኛ ጊዜ ፓርላማውን** የዘጉት ከማን ጋር ተስማምተው ነው ? የሚል ጥያቄ **ሲቀርብ መልስ** የላቸውም፡፡ ይህ በመንግሥቱ መሪ የተወሰደው እርምጃ በቀጥታ **ሕገ መንግሥቱን** የጣሰ በመሆኑ፣ የንጉሠ ነገሥታችን መልካም ፈቃድ ሆኖ፣ **ፓርላማው** እንዲከፈትና እኛም ኃላፊነታችንን እንድንፈጽም በታላቅ ትህትና **እናመለክታለን**፡፡ ....... » የሚል ማመልከቻ ይዘው፣ የተመረጡት አሥሩ የፓርላማው መልዕክተኞች በአዲስ አበባ በእምሳለ ገነት ጽ/ቤት ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረቡ፡፡

ይዘ አቤቱታ ከመቅረቡ በፊት ንጉሠ ነገሥቱ ቺፍ ኤግዜኩቲፉንና የፓርላማውን ፕሬዚዳንት አዲስ አበባ አስጠርተው ሲጠይቋቸው፣ ምክር ቤቱ የተዘጋው በቂ በሆነ ምክንያትና ሕገ መንግሥቱ የሚያዘውን ተከትለው መፈጸማቸውን ዘርዝረው አስረድተዋል፡፡ ሆኖም በዚያን ሰዓት በነበረው ሁኔታ ጉዳዩ የሚታየው በፖለቲካው መስክ እንጂ፣ በአስተዳደርና በሕግ ረገድ ስላልሆነ፣ ከምክር ቤቱ ጠቅላላ አባሎች ሁለት ሶስተኛውን ያስተባበረውን ሀሳብ ከመደገፍ ይልቅ፣ የተድላንና የዓሊን ሮሮ ማዳመጡ፣ ለጃንሆይ የሚጠቅማቸው አልነበረም፡፡ ከአሥመራም በየዕለቱ የሚደርሳቸው ራፖር የተድላ ባይሩ ከሥልጣን መነሳት፣ ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ያስተዳደር ውህደት ምን ያህል በር ከፋች መሆኑን ስለሚደጋግምላቸው፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይህን አጋጣሚ ለመጠቀም አስፈላጊነቱን አመኑበት፡፡

በእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ቴክኒካል እርዳታ፣ ከኤርትራ ሕዝብ ወኪሎች የቀረበላቸውን አቤቱታ በእምሳለ ገነት ቢሮአቸው ካዳመጡ በኋላ፣ ጃንሆይ ውሳኔያቸውን ሲሰጡ፣ « ...... <u>እንኳን ተድላ እኛም ብንሆን ምክር ቤቱን በዚህ አኳኋን ለመዝጋት አንችልም፡፡ አሁንም ፓርላማው እንዲከፈት ስለአዘዝን፣ እናንተም ወደ ሥራችሁ ተመለሱ፡፡</u> ...... » አሏቸው፡፡ መማክርቶቹ ይህን ከፍተኛ ፍርድ ሲያገኙ ለደስታቸው ገደብ ስላልነበረው፣ ከቤተ መንግሥቱ ሲወጡ ያገኙትን ሰው ሁሉ፣ የሚያውቁትንም ሆነ የማያውቁትን እያነቁ ሲስሙ ይታዩ ነበር፡፡ ወዲያውም አሥመራ ስልክ ደውለው « ..... ጃንሆይ፣ የተድላንና የዓሊን ሀሳብ አልተቀበሉም፡፡ ምክር ቤቱ እንዲከፈት አዘዙ ...... » የሚል የምሥራች ቃል በማስተላለፋቸው፣ በወገኖቻቸው ዘንድ ትልቅ ፈንጠዝያ ሆነ፡፡ መልዕክታቸውን በዚህ አኳኋን ፈጽመው ከአዲስ አበባ ተነስተው አሥመራ አውሮፕላን ማረፊያ በደረሱ ጊዜ፣ በጦር ሜዳ ጀብዱ ሠርተው እንደተመለሱ ጀግኖች፣ የተደረገላቸው አቀባበልና የተገለጸላቸው የአድናቆት ስሜት እጅግ የጋለና የደመቀ ነበር፡፡ ቺፍ ኤግዜኩቲፉና የፓርላማው ፕሬዚዳንት ከአዲስ አበባ ወደ አሥመራ በአውሮፕላን የተጓዙት፣ አጋጣሚ ሆኖ ከእነዚሁ የምክር ቤቱ መልዕክተኞች ጋር ነበር፡፡ አንድ ሰዓት ተኩል በፈጀው የአየር ጉዞአቸው፣ አንድም ቃል ሳይለዋወጡ እንደተኳረፉ አሥመራ ሲደርሱ፣ ስገጥ መስሎ በአውሮፕላን ጣቢያ የተሰለፈው ሕዝብ፣ በተድላና በዓሊ ላይ የሚያሳየው የጥላቻ መንፈስ፣ ለፓርላማው መልዕክተኞች የሚገልጸው የጋለ ደስታ ያልተጠበቀና ያልታሰበ ቴያትር ሆነ፡፡

ሁለቱ የወንድማማች ፍቅር ያደረባቸው የሥራ ወዳጆች፣ ክቡር ደጃዝማች ተድላ ባይሩና የተከበሩ ሼህ ዓሊ መሐመድ ሙሣ ራዳይ፣ የሥልጣናቸው ዘመን ያከተመ መሆኑን ከልባቸው የተረዱት፣ በዚያች ዕለትና በዚያች ሰዓት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

# አልቻልኩም ያውላችሁ!

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ፓርላማው እንዲከፈት የሰጡትን ውሳኔ አክብሮ ከመፈጸም በስተቀር፣ ለደጃዝማች ተድላ ባይሩ ሌላ ምርጫ አልነበረም።

« ...... እንኳን ተድላ እኛም ብንሆን ምክር ቤቱን በዚህ አኳኋን ለመዝጋት አንችልም ...... » ሲሉ ጃንሆይ የተናገሩት ቃል ተድላን እጅግ ቢያሳዝንም፣ የተድላ ተቃዋሚዎች ሆነው በተሰለፉት በአርባ አራቱ መማክርቶች ዘንድ ተወዳጅነትንና አድናቆትን አስገኝቶላቸዋል። ይሁን እንጂ በኤርትራ ሕገ መንግሥት ውስጥ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ፓርላማውን ለመዝጋት ይችላሉ። እንዲሁም በቺፍ ኤግዜኩቲፉ የተዘጋውን ፓርላማ እንዲከፈት ያዛሉ። የሚል አንቀጽ ስለሌለ፣ « እንኳን ተድላ እኛም ብንሆን» የሚለው ቃል፣ መሠረቱ ምን እንደሆነ አይታወቅም። ነገር ግን የሚያስቡትን በሚፈልጉት አኳኋን የሚናገሩት አባ ጠቅል ስለሆኑ፣ ሁሉም እጅ ነስቶ ከመቀበል በስተቀር ሕጉን መመራመር የሚሞክር የለም። ጃንሆይ ይህን ንግግር ባደረጉበት ዕለት፣ በጥተ ልዑል ቤተመንግሥት ተገኝተው ያዳመጡት፣ አቶ ሠረቀ ብርሃን ገብረእግዚእ የፖስታ ቴሌፎን ቴሌግራፍ ምክትል ሚኒስትር፣ ወዲያውኑ የማስታወቂያ መሥሪያ ቤትን ለሚመሩት ላቶ መኰንን ሀብተወልድ ስልክ ደውለው፣ ለመማክርቶቹ የተነገረው ንጉሣዊው ቃል ብዙ ትችት የሚያስከትል መሆኑን አሳሰቡ። በዚህ መሠረት፣ « እንኳን ተድላ እኛም ብንሆን » የሚለው ሀረፍተ ነገር በአዲስ አበባ ራዲዮና ጋዜጦች ላይ ሳይገለጽ ቀረ።

በጃንሆይ ትዕዛዝ፣ ሐምሌ 26 ቀን 1955 ከእኩለ ቀን በፊት በአራት ሰዓት፣ ለአርባ ቀናት የተዘጋው ፓርላማ ሲከፈት፣ አርባ አራቱ መማክርቶች ዘመጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ የፕሬዚዳንታቸውን የዓሊ ራዳይን ሽረት ማጽደቅና ዘምትካቸው ኢድሪስ መሐመድ አዱምን በመሾም ነበር።

ሼህ ዓሊ መሐመድ ሙሳ ራዳይ ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ የተፈረደባቸው፣ በጨዋነታቸውና በቅንነታቸው እንከን የተገኘባቸው ሰው ሆነው አልነበረም። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የእሳቸው ትልቁ ኃጢያት፣ የቺፍ ኤግዜኩቲፉ ፍጹም ወዳጅ በመሆን፣ ፓርላማውን በማስከበር ፋንታ አስጠ ቅተውታል። ደጃዝማች ተድላንም በሥልጣን ለማንቀባረር ምቹ ሆነዋል በመባል ነው። እኚህ የቆላ ሰው ሐምሌ 26 ቀን ፓርላማው ከመከፈቱ በፊት፣ በገዛ ፈቃዱ የፕሬዚዳንትነቱን ሥልጣን ለቅቄያለሁ ብለው ቢያስታውቁም አርባ አራቱ መማክርቶች « ሲሰሟት ትታ ሲሰቧት » የተባለውን ምሳሌ በማፌዝ እየጠቀሱ፤ « እኛ ከሻርንህ ስንብቷል » በማለት ማመልከቻቸውን አልተቀበሏቸውም።

በዓሊ ራዳይ ምትክ የፓርላማው ፕሬዚዳንት ሆነው ስለተመረጡት ኢድሪስ መሐመድ አዱም፣ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል በሰጡኝ ማስታወሻ ውስጥ፣ እንዲህ የሚል ቃል ይገኝበታል። « ...... ኢድሪስ መሐመድ አዱም ጨርሶ ያልተማረና ዘላን የሆነ ሰው ነበር። ይህን መሀይማን በጊዜያዊነት ፕሬዚዳንት አድርገን ብንጠቀምበት ይሻላል ብዬ ሀሳቡን ስሰነዝር ተቃዋሚ አልጠፋም ነበር። እኔ ግን ሳልበገር ተወጣሁት ...... ይህን ሀሳብ ያመጣሁት በሁለት ምክንያቶች ነበር። ይኸውም፣

1ኛ/ ለፕሬዚዳንትነቱ ሥልጣን የሚታጨው፣ ያው ከቆላው ተወካዮች ውስጥ መሆን ስላለበት ፣ አንድ ባላባት ነኝ የሚል የታወቀ ሰው የተመረጠ እንደሆነ፣ ችግር ፈጥሮ ሊለያየን ይችላል የሚል ሥጋት አደረብኝ::

2ኛ/ ከዝቅተኛ ክፍል የመጣ፣ ሞያ የሌለውን እንደ ኢድሪስ የመሰለውን ሰው ያደረግን እንደሆነ፣ለጊዜው የምንፈልገውን ሁሉ እያዘዝን ለመፈጸም ይመቸናል ብዬ አሰብኩ::

በዚህ መሠረት መማክርቶቹ ተስማምተው የተባለውን ሰው መረጡ ...... »

እንግዲህ ቢትወደድ አስፍሐ እንደገለጡት የዓሊ ራዳይ ሽረት ብቻ ሳይሆን የኢድሪስ መሐመድ አዱም መመረጥም፣ በደጃዝማች ተድላ ላይ ችግር ለመፍጠር የታቀደ መሆኑን ያረጋግጣል:: በዚህ በሐምሌ 26 ቀን 1955 ዓ.ም በፓርላማው የተወሰደው እርምጃ ሁሉ እጅግ አድርጐ ስለአበሳጫቸው፣ ከዚሁ ዕለት ጀምሮ ደጃዝማች ተድላ የሚሠሩት ሁሉ በጥሞና ያልታሰበበትና ያልተመዘነ መሆኑን ያሣያል:: የፓርላማው ፕሬዚዳንት ሽረት በይፋ እንደተገለጸ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ በድንገት ተነስተው ዓሊ ራዳይ የካቢኔያቸው አባል እንዲሆኑ መሾማቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ላኩላቸው::

*« ....... የኤርትራ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሆነው ለኤርትራ ሕዝብ እንደፈጸሙት ታላቅ አገልግሎት፣ ለኤርትራም መንግሥት እንዲለግሱት፣ በእኔ ካቢኔ « የውስጥ ጉዳይ ሴክረተሪ » (ያገር ግዛት ሚኒስትር) ኃላፊነት ለስጥዎ ደስታዬ ከፍ ያለ ነው:: ከርሶም በኩል የሚያስደስት መልስ አገኛለሁ ብዬ እጠብቃለሁ:: >>*

ፊርማ ተድላ ባይሩ
የመንግሥት መሪ

ሳያስቡትና ሳይጠብቁት፣ በተለይም ሳያማክሯቸው፣ ውድ ወዳጃቸው የኤርትራ መንግሥት መሪ ላቀረቡላቸው ሹመት፣ ዓሊ ራዳይ የሰጡት መልስ የደጃዝማችን ሞራል የበለጠ አዳከመው::

*« ...... ከጥቂት ቀናት በፊት አዲስ አበባ ሄጄ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጋር እንድገናኝ ክብር ባገኘሁበት ዕለት፣ ...... የእኔ አገልግሎት በመንግሥታቸው በኩል የሚፈለግ መሆኑን ግርማዊነታቸው ስለነገሩኝ፣ አሁን ክቡርነትዎ ያቀረቡልኝን ኃላፊነት ልቀበለው አለመቻሌን እንድገልጽልዎ ይፍቀዱልኝ:: ....... »*

ፊርማ ዓሊ መሐመድ ሙሣ ራዳይ

ወዳጄ ወንድሜ እያሉ በደጉም ሆነ በክፉው ጊዜ የሚተማመኑባቸው ሼህ ዓሊ ራዳይ የላኩላቸው የእምቢታ ደብዳቤ ሲደርሳቸው፣ ከእንግዲህ ወዲህ የኤርትራ መንግሥት መሪ ሆኖ ለመቀጠል ጨርሶ እንደማይቻል፣ ደጃዝማች እርግጠኛ ሆኑ:: « ዓሊ ራዳይ እቢታው ከሌለ፣ ተድላ ባይሩ ብቻውን አይቀጥልም » እየተባለ በጀርባቸው ሲጐነጐንና ሲወራ የነበረው፣ እውነት እየሆነ መጣ:: የቆላ ሰዎች ወዳጅ ከሆኑ እስከ መጨረሻው አይከዱም ተብሎ የሚነገርላቸው፣ ለካስ

ከንቱ ውዳሴ ኖርዋል ? በማለት ደጃዝማች እጅግ ተገረሙ:: ከዓሊ ራዳይ ጋር አዲስ አበባ አብረው ከርመው፣ ወደ አሥመራ የተመለሱትም አብረው ሲሆን፣ ከጃንሆይ ጋር በተለይ ተገናኝተው ስለ ወደፊቱ ሥራ ጉዳይ መነጋገራቸውን እንዳችም ፍንጭ አልሰጧቸውም:: ይህንን ለማወቅ የቻሉት በዚህ በጻፉላቸው ደብዳቤ በመሆኑ፣ ተድላ ከወሰን ያለፈ ሀዘን ተሰማቸው::

ዓሊ ራዳይ ደግሞ በበኩላቸው ከሌሎች ወዳጆቻቸው ጋር ሲወያዩ፣ « ..... ለተድላ ስል ብዙ ታግያለሁ:: ወዳጅነቴን አላጐድልም ብዬ እስከ መጨረሻው መስዋዕትነትን ተቀብያለሁ:: ...... ከእንግዲህ ወዲህ ከተድላ ወዳጅ ጋር የማደርገው ጉዞ፣ የት እንደሚጥለኝ ስለማላውቀው፣ እኔም በመንገዴ እሱም በመንገዱ ተለያይተን ለየራሳችን ብናመራ ይሻላል ብዬ ወሰኛለሁ ...... » ይላሉ:: ተድላ ባይሩ የኤርትራ መሪ ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሠላሣ አራት ወራቶች ውስጥ፣ የዓሊ ራዳይን ወዳጅነት ለሥልጣናቸው ምን ያህል እንደተጠቀሙበት አስረጂ ናቸው ተብለው የተዘረዘሩት ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው::

1. በሕገ መንግሥት አንቀጽ 56 እንደተገለጸው ምክር ቤቱ የቺፍ ኤግዜኩቲፉን ሥራ ለመቆጣጠር የተሰጠውን መብት እንዳይጠ ቀምበት፣ ጃዝማች ተድላ በአንቀጽ 48 መሠረት እየተሸቀዳደሙ ፓርላማውን ለሀያ ቀናት በመዝጋት እንደልባቸው ሲከላከሉ የቆዩት የፕሬዚዳንቱን ድጋፍ ይዘው ነው::

2. በመጋቢት 1953 ዓ.ም ደጃዝማች ተድላ፣ የባለጋራቸውን የወልደአብ ወልደማርያምን ምርጫ፣ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 46 የሚያዘውን ሳይከተሉ በራሳቸው ሥልጣን የሰረዙት፣ የዓሊ ራዳይን ትብብር በመጠቀም ነው::

3. በታህሣሥ 1953 ዓ.ም ቺፍ ኤግዜኩቲፉ፣ እነ ደጃች አብርሃ ተስማን እስር ቤት ሲጨምሩ፣ በሕገ መንግሥት አንቀጽ 54 የተመለከተውን በመጣስ፣ የፓርላማውን አባል አዝማች ገብረኪዳን ተስማን አብረው በማስር፣ የፈጸሙት ሕገ ወጥ ተግባር እንዳያስጠይቃቸው ነገሩ ተሸፋፍኖ የተዘጋው በፕሬዚዳንት ዓሊ ራዳይ እርዳታ ነው::

ከዚህ በላይ እንደታየው፣ ዓሊ ራዳይ ይህን ሁሉ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ፡ መጨረሻው እኔን የሚያስወቅስና ከሥልጣኔም እንድወርድ የሚያስፈርድ ነው ከተባለ፣ ከወዳጅ ጋር አንድ ላይ መቆሙ ለሁለታችንም አይበጅም ብዬ መንገዱን ለውጫለሁ በማለታቸው፣ ደጃዝማች ተድላን ሊያሳዝን አይገባም ይባል ይሆናል:: ሆኖም በዓሊ ራዳይ በኩል፣ ይህ የተለወጠው መንገድ በየትኛው አቅጣጫ እንዳመራና ከማን ማህበር ውስጥ እንደገባ መመልከቱም አስፈላጊ ይሆናል::

የንጉሠ ነገሥቱን እንደራሴ ፊት ፊት እያስቀደሙ፣ እሳቸው ከጀርባ ሆነው ፖለቲካውን የሚነድፉትና የሚያጠነጥኑት ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ ገና ከእንግሊዞች ዘመን ጀምሮ ከቆለኛው ከዓሊ ራዳይ ጋር የዘረጉት ልዩ የወዳጅነት ግንኙነት ተቋርጦ አያውቅም:: የዓሊ ራዳይ ከሥልጣን መነሣት ተድላ ባይሩን ለማባረር ትልቅ ቁልፍ ነው በማለት ብዙ ጥረት ቢያደርጉም፡ አስፍሐ ወልደሚካኤል በቆላው ሕዝብ ዘንድ እጅግ የታወቁትን ሰው፣ ምንጊዜም ለኤርትራ ጉዳይ ጠቃሚነታቸውን ስለሚያምኑበት፣ በሽረት ወድቀው እንዲቀሩ አልፈለጉም:: ከዚህም በላይ፣ ዓሊ ራዳይን ፓርላማው የሚሸራቸው የአንድነት ወገኖች ባከማቹት

ድምፅ ኃይል ስለሆነ፣ ወሬው ለጠላት ምቹ ሆኖ የእስላሞችና የክርስቲያኖች ጠብ መጫሪያ እንዳይሆን አስፍሐ አንድ መፍትሔ ፈጥረው ተሳካላቸው:: ሼህ ዓሊ ሙሣ ራዳይ በሚኒስትር ዴታ ማዕረግ በኤርትራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ ዋና አማካሪ ሆነው ቢሾሙ፣ በምዕራባዊው ቆላ ሕዝብ ዘንድ የሚፈጥረውን ልዩ ስሜትና ደስታ ተንትነው በመግለጽ ፊታውራሪ አስፍሐ ለጃንሆይ ያቀረቡት ሀሳብ ወዲያው ተፈቀደላቸው:: ዓሊ ራዳይ ከፓርላማ ፕሬዚዳንትነታቸው የሚለቁት በክብር እንጂ በውርደት አለመሆኑን፣ ከዚህም በላይ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ራሳቸው አስበው የዘውድ እንደራሴያቸው ዋና አማካሪ እንዲሆኑ የሰጧቸውን ሹመት፣ የምዕራባዊው ቆላ ሕዝብ በትክክል እንዲያውቀው ለማድረግ አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቀቀ::

እንግዲህ በቆላው ሕዝብ ዘንድ ወገኑ ብዙ ለሆኑት ለሼህ ዓሊ ራዳይ ይህ ሁሉ ሲዘጋጅ፣ ለብቸኛው ተድላ ፍጻሜ ምን ታስቦለት ይሆን ? ተብሎ ሲጠየቅ፣ መልሱ ምንም የታሰበ ነገር የለም ከማለት አላለፈም:: ከተድላ የሚጠበቀው ትልቁ ቁም ነገር፣ ዓሊ ራዳይ ሲወጡ እኔም ሥልጣኑን አልቻልኩትም ብለው በቶሎ እንዲለቁ ብቻ ነው:: ለባለጋራዎቻቸው ምቹ የሆኑት ብቸኛው ተድላ፣ ከዓሊ ራዳይ እምቢታ በኋላ በ24 ሰዓቶች ውስጥ ስለራሳቸው አንድ ውሳኔ ማድረግ አለብኝ ብለው ተነሱ::

1. ፓርላማውን የዘጉበትን ምክንያት ለማስረዳት አዲስ አበባ በሄዱ ጊዜ፣ ጃንሆይ ጉዳዩን የተመለከቱበት አኳኋንና፣ በመጨረሻም ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ተቆጥተው የሰጡት ውሳኔ እጅግ ቅር አሰኝቷቸዋል::

2. ከእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ጋር በመተባበር፣ ባላጋራ ሆነው ያበሩባቸው አርባ አራቱ የምክር ቤት አባሎች፣ የሚፈልጉትን ሁሉ ለማድረግ መቻላቸው ከፍያለ ብስጭት አሳድሮባቸዋል::

3. ወዳጃቸው ዓሊ ራዳይ የካቢኔያቸው አባል ሆነው ችግሩን አብረው ለመግፋት የጠየቋቸውን አለመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ተድላን ሸሽተው ከነ አስፍሐ ጋር መግጠማቸው እጅግ አሳዝኗቸዋል::

እንግዲህ በዚህ ሁሉ ሁኔታ እንደምን እድርጌ ኃላፊነቴን መቀጠል እችላለሁ ? .... የቆምኩት ብቻዬን ስለሆነ፣ ሁሉም ተባብረው የበለጠ ችግር ላይ ከሚጥሉኝ፣ በገዛ ፈቃዴ ሥራዬን መልቀቅ ይሻለኛል ብለው መረጡ:: ይህንንም ውሳኔ በይፋ ለማስታወቅ፣ ሐምሌ 29 ቀን 1955 ዓ.ም በአሥመራ ከተማ በሚገኘው በሲኒማ ካፒቶል፣ የከተማው ሕዝብ እንዲሰበሰብላቸው ጠየቁ::

ዮሐንስ ተሰፋ እግዚእ፣ በዚያን ጊዜ የግርማዊነታቸው እንደራሴ የፕሬስ ሹም፣ ደጃዝማች ተድላ በሲኒማው አዳራሽ ባደረጉት የሕዝብ ስብሰባ ላይ ከተገኙ በኋላ፣ ቺፍ ኤግዜኩቲፉ ለመሰናበቻ ካደረጉት ንግግር ውስጥ፣ ባጭሩ ለቢትወደድ አንዳርጋቸው ያቀረበላቸው ራፖር የሚከተለው ነበር:: « ...... የኤርትራ መንግሥት መሪ ሆኜ የተቀበልኩትን ከባድ ኃላፊነት ለመፈጸም እንዳልችል፣ ብዙ ችግሮች ስለአጋጠሙኝና ወደፊትም ለመሥራት እንደማልችል ስለተረዳሁት፣ በዛሬው ቀን ሥልጣኔን በገዛ ፈቃዴ ለቅቄያለሁ:: ...... በእኔ ቦታ የሚሆነውን መምረጡ የፓርላማው ሥልጣን ነው:: ...... እኔ ግን ዕድሜ ለንጉሠ ነገሥታችን



ተድላ ባይሩ ለቺፍ ኤግዜኩቲፍነት፣ ዓሊ ራዳይ ለፓርለማው ፕሬዚዳንትነት፡ በመስከረም 1952 ዓ.ም ሁለቱም በአንድ ቀን ተመርጠው ነበር:: በሐምሌ 1955 ዓ.ም ሁለቱም በአንድነት ሥልጣን ለቀቁ::

ለቀዳግማዊ ኃይለሥላሴ ለሕይወቴ መግፊያ የሚሆን ሥራ አላጣም ...... » በሚል ቃል ንግግራቸውን ፈጽመዋል አሉ።

እንደሚታየው ቺፍ ኤግዜኩቲፉ የኤርትራ ሕዝብ እንዲያውቅላቸው የፈለጉት መንግሥታቸውን ለመምራት የሚያደርጉትን ጥረት ሁሉ የሚያደናቅፉና የሚተናኮሉ ጠላቶች በመብዛታቸው፣ ኃላፊነታቸውን ለመቀጠል አለመቻላቸውን ነው። ደጃዝማች ተድላ ችግራቸውን ለሕዝቡ ሲያስረዱ፣ ከሥልጣን እስከ መልቀቅ ያደረሳቸውን ትክክለኛ ምክንያት መተንተን አልፈለጉም። በሥራቸው ጣልቃ እየገቡ አስቸግረውኛል የሚሏቸውንም ሰዎች ስም አልጠቀሱም። <u>ዕድሜ ለጃንሆይ ለራሴ ሕይወት አልጨነቅም</u> በሚል ቃል የኤርትራን ሕዝብ በተሰናበቱ ማግሥት፣ ሻንጣቸውን ይዘው አዲስ አበባ ገቡ።

ለወደቀ ዛፍ ምሣር ይበዛዋል እንደሚባለው፣ ደጃዝማች ተድላ ሥልጣናቸውን በለቀቁ ማግሥት፣ የኤርትራ ጋዜጦች በየዓይነቱ የወቀሳ አጐዳ አወረዱባቸው። ..... ከሕዝቡ በአደራ የተሰጣቸውን ሥልጣን «<u>ኤርትራ አትችልም</u>» ሳትላቸው፣ « <u>አልችልሽም</u> » ብለው ጥለዋት ሄዱ። ...... <u>አገሪቱን ገረማት</u> ..... <u>ሕዝቡንም ገረመው</u> ..... የሚሉ ልዩ ልዩ ርዕሰ አንቀጾች በየጋዜጦቹ አምድ ላይ ተቀጣጠሉ። ከዚህም ጋር አያይዘው ስለወደፊቱ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አመራረጥ ጉዳይ፤ የሕዝቡን ስሜት ተርጉመን ነው በማለት፣ ጋዜጦቹ የገለጿቸው አስተያየቶች፣ ቀድሞውንም ቢሆን ደጃች ተድላ ያልተወደዱ ነበሩ ለማለት የሚቃጡ ናቸው። « ..... <u>በተድላ ቦታ የሚመረጠው ሰው፣ ከአዋቂነቱ በላይ ኢትዮጵያዊነቱ የተመሰከረለት፤ አንተ የጴጥሮስ አንተ የጳውሎስ ብሎ አድሎ የማይሠራ፤ ትህትናና ትዕግሥት እንጂ፣ ዕብሪትና ኩራት የሌለው መሆን አለበት</u> ...... » የሚሉ ቃላቶች ተሰንዝረዋል።

ደጃዝማች ተድላ « አልቻልኩም ያውላችሁ ! » ብለው ሥልጣናቸውን ለቅቀው ሲወጡ፣ ይህን ያህል ወቀሳና ትችት ይደርስብኛል ብለው አልጠበቁም ነበር። ይልቁንም በዴሞክራሲ ሥርዓት፣ እኔ አልቻልኩምና እናንተ ሞክሩት ማለታቸው፣ ለታሪካቸው አንድ ዓይነት ግምት እንደሚያስጣቸው ሳይመኙ አልቀሩም። ከዚህ ዓለም ችግር ጋር ለመቋቋም፤ <u>ዳኛ ሲገኝ ተናገር፤ ውሃ ሲጐድል ተሻገር፤</u> የሚባለውን ለመጠቀም፤ ደጃዝማች ተድላ ባይሩ በማናቸውም መልክ አልተመቻቸውም።

## ወራሽ ማን ነው?

በመስከረም 1952 ዓ.ም ተድላ ባይሩ ለኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍነት፣ ከአብርሃ ተሰማ ጋር ተወዳድረው ባሸነፉ ጊዜ፤ ዓምደሚካኤል ደሳለኝ « ... ጃንሆይ ! ድሉ አሁንም የርስዎ ነው። የአንድነቶች መሪ ተመረጠ ...» በሚል ቃል ዜናውን እንደአበሰሩት ሁሉ፤ የሐምሌውን 1955 ዓ.ም ታሪክ ደግሞ፣ ቢትወደድ አንዳርጋቸው ለንጉሠ ነገሥቱ ሲገልጹ፣ « .... ያሰብነው ሁሉ በደህና እንዲፈጸምልን የጃንሆይ አምላክ ረድቶናል። ደጃዝማች ተድላ በገዛ ራሱ ሥልጣኑን ለቀቀ ...... » ብለዋል።

እንግዲህ፣ በ1952 ዓ.ም የአቶ ተድላ ባይሩ ለኤርትራ መሪነት መመረጥ ጠቃሚነቱ ታምኖበት እንደተደከመበት ሁሉ፤ በ1955 ዓ.ም ደግሞ የደጃዝማች

ከሥልጣን መውረድ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ምን ያህል ጥረት እንደተደረገበት ከሥልጣን ለማስለቀቅ፣ እነ መገንዘብ ይቻላል:: ቺፍ ኤግዜኩቲፉን ገፋፍቶ ከሥልጣን ለማስለቀቅ፣ እነ ቢትወደድ እስከዚህ ድረስ የጃንሆይን አምላክ ሲማጸኑ ከስነበቱ፣ ሰውየው የሚቀረኝን የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመን ከመፈጸም የሚያግደኝ የለም ብለው፣ በሥራቸው ላይ ቢቆዩ ኖሮ፣ ብዙ ችግር ሊፈጥሩ ይችሉ ኖርዋል ወይ ? ያሰኛል:: እንደ ፊታውራሪ ከመሠረቱ ሲታይ ተድላ ባይሩ ጨርሶ አስጊ ሰው አልነበሩም:: እንደ ፊታውራሪ አስፍሐ በፖለቲካው ጥበብ የተካኑ ቢሆኑ ኖሮ፣ መጀመሪያ በምክር ቤቱና በመንግሥታቸው መካከል የተፈጠረው ጠብ፣ እስከዚህ ድረስ መካረር አልነበረበትም:: ሁለተኛ/ በብስጭት ሥልጣናቸውን አውልቀው ከመጣል ይልቅ፣ በሚቀራቸው የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመን ውስጥ፣ መንገዳቸውን ለውጠው ከአርባ አራቱ መማክርቶች ጋር አዲስ የመግባባት በር በመክፈት፣ የባለጋራዎቻቸውን ቅስም መስበር ይችሉ ነበር:: ነገር ግን፣ አቦይ ተድላ ግልፍተኛ እና ብቸኛ በመሆናቸው፣ ስለወደፊቱ የፖለቲካ ሕይወታቸው አርቀው በጥልቅ ሳይመረምሩ፣ በችኮላ ሥልጣናቸውን « ያውላችሁ » ብለው ፈረጠጡ::

የንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ከጫንቃቸው ላይ እያንዣበበ፣ ፊታውራሪ አስፍሐ የደከሙበት ፕላን በተግባር ላይ ውሎ ተፈላጊው ውጤት ከተገኘ በኋላ፣ የእንደራሴው ጽሕፈት ወራሹ ማነው ? የሚለው ጥያቄ ጋራውን አህሎ ብቅ አለ:: የእንደራሴው ጽሕፈት ቤትና አርባ አራቱ መማክርቶች፣ በሐምሌው ክረምት ተድላን ለመጣል ያንን ሁሉ ጥረት ሲያደርጉ፣ ወራሹ ማን እንደሚሆን ተነጋግረው ያዘጋጁት እጩ አልነበረም::

ከማህበረ ፍቅረ ሀገር አባሎች መካከል፣ በተለይ የአንድነት አጥባቂ ወገኖች፣ በመላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም መሪነት ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤልን እጩ ሲያደርጉ፣ ሞደሬቶቹ ደግሞ የተድላ ካቢኔ የኤኮኖሚ ሴክረተሪ የሆኑትን ፊታውራሪ ሐረጐት አባይን ጠየቁ:: የእስላም ሊግ ወገኖች ለመንግሥቱ መሪነት ከማህበረ ፍቅረ የፓርላማውን ፕሬዚዳንትነት ካገኙ በኋላ፣ ለመንግሥቱ መሪነት ከማህበረ ፍቅረ ሀገር የሚቀርበውን ተወዳዳሪ የምንደግፈው እንደ ግለሰቡ አቋምና ሁኔታ አይተን ነው አሉ::

ፊታውራሪ አስፍሐ በዚህ ሁሉ ማህል ከምኑም ውስጥ እንደሌሉ ለማስመሰል፣ የማህበረ ፍቅረ ሀገር ፕሬዚዳንት የሆኑት ደጃዝማች በየነ ባራኪ ቺፍ ኤግዜኩቲፍነቱ ይገባቸዋል በማለት፣ ቢትወደድ እንዳርጌን አሳምነው፣ ማስታወሻ ለጃንሆይ እንዲቀርብ አስደረጉ:: ንጉሠ ነገሥቱም ገና ቀደም ሲል ለተድላ ወራሽ አስፍሐን አዘጋጅተው ስለነበረ፣ ደጃች በየነ እንዲሆኑ ከእንደራሴያቸው ለቀረበው ሀሳብ፣ ምንም መልስ ሳይሰጡ የነሐሴ ወር የፍልሰታው ጾም ደርሶ ወደ ድሬደዋ ሄዱ::

አስፍሐ ወልደሚካኤልን ለማስመረጥ የነ መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ጥረት እያየለ መጣ:: ከአንድነቶችም አልፎ ከእስላም ሊግ ወገኖችም፣ ደጋፊዎች መጠ ራቀም ጀመሩ:: በተለይም ከአሥራ አምስት እስከ ሀያ የሚደርሱት የዓሊ ራዳይ ተከታዮች ለአስፍሐ ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን በይፋ አስታወቁ:: በዚህ ጊዜ የግርማዊነታቸው እንደራሴ፣ የምርጫው ውድድርና የእጩዎቹ ጉዳይ ከቁጥጥራቸው ውጪ እየሆነ ሲመጣ፣ ወደ ድሬዳዋ ቤተ መንግሥት ለጃንሆይ አስቸኳይ የሆነ ልዩ መልዕክት ላኩ::

« ...... እነ መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ከእኔ ጋር ሳይመካከሩ፣ ፊታውራሪ አስፍሐን ለቺፍ ኤግዜኩቲፍነት ለማስመረጥ ልዩ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው:: እኔ እንደማውቀው ፊታውራሪ አስፍሐ ለቦታው ልወዳደር ብሎ አላመለከተም:: ለመወዳደር ቢመኝ እንኳን የግርማዊነትዎ ምክትል እንደራሴ በመሆኑ፣ ለኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍነት ለመቅረብ ከሕጉና ከሥርዓቱ ውጭ ሆኖ ይገመታል ብዬ አስባለሁ:: በተጨማሪም የፊታውራሪ ሐረጎት አባይ ተወዳዳሪነት አንድነቶችን ሊከፋፍል ይችላል ብዬ ስግቻለሁ:: ስለዚህ፣ ቀደም ብዬ ለጃንሆይ እንዳመለከትኩት፣ <u>ያገር ፍቅር አንድነት መሪ በመሆን እጅግ የተከበሩት ደጃዝማች በየን ባራኪ</u> እጩ ሆነው እንዲቀርቡ ብናደርግ ከብዙ የተወሳሰበ ችግር ያድነናል:: ጊዜው በጣም ስለአጠረ፣ የግርማዊነትዎን መሪ ትዕዛዝ በትጋት እጠብቃለሁ..... »

ቢትወደድ አንዳርጌ፣ ከጃንሆይ የሚጠብቁት መልስ ውሎ ሳያድር በፍጥነት ደረሳቸው::

« ...... በእኛ በኩል ለኤርትራ አስተዳዳሪነት <u>አስፍሐ እንዲሆን መልካም ፈቃዳችን ብቻ ሳይሆን አጥብቀን የምንፈልገው ነው::</u> ሕጉ ላይፈቅድ ይችላል ብለህ ለጠቀስከው ነገር፣ ጉዳዩን ቀደም አድርገን ያሰብንበት በመሆኑ፣ አክሊሉ ሀብተወልድን አነጋግረነው፣ በሕገ መንግሥቱ መሠረት የሚመረጠው የኤርትራ አስተዳዳሪ በግዴታ ከፓርላማው አባሎች ውስጥ መሆን የለበትም ብሎናል:: አስፍሐ ምክትል እንደራሴያችን መሆኑ፣ ኃላፊነትን ለመቀበል የበለጠ የሚረዳው እንጂ የሚቀንስበት እንደማይሆን የታወቀ ነው:: ከዚህ ውጪ ሌላ ችግር አለ ካልክ፣ የአስፍሐ ነገር በእኛ በኩል የተቆረጠ ስለሆነ፣ እዚያው ጠንክረህ እንደሚሆን ማስተካከልና ማስፈጸም ነው:: <u>ለበየን ባራኪ አገልግሎቱ ትላቅ ስለሆነ፣ ከዚህ ቀደም አስፍሐ እንዳመለከተን ራስ ተብሎ የራስ ወርቅ እንዲያስር በቅርቡ እንፈቅድለታለን::</u> ሐረጎት አባይም የሠራውን ግለፊያ ነገር ሁሉ ስለምናውቅለት፣ የሚገባውን ወደፊት እናስብለታለን:: በማናቸውም እኳኋን ሁላችሁም ተጋግዛችሁ አስፍሐ ወልደሚካኤል እንዲመረጥ ይሁን:: ...... »

ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ ይህ መልዕክት ሲደርሳቸው ፊታውራሪ አስፍሐን ክፉኛ ጠረጠሯቸው:: ለካስ በእኔ ጀርባ እየተነጋገረ መንገዱን አዘጋጅቶ ኖሯል ? ብለው አሰቡ:: ሆኖም የንጉሡ ነገሥቱን ትዕዛዝ መፈጸም ስለአለባቸው፣ ፊታውራሪ ሐረጎት አባይን ጠርተው የአስፍሐ ምርጫ እንዲሳካ የተወዳዳሪ ቦታቸውን እንዲለቁ ጠየቋቸው:: የቀድሞው የተድላ ካቢኔ የኢኮኖሚ ሴክሬተሪ፣ ውድድሩ ውስጥ የገባሁት አቅሜን ለክቼ፣ እንደማሸንፍም እርግጠኛ ስለሆንኩ አልለቅም አሉ:: ቢትወደድም ለማስፈራራት፣ ምርጫው በገንዘብ ኃይል የሚከናወን ከሆነ፣ ንጉሡ ነገሥቱ ላለመቀበል የሚችሉ አይመስልዎትም ? ብለው ጠየቋቸው:: እኔ ሐረጎት በገንዘብ ኃይል አመረጣለሁ ብዬ አልተናገርኩም:: አለአግባብ ይህን የሚሉት እርስዎ ነዎት:: መብቴ በሕግ የተጠበቀ ስለሆነ የጀመርኩትን እገፋበታለሁ ብለው፣ ከቢሮአቸው ወጡ::

መላከ ሠላም ዲሚጥሮስ ገብረማርያም በአንድነቶች በኩል፣ ሼህ ዓሊ ራዳይ በቆላው ሕዝብ መማክርቶች በኩል ሆነው፣ ምርጫው ለአስፍሐ ወልደሚካኤል እንዲሆን የውድድሩን ትግል አፋፋሙት:: <u>የእስላም ሊግ መሪ የተባለው ኢብራሂም ሡልጣን፣ በድንገት ብድግ ብሎ፣ ከሐረጎት አባይ አስፍሐ ይሻሉኛል አለ::</u> ነገሩ ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ሆነ:: <u>የፌዴሬሽኑ አስተዳደር ሕጉን ተከትሎ እንዲቀጥል</u>

የደርጋሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸውን ሐረጐት አባይን ተቃውሞ፤ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ የመጡ ናቸው የሚባሉትን አስፍሐ ወልደሚካኤልን መደገፍ፤ ከኢብራሂም ሡልጣን ጨርሶ የሚጠበቅ አልነበረም።

ነሐሴ 8 ቀን 1955 ዓ.ም፣ በአዲሱ ፕሬዚዳንት በኢድሪስ መሐመድ አዱም ሊቀመንበርነት በተደረገው የፓርላማው ጠቅላላ ስብሰባ ላይ፤ በኤርትራ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምክትል እንደራሴ የሆኑት ፊታውራሪ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ ከስልሣ ሰባት (67) መማክርቶች ውስጥ አርባ ስምንት (48) የድጋፍ ድምፅ በማግኘት የተድላን የአንድ ዓመት የሥልጣን ዘመን ለመፈጸም የኤርትራ መንግሥት መሪ ሆነው ተመረጡ።

# ደጀጠኒው ደጃዝማች

ሐምሌ 30 ቀን 1955 ዓ.ም ሥልጣናቸውን መልቀቃቸውን ባስታወቁ ማግሥት፣ ከአሥመራ አዲስ አበባ ሲደርሱ፣ ለደጀጠኒው ደጃዝማች ያ የተለመደው ታርጋ የሌለው የቤተመንግሥት ጥቁር ካዲላክ አምሮ ተወልውሎ አልጠበቃቸውም። ከአውሮፕላኑ ሲወርዱም፣ ያ ጀብ ጀብ እያለ ኮሮጆአቸውን የሚቀበልና ወደ አውቶሞቢሉ የሚመራቸው የጸጥታ መቶ አለቃ አልነበረም።

በአውሮፕላን ጣቢያው መግቢያ ላይ ከተደረደሩት ታክሲዎች አንዱን ይዘው፣ አዲስ አበባ በመጡ ቁጥር ወደሚያርፉበት ወደ ራስ ሆቴል በመሄድ፣ አንድ ክፍል መኝታ ቤት ያዙ። በማግሥቱም ጠዋት በአንድ የወዳጅ አውቶሞቢል ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ሄደው እጅ ሲነሱ፣ ንጉሡ ነገሥቱ ለሶስት ደቂቃ ያህል ካነጋገሯቸው በኋላ፣ « ስለ ሥራህ የሚሆነውን እስክናስታውቅህ ድረስ እዚሁ ቆይ » አሏቸው። ይህ ቃል በሌላ አነጋገር ከአዲስ አበባ ሳትወጣ ደጅ ጥናትህን ቀጥል ማለት ነው። ደጃዝማች ተድላ በዚች ሶስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ፣ ችግራቸውን ሁሉ ለጃንሆይ ለመግለጽ አልደፈሩም። አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ብላታ ዳዊት እቁበእግዚእ የውጭ ጉዳይ ተጠባባቂ ሚኒስትር በመሆናቸው፤ ወዲያው ጃንሆይ ቢሮ ገብተው፣ ለቀድሞው የኤርትራ መሪ የሆቴል ወጪና አውቶሞቢል እንዲፈቀድላቸው አመለከቱ። ከመንግሥት ጋራዥ (በዚያን ጊዜ እርማ ጋራዥ) አንድ መለስተኛ አውቶሞቢል ከነ ሾፌሩ እንዲመደብላቸው፣ ሥራ እስከሚሰጣቸው ድረስ፣ የሆቴል አበል እና በየወሩም በኤርትራ መሪነት ያገኙት የነበረው ደሞዛቸው እንዲከፈላቸው የንጉሡ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ሆነ።

ደጀጠኒው ደጃዝማች አዲስ አበባ በከረሙበት ሰሞን ብዙ ነገሮች ለማስብና ለማሳሰል ሰፋ ያለ ጊዜ አግኝተው ነበር። ..... የሚተማመኑባቸው ወዳጃቸው ዓሊ ሙሣ ራዳይ፣ የግርማዊነታቸው እንደራሴ ዋና አማካሪ ሆነው በመሾማቸው በመገረም ላይ እንዳሉ፣ የአስፍሐ ወልደሚካኤልን ለቺፍ ኤግዜኩቲፍነት መመረጥ ነሐሴ 8 ቀን 1955 ዓ.ም ከፍ ባለ ድንጋጤ ሰሙ። ሥራዬን ለማደናቀፍ ብዙ ተንኮል ፈጽመውብኛል የሚሏቸው ሰው፣ በውድድሩ ላይ ሐረጐት አባይን ማሸነፍ አይችሉም የሚል ተስፋ ነበራቸው። ድል አድራጊው አስፍሐ የተመረጡት፣ በአርባ ስምንት (48) ድምፅ ብልጫ በመጀመሪያው ዙር መሆኑንም ሲሰሙ የበለጠ ተደነቁ። በ1952 ዓ.ም ተድላ ባይሩ አብርሃ ተሰማን አሸንፈው የተመረጡት በሁለተኛው ዙር በአርባ ሁለት (42) ድምፅ ብልጫ ብቻ ነበር። አስገራሚው ነገር

ይህ ብቻ አልነበረም። ኢብራሂም ሡልጣንና ዋና ዋና ቀንደኞች የተባሉት የእስላም ሊግ አባሎች ከሐረጉት አባይ አስፍሐ ይሻሉናል ግለታቸው ነው። ከዚህ በቀር ደግሞ በአዲስ አበባ፣ በታላላቅ የመንግሥት ሥራ ላይ ያሉት ኤርትራውያኖችም ንፋሱ ወደ አለበት በማዘንበል፣ የፊታውራሪ አስፍሐን መመረጥ በሞቀ ደስታ ተቀብለናል ብለው ሲፎልሉ ተመለከቱ። ስለ ፊታውራሪ አስፍሐም አዋቂነትና ከፍተኛ ችሎታ፣ ስለመልካም ጠባያቸውና አርቆ ተመልካችነታቸው፤ በአዲስ አበባ ራዲዮና ጋዜጦች ላይ አስተያየት ለመስጠት፣ የሚሻሙት ሰዎች ብዙ መሆናቸውን አዩ። እንግዲህ በዚህ ሁሉ ትርምስ ላይ ደጃች ተድላ አንድ ቃል ቢናገሩ፣ ብዙ ጉዳት እንደሚደርስባቸው ስለተረዱት፣ ዝምታን መረጡ።

ክቡር አቶ ሥረቀብርሃን ገብረእግዚእ የፖስታ ቴሌፎን ቴሌግራፍ ምክትል ሚኒስትር፣ በኤርትራ የተደረገው ምርጫ ውጤት ከታወቀ በኋላ፣ በአዩትና በተመለከቱት የተሰማቸውን ለአቶ መኰንን ሀብተወልድ የገንዘብ ሚኒስትር በሰፊው ገልጸዋል። ከሥረቀብርሃን አስተያየቶች ውስጥ የተቃረሙት ዋና ዋናዎቹ ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

*« ...... በአሁኑ ሰዓት በኤርትራ የተካሄደው ምርጫ ጉዳዩ የተድላና የአስፍሐ ይመስል፣ ቢያለበት የሚደረገው ትችት በጣም አስገርሞኛል። ቀም ነገሩ የእነዚህ ሁለት ሰዎች ትልቅነት ወይም ጨዋነት፣ ደካማነት ወይም አዋቂነት አልነበረም። እንደሚታወቀው፣ በትምህርትና በችሎታ ረገድ በተድላና በአስፍሐ መካከል ልዩነት የለም። ሁለቱም የጣልያን አራተኛ ክፍል ምሩቆች ናቸው። ከዚያ ወዲያ ተድላ ፍሎራንስ፣ አስፍሐ ሮማ ሄደው ነበር የሚባለው፤ በአካዳሚ ትምህርት ለመማር አይደለም። ለዚህም ደረጃ የሚበቁ አልነበሩም። እርግጥ አስፍሐ በተፈጥሮው ብልሁ ብልሆንና የታወቀ ፋሽስቶችንም በማገልገል ብዙ ነገሮች ስለቀሰመ፣ የፖለቲካን ጠባይ በመጠኑ አውቋል ማለት ይቻላል። ከፌደል አስቆጣሪነት በቀጥታ ተነስቶ የመጣው ተድላ ባይሩ ግን፣ የፖለቲካ ሥራ የሚካሄደው በእልህና በሥልጣን ስለመሰለው፣ አለአግባብ ሲጨቃጨቅ፤ ለጠላቶቹ ምቹ ሆኖ ወደቀ። አስፍሐ የሚበልጠው እዚህ ላይ ነው። ተድላ ከደጋፊዎቹ ጭምር ሲቃቃር፣ አስፍሐ ተቃዋሚዎቹን ወገኖቹ አድርጐ ይለውጣቸዋል። በዚህ ምርጫ ላይ የኢትዮጵያ ተወካዮች እና ኢብራሂም ሡልጣን ጭምር አስፍሐን መደገፋቸው በቂ ማስረጃ ነው።*

*...... አሁን ይህንን ሁሉ ለታሪክ አዘጋጆች ልተውና ወደ ዋናው ሀሣብ ልመለስ። « ....... ጃንሆይን መርዳት በቀጥታ ኢትዮጵያን መርዳት ነው። ይህን ቁም ነገር ለመፈጸም ደግሞ፣ ሀሳብን ሳይደብቁ በቀጥታ ማቅረብ ነው። ....... » እያሉ ጌታዬ ወዳጄ፣ በየጊዜው የሚመክሩኝን አስታውሳለሁ። ዛሬም ሀሳቤን የምገልጸልዎ በዚህ በተከበረው ቃልዎ ተመሥርቼ ነው።*

*...... በተድላ ቦታ ተተኪው አስፍሐ መሆኑ በጣም አሳስቦኛል። የቀድሞ የዱካ ዳውስታ ፊታውራሪ፣ ኢትዮጵያዊነቱን የበለጠ ለማሳየት ተንደርድሮ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ፣ እሳት እንዳይጭር እሰጋለሁ። የኤርትራ ሕዝብ የፌዴሬሽኑ ጥቅም ገብቶት መፍረሱን ይቃወማል ብዬ አላስብም። ነገር ግን ፌዴሬሽኑ ቢፈርስ የኤርትራ ሕዝብ በኢትዮጵያ አስተዳደር ሕይወቱ በአንድ ጊዜ፤ እንደሚሻሻልለት አለመስለው፣ እነ አስፍሐ የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ፣ በመጨረሻው ውጤቱ ከደስታ ወደ ክፉ ሀዘን እንደሚለወጥ በሚገባ መታሰብ አለበት። እንደዚህ በችኮላ ፌዴሬሽኑ የሚፈርስ ከሆነ ደግሞ፣ የኤርትራ ፕሮብሌም ተዳፍኖ ለብዙ ዘመን የጃንሆይን መንግሥት ሠላም የሚነሳ ክፉ በሽታ ይተክልለታል። ...... ኧረ ለመሆኑ ጌታዬ እስቲ ያስቡት? የኤርትራ ፌዴሬሽን ቢፈርስ ለኢትዮጵያ የሚያመጣው ጥቅም ምንድን ነው? የጃንሆይስ መንግሥት አሁን ባለበት ሁኔታ የኤርትራን የውስጥ*

*ፕሮብሌም ለመደረብ፣ አቅሙ የት ላይ ነው ? አሁን ማን ይሙትየ፤ የደጃች መስፍን ያገር ግዛት ሚኒስቴር ነው የኤርትራን የተወሳሰበ አስተዳደር የሚረከበው ? * ...... እንደዚህ ከሆነ የሚታሰበው በእውነቱ ቀልድ ነው። እኔ እንደርስዎ ወዳጅ ጌታዬ፣ ለጃንሆይና*

*ለኢትዮጵያ ቀንና ሌሊቱን በመጨነቅ ባላላልፍም፣ ከቀኑ ውስጥ አብዛኛዎቹን ሰዓቶች ስለ አገሬ ስለ ኢትዮጵያ ማሰቤ የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ፣ የስጋሁብትን ጉዳይ፣ ጌታዬ በቁም ነገር እንዲመለከቱት አጥብቄ እለምናለሁ። አስፍሐ ብዙ ደጋፊዎች አሉኝ ብሎ ፌዴሬሽን ለማፍረስ ሩጫውን እንዳይቀጥል ጃንሆይ አንድ ልጓም ሊያደርጉለት ይገባል ....... » ።*

*ፊርማ*

*ቀናተኛው ኢትዮጵያዊ ሠረቀ ብርሃን ገ/እግዚእ*

በዚያን ዘመን አቶ ሠረቀ ብርሃን፣ ኢትዮጵያን በሚመለከት በማናቸውም ጉዳይ፣ የኔ አስተያየት ካልተደመጠ ብለው ከብዙ ሚኒስትሮች ጋር በቀላሉ የሚጋጩ ሰው በመሆናቸው፣ ብዙዎቹ ከሩቁ ይሸሿቸዋል። አንዳንዶቹም በቅርብ የሚያውቋቸው ሠረቀ ብርሃን በአቴና ዩኒቨርስቲ <u>ፍልስፍና ለመማር ገብቶ</u> <u>ሶክራትን</u> ለማጥናት ያላለፈው ጊዜ፣ ጢባርሳም አድርጐ መርቆታል፤ እያሉ በቀልድ ይተቻሉ። ሰውየው ትዕግሥት የሚያጥራቸውና በጣም ቁጡ በመሆናቸው ነው እንጂ፣ የተማሩና የበሰለ አስተያየት እንዳላቸው የታወቀ ነው። ለኢትዮጵያም ያላቸው ፍቅርና ኩራት ወሰን የለውም። ቀናተኛው ኢትዮጵያዊ እያሉ የሚፈርሙትም፣ ስሜታቸው በዚህ መልክ ተመሥርቶ ነው። የኤርትራና የኢትዮጵያ መቀላቀል በዓል በአገር ፍቅር ማህበር አዳራሽ ሲከበር፤ «ኢትዮጵያ

ተሟላች ልጇን ተረከበች» በሚል ዜማ መድረኩ ላይ ወጥተው ለሕዝብ ንግግር ሲያደርጉ፣ ከስሜታቸው የተነሳ እንባቸው አልታገድ ብሎ እንዳስቸገራቸው ታይቷል።

አቶ መኰንን ሀብተወልድ፤ ከሠረቀ ብርሃን የቀረበውን ሀሳብ ምን እርምጃ እንደወሰዱበት ባይገልጡትም፣ በማስታወሻው ላይ « ከተናገረው ውስጥ የማይታበል <u>ፍሬ ነገር አለበት</u> » የሚል ቃል አሳርፈውበታል። ይህም ፍሬ ነገር የሚሉት ምናልባት የፌዴሬሽኑ መፍረስ፣ የኋላ ኋላ ለኢትዮጵያ ችግር ይፈጥራል የተባለውን ሳይሆን አይቀርም። የአስፍሐን ዘመነ መንግሥት በምንመለከትበት ጊዜ ሁኔታውን ለመገንዘብ ስለምንችል አሁን ወደ ደጃዝማች ታሪክ፣ እንመለሳለን።

ተድላ ባይሩ አዲስ አበባ ከደረሱበት ዕለት ጀምሮ፣ ምንም እንኳን አልፎ አልፎ ብቅ እያሉ የሚያነጋግሯቸው አንዳንድ ወዳጆች ባይታጡም፣ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ብቻቸውን በትካዜ መሆኑን የአጥታው ክፍል ሳይቀር፣ በዕለት ሪፖርቱ ይገልጠው ነበር። አንድ ጊዜ አሥመራ ላሉት ወዳጆቻቸው፣

* በዚያን ጊዜ ያገር ግዛት ሚኒስትሩ ደጃዝማች (ኋላ ራስ) መስፍን ስለሺ ነበሩ።

ለፊታውራሪ ሀድጉ ጊላጋብርና ለብላታ ደምሣስ ወልደሚካኤል በትግርኛ የጻፏቸውን ደብዳቤዎች የጸጥታው ክፍል ስለደረሰበት፣ ወደ አማርኛ ተርጉሞ ለንጉሠ ነገሥቱ ሲያቀርብ፣ ላቶ መኰንን ሀብተወልድ ግልባጩን ልኮላቸው ነበር:: ተድላ ባይሩ ለሁለቱም ወዳጆቻቸው የጻፏቸው ደብዳቤዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ፣ ሀሳባቸውን የገለጡት በሚከተለው አኳኋን ነበር::

...... ለጤናዬ ደህና ነኝ:: ሥራ ስለሌለኝ ይሆናል ትንሽ ሳልወፍር አልቀረሁም:: አዲስ አበባ እንደ ድሮው አልተቀበለኝም:: እኔም ይህን ያህል አልጠብቅም ነበር:: ሆኖም እስከዚህ ደግሞ ችላ እባላለሁ ብዬ አላሰብኩም:: እሳቸው (ጃንሆይ) ያነጋገሩኝ በትንሹ ነው:: ስለ ሥራዬ ታስቦ እስከሚነገረኝ እዚሁ ጠብቅ ተብያለሁ:: እንዳንድ ሰዎች እንደሚሉኝ ከአዲስ አበባ መውጣት የለብኝም ማለት ነው:: እንግዲህ ቀኑ እስኪደርስ መጠበቅ ነው:: ...... ጊዜ ስላለኝ ከአሥር ዓመት በላይ ለአገራችን ለኤርትራ አብረን የታገልነውን ሁሉ ሳስታውስ፣ በተለይ እኔ የተሳሳትኩት የት ላይ እንደሆነ፣ እስካሁን ፈልጌ ማግኘት አልቻልኩም:: ምንም አላጠፋሁም ለማለት አይደለም:: ኃላፊነት ተቀብሎ የማይሳሳት የለም:: ...... እዚህ፣ ስለእኔ የሚወራው፣ ተድላ ፌዴሬሽኑን አላፈርስም በማለቱ ጠላት በዝቶበት፣ ሥራውን ለቀቀ እየተባለ ነው:: ሁሉም የሚያምነው እንደዚህ ከሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም ማለት ነው:: የተባበሩት መንግሥታት ያዘጋጀውን፣ የኤርትራ ሕዝብ ወኪሎች የተስማሙበትን፣ ንጉሠ ነገሥታችን ያጸደቁትን ሕገ መንግሥት አክብሬ ለመሥራት፣ በመሀላ የተቀበልኩትን ኃላፊነት በትክክል ለመፈጸም ያደረግኩትን ጥረት፣ ሕዝቡ ካወቀልኝ ከዚህ የበለጠ መደሰቻ የለኝም:: ...... ወዳጆቼ እንደሚያውቁት ሁሉ፣ ፌዴሬሽን የሚፈርሰው በእኛ ለአስተዳደር በተመረጥነው ሰዎች ሳይሆን፣ በቀጥታ ሕዝቡ ሲፈቅድ ነው ብዬ በመታገሌ፣ ብዙ ጠላት እንደተፈጠረብኝ አልክድም:: ሕዝቡ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ከተስማማ ግን በመጀመሪያ የምደሰት እኔ ነኝ ብዬ ተናግሬ ነበር:: ይኸ ዛሬ ተረስቷል:: ማንም አያስታውሰውም:: ....... እኔ ሁሉም ነገር ሕጉን ተከትሎ ይፈጸም በማለቴ፣ ኢትዮጵያዊነቴ ላይ ጥርጣሬ እንዲገባ ያደረጉት ሰዎች፣ በእኔ ቦታ አስተዳዳሪ ሆነው መመረጣቸው በጣም ያሳዘነኝ መሆኑን አልደብቅም:: <u>ሆኖም የእኔ ኢትዮጵያዊነት ከእነሱ የሚቀንስ አለመሆኑን፣ አንድ ቀን ታሪክ ያወጣዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::</u> ለኤርትራም ሕዝብ፣ እነሱ እናደርግልሃለን የሚሉት፣ እኔ መሥራት ያልቻልኩትን ከሆነ፣ ከዚህም በቀር እኔ የማስበው መጥፎ ሆኖ፣ እነሱ ለወደፊት ዕድል የሚሠሩት ጥሩ ነው ተብሎ ሕዝቡ ደስ ካለው፣ እኔም ደስ ይለኛል:: ....... »

ከዚህ በላይ እንደታየው ደጃዝማች ተድላ በደብዳቤያቸው ላይ ንጉሠ ነገሥቱን አልወቀሱም:: በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ምሬታቸውን የገለጹት በእነ ፊታውራሪ አስፍሐ ላይ ነው:: በሥልጣን በቆዩበት ዘመን የተሳሳትኩት እምን ላይ ኖርዋል ? ብለው ለመመራመር መሞከራቸው ግምት የሚሰጠው ነው:: ብዙ ጊዜ ባለሥልጣኖች ከሥራቸው ሲፈናቀሉ ወይም ሲለቁ፣ ጥሩ በመሥራቴና በመትጋቴ ምቀኛው አላሠራም ብሎኝ ነው ይላሉ እንጂ፣ አጥፍቼ ይሆን ወይ ? ብለው ራሳቸውን ለመጠየቅ ሲሞክሩ አይታዩም:: አቦይ ተድላ በዘመናቸው የፈጸሙትን ስህተት እራሳቸው ፈልገው ባያገኙትም፣ የቅርብ ወዳጅ እስቦ ባይነግራቸውም፣ ጥፋታቸውን የሚተነትኑላቸው ሰዎች አላጡም:: እነዚህ የትናንት ወዳጆች የዛሬ ተቃዋሚዎች የሆኑት፣ ስለደጃች ተድላ እየተራቀቁ ሲያወሩ፣ <u>ካባ ማንዘርፈፉ፣ በፖሊስ ሞተር መታጀቡ፣ በወጡ በገቡ ቁጥር ጆብ ጆብ ማብዛቱ፣</u> ከሕዝብ የሚያራርቅ፣ ከወዳጅ የሚለይ መሆኑን ደህና አድርገን መክረን ነበር::

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ፣ ቀን ከአንድነቶች ጋር ሲያዜሙ እየዋሉ፣ ማታ ከፌዴራሊስቶች ጋር ሲጨፍሩ የሚያነጉት፣ አንድ ቀን ተጋልጠው ቅሌት ላይ እንደሚጥላቸው አስረድተን ነበር ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች ይህን ምክራቸውን ለባለ ጉዳዩ ሲለግሱ የሰማቸው ምስክር የለም:: እርግጥ ደጃች ተድላን ከሥልጣናቸው እስከ መፈናቀል ያደረሳቸው፣ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር ለማቆየት ስለፈለጉና የፖለቲካውንም ጥበብ ስላላወቁበት መሆኑ ጥርጥር የለውም::

ንጉሠ ነገሥቱም፣ « ..... ተድላ ያንን ያህል ስናቀርበውና ዕምነታችንን ስንጥልበት፣ ዘወር ብሎ በፌዴሬሽኑ አስተዳደር መመካቱ ያሳዝናል... » ብለው ቅር መሰኘታቸው እውነት ነው:: አቶ ተድላ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ሆነው እንደተመረጡ « ..... ተድላ የተቀበለውን ኃላፊነት በታላቅ ችሎታው እንደሚፈጽም እናምናለን:: ..... » በማለት ጃንሆይ ያደረጉት ንግግር፣ የፌዴሬሽኑን አስተዳደር እንዲያጠነክሩት ለማበረታታት አልነበረም:: አቶ ተድላም በዚያን ሰሞን ለንጉሠ ነገሥቱ ያሳዩት መንፈስ ፌዴሬሽኑን ወደዚያ ወርውሮ፣ የአንድነት ውህደቱን ለመገንባት እንደነበረ አይካድም:: ነገር ግን ጉዳዩን እያደር በጥልቅ ሲያዩት፣ በአሥመራም ሆነ በአዲስ አበባ፣ የኤርትራን መሪ ደረጃና ሥልጣን፣ እጅግ እንዲከበር ያደረገው፣ « እዚ ፈደራሲዮን ዝተባሕለ ሕገ » (ይህ ፌዴራሲዮን የተባለ ሕግ) ስለሆነ፣ አበይ ተድላ እንኳንስ ማፍረሱ ማላላቱም አይገባም አሉ::

ከ1941 እስከ 1952 ዓ.ም ድረስ፣ ኤርትራ ያለምንም ሀተታ ፍጹም ኢትዮጵያ ነች ብለው፣ ያለማቋረጥ ባደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ፣ እንዳሰቡት ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ፣ በመጨረሻ ተድላ ምን ዕድል ይጠብቁ ነበር ? ያለጥርጥር፣ የኤርትራ መንግሥት መሪ ተብዬ፣ ካቢኔ አቋቁሜ፣ ተድላ ተድላ እየተባልኩ ከሩቅ ይከበራል፣ አጀቡ ይደምቃል፣ ግርማ ሞገሱ ያሸበርቃል፣ ባለሥልጣን መሆኔ ብለው አላሰቡም:: ያለ ምንም ሀተታ ኤርትራ ፍጹም የኢትዮጵያ እንድትሆን ተፈርዶ ቢሆን ኖሮ፣ ከዚያ ሁሉ መልካም ሥራ፣ ከዚያ ሁሉ ድካም፣ ከዚያ ሁሉ ጥረት በኋላ፣ ተድላ ከሕይወታቸው የኑሮ መሻሻል ጋር (በሽልማትና በዳረጐት) ከደጃዝማችነት ማዕረግና ከአንድ አውራጃ ገዥነት በስተቀር ሌላ ምንም ሊደረግላቸው እንደማይችል፣ እሳቸውም እንደማይጠብቁ ይታመናል:: በደጅ ጥናት አዲስ አበባ በከረሙበት ጊዜ፣ ይህን ሁሉ ሳያሰላስሉት አልቀሩም:: አሁንስ ? ...... የማህበረ ፍቅሪ ሀገር ዋና ጸሐፊ፣ ለሕገ መንግሥት ዝግጅት የፓርላማ ፕሬዚዳንት፣ የመጀመሪያው የኤርትራ መንግሥት መሪ፣ ከሆኑ በኋላ፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምን ይሆን የሚጠብቁት ? ...... እድሜ ለጃንሆይ ለሕይወቴ መግፊያ አንድ ነገር አላጣም፣ ብለው ሻንጣቸውን ይዘው አዲስ አበባ ሲመጡ፣ ያለጥርጥር ከሙሉ እምነትና ተስፋ ጋር ነው:: በገቡ ማግስት በወዳጅ ተሽከርካሪ ተጉዘው ቤተመንግሥት ሲደርሱ፣ ያ « ተድላ እንዴት ሰነበትክ ? » የማለው ንጉሣዊ ቃል በለመዱት አኳኋን ሞቅ ብሎ ከጆሮአቸው ጥልቅ አላለም:: ሆኖም « ስለ ሥራህ አስበን እናስታውቅሀለን » የተባለው የንጉሠ ነገሥቱ ቃል፣ እንደ ጤና ጥበቃና እንደ ፖስታ ለመሣሰሉት መሥሪያ ቤቶች፣ የካቢኔ ሚኒስትርነት ደረጃ ነው ብለው አንዳንድ ሰዎች ስለተረጐሙላቸው፣ ተስፋቸውን አላደከሙም:: የሚኒስትርነቱ ቦታ የማይመች ከሆነ ደግሞ፣ በዚያን ጊዜ ሹመቱ የጃንሆይ ሥልጣን የሆነው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት ይሆናል፣ የሚል ወሬ በድንገት ሽው አለ:: ይህ ሹመት ከዚህ ቀደም ለብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ ተሰጥቶ የነበረ የክብር ቦታ በመሆኑ፣ ለሕግ መወሰኛው ፕሬዚዳንት ለደጃዝማች መንገሻ ውቤ እንደተደረገው ሁሉ፣ ለደጃዝማች ተድላም « እጅግ የተከበሩ »

የሚለው የመጠሪያ ማዕረግ ተቀጥሎበት ይሰጣቸዋል እየተባለ በሰፊው መወራቱን ቀጠለ::

ለደጃዝማች ተድላ፣ ሥራ ስለ መስጠት ጉዳይ አጥንተው ሀሳብ እንዲያቀርቡ ከጃንሆይ የታዘዙት፣ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ራስ አበበ አረጋይ የመከላከያ ሚኒስትር፣ አቶ መኰንን ሀብተወልድ የገንዘብ ሚኒስትር፣ አቶ ገብረወልድ እንግዳወርቅ ምክትል ጸሐፊ ትእዛዝ ነበሩ:: እነዚህ ታላላቅ ባለሥልጣኖች ጉዳዩን በሚያጠኑበት ጊዜ፣ ስለ ደጃች ተድላ ሹመት የሚወራውን ሁሉ መስማታቸው ባይቀርም፤ አዲስ አበባ ከሚነፍሰው ወሬ ይልቅ፣ ከአሥመራ « የሕዝብ አስተያየት » እየተባለ፣ በእንደራሴው ጽሕፈት ቤት በኩል የሚደርሰው ራፖር ይጠቅማል ብለው አሰቡ:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ከአሥመራ የእንደራሴው ጽሕፈት ቤት ብዕር የነካው ራፖር፤ በትክክሉ ከሕዝብ የተቃረመ አስተያየት ነው ማለት አይቻልም:: የሆነ ሆኖ ከብዙ ጥናት በኋላ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮሚቴ ለጃንሆይ ውሳኔ ያቀረበው ሀሳብ የሚከተለውን ነበር::

1. ደጃዝማች ተድላ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቀቁ የተባለው፣ በፓርላማው የኤርትራ ሕዝብ ወኪሎች አስተዳዳሪነታቸውን በብርቱ ስለነቀፉት፣ ወደፊት ለመቀጠል ባለመቻላቸው መሆኑን ተረድተናል::

2. ሥልጣናቸውን ሲለቁ፣ በወጉና በሥርዓቱ ለፓርላማው በማቅረብ ፋንታ፣ በሲኒማ ቤት የየመንገዱን ሕዝብ አሰባስበው በንግግር ስንብት ማድረጋቸው፣ መልካም ሞያ እንደፈጸሙ አያስገምታቸውም::

3. ደጃች ተድላ የተመረጡበትን ጊዜ በሠላም ፈጽመው፣ በሠላም ተሰናብተው ቢሆን ኖሮ፣ ጃንሆይ ለሚኒስትርነት ደረጃ ወይም ለፓርላማው ፕሬዚዳንትነት ሊያበቋቸው ይችሉ ነበር:: የደረሰው ሁኔታ ግን፣ በዚህ አኳኋን ለማሰብ የሚያመች ሆኖ አላገኘነውም::

3. በሁሉም በኩል ጉዳዩን በሰፊው ካጠናን በኋላ፤ ደጃች ተድላ ከዚህ ቀደም የሰጡትን ከፍተኛ አገልግሎት በማሰብ፣

ሀ/ የኑሮ መደገፊያ የሚሆን የጃንሆይ ልዩ ችሮታ እንዲሰጣቸው::

ለ/ አሁን በኤርትራ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ እስኪረጋጋ እና፣ የደጃዝማች ተድላም ጉዳይ እስኪዘነጋ ድረስ፣ አዲስ አበባ ከሚቆዩ፣ በውጭ አገር የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን የጃንሆይ መልዕክተኛ ሆነው፣ እንዲ መደቡ ቢደረግ ይሻላል ብለን በታላቅ ትህትና እናቀርባለን:: ...... »

ንጉሠ ነገሥቱ የቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ራፖር ከደረሳቸው በኋላ፣ « አክሊሉ ! አንተስ ምን ታስባለህ ? » ..... የሚል ጥያቄ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ላኩላቸው::

አቶ አክሊሉ ለጃንሆይ ባቀረቡት ሀሳብ « ..... የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ የነበረውን ሰው የእንድ የሌጋሲዮን ሚሲዮን ኃላፊ ማድረግ፣ በውጭውም ዓለም ሆነ በአገር ውስጥ፤ ብዙ ትዝብት ይፈጥራል ...... » አሉ:: አስተያየታቸውንም በመቀጠል፣ ...... ደጃዝማች ተድላ የኤርትራ መሪ ሆኖ በተመረጠ ጊዜ፣ በተባበሩት

መንግሥታት ባለሥልጣኖችና በኮር ዲፕሎማቲኮች ፊት ከጃንሆይ ሚኒስትሮች በላይ የተሰጠውን ከፍተኛ ፕሮቶኮል፣ የሚያስታውሱ ብዙዎች ናቸው:: ...... ስለ ደጃዝማች ተድላ በአፈሴል የሚታወቀው፣ ሥልጣኑን በገዛ ፈቃዱ ዴሚሲዮን አድርጎ መልቀቁን ነው እንጂ፤ በፓርላማ ተሽሯል ተብሎ አይደለም:: ከነበረበት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ ሹመት ቢሰጠው፣ ታላላቆቼ እንዳቀረቡት ሀሳብ የኤርትራ ሕዝብ ይቀየማል ማለት አይቻልም:: ቅር የሚሰኙ ሰዎች ቢኖሩ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂቶች ናቸው:: ..... ስለዚህ ፀኔ አገልጋይዎ አስተያየት የካቢኔ ሚኒስትርነቱ እንዲሰጠው እደግፋለሁ:: ይህ የማይቻል ከሆነ፣ ለጊዜው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት እንዲሰጠው ሀሳቤን ቢታላቅ ትህትና አቀርባለሁ:: ...... »

ጃንሆይ የአክሊሉን ሀሳብ አልተቀበሉም:: ለተድላ ምኑ ነው የሚያንሰው ? ራስ እምሩ እንኳን በውጭ አገር መንግሥታት ዘንድ ልዩ መልዕክተኛችን ሆኖ ይሠራ የለም ወይ? ይኸ እንዴት ተዘነጋ ? ...... በማለት ቀደም ሲል የጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮሚቴ አጥንቶ ያቀረበውን ሀሳብ አጸደቁ::

ቀድሞ በአቶ ገብረመስቀል ክፍለእግዚአ ተይዞ የነበረውን ቦታ፣ ከዘጠኝ ወራት ደጅ ጥናት በኋላ፣ ግንቦት 9 ቀን 1956 ዓ.ም ደጃዝማች ተድላ ባይሩ በስዊድን የግርማዊነታቸው ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ::